ፍኖተ
# ነፃነት

ፍኖተ ነፃነት ማክሰኞ ጥር 08 ቀን 2004 ዓ.ም.
ዋጋ 6:00

2ኛ ዓመት ቅጽ.2 ቁ.25

የኢትዮጵያ ሕዝብ የሉዓላዊ ሥልጣኑ ባለቤት እንዲሆን እንታገል!



## በፓርቲያችን የፕሮፓጋንዳ ፍረጃ ሲፈፅሙ ጠንካራ ፓርቲ እንዳለን የሚጠቁም ነው!

6

አቶ ወንድወሰን ፀጋዬ

# የህዝብ ኡኡታና የሊዝ አዋጅ




2

## ከሰኞ እስከ ሰኞ በሀገሪቱ የተካሄዱ ተቃውሞዎች?

ባለፈው ማክሰኞ ጥር 1 ቀን 2004 ዓ.ም በአዴት ከተማ ውስጥ 800 ሕገ ወጥ ቤቶች አሉ ተብሎ እንዲፈርሱ ለማድረግ ሲሞከር በተፈጠረ ረብሻ አንድ የወረዳው አመራር ሲሞት ሦስት ሰዎች ቆስለው ሆስፒታል መግባታቸውን የፍኖተ ነጻነት የዜና ምንጮች ገለጹ፡፡ እንደ ዜና ምንጮቻችን አገላለጽ "በዕለቱ በወረዳው የአነስተኛና ጥቃቅን እና በትራንስፖርትና መገናኛ ቢሮ ኃላፊ በሆኑት በአቶ ይበሉ ደሴ የሚመራ አፍራሽ ግብረ ኃይል በበርካታ ተጣቂዎች ታጅቦ በከተማው ውስጥ ሕገ ወጥ ቤቶች ናቸው የተባሉ 800 ቤቶችን ለማፍረስ ሲሞከር ቤቶቹ ከሚፈርስበት አንዱ ከታጣቂዎች ላይ መሣሪያ ነጥቆ በጀመረው ተኩስ በተፈጠረው ረብሻ የቡድኑ መሪ የነበሩት አቶ ይበሉ ደሴ ሲገደሉ የአፍራሹ ግብርረ ኃየል አባል ሆነው ከመጡት ውስጥ አቶ ገበያው ደመላሽ፣አቶ እንድሪስና ፖሊስ ይልማ የተባሉ ግለሰቦች በጥይት ተመተው ሆስፒታል መግባታቸውን ገልፀዋል፡፡ በዚህ ምክንያትም የከተማው ኗሪዎች የቤቶች ማፍረስ ሂደቱ እንዲቆም ተቃውሞ አቅርበዋል፡፡ ወደ ህትመት እስከገባንበት ሰዓት ድረስ ከተማው በከፍተኛ ጥበቃ ላይ የሚገኝ ሲሆን የወረዳው አመራር በተደጋጋሚ በስብሰባ ላይ የሚገኝ ሲሆን የከተማው ሕዝብ ደግሞ ቤቶቹ እንዳይፈርሱበት በንቃት በመጠባበቅ ላይ እንደሚገኝ የመረጃ ምንጮቻችን ገለፀዋል፡፡ የወረዳው አስተዳደር ጽ/ቤት በጉዳዩ ላይ . . .

ሌሎቹን በገጽ 3 ይመልከቱ

## በአወሊያ ኮሌጅ ትምህርት ተቋርጧል

በዓለም አቀፍ እስላማዊ ድርጅት ይተዳደር የነበረው የአወሊያ ትምህርት ቤት ከጥር 1 ቀን 2004 ዓ.ም ጀምሮ ለተወሰኑ ቀናት ትምህርት ተቋርጦ እንደነበር ይታወሳል፡፡ ተማሪዎችም "ጥያቄዎቻችን እስካልተመለሰ ድረስ ከግቢ አንወጣም፣ የተባረሩ የግቢው ሰራተኞችም ካልተመለሱ ትምህርት አንጀምርም" የሚልና ሌሎች ጥያቄዎችን ለኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ም/ቤት አቅርበው ምላሽ እንዳላገኙ፤ መንግስትም ለጥያቄያችን ....

10

### ወሎ ዩኒቨርስቲ

## ጠፋ የተባለው ተማሪ ልብሱ በደም ተበክሎ ተገኘ

በደሴ ከተማ በሚገኘው ወሎ ዩኒቨርስቲ ተማሪዎች በአስደንጋጭ ስጋት ውስጥ እንደሚገኙ የዜና ምንጮቻችን ገለፁ፡፡ እንደዜና ምንጮቻችን ገለፃ:: ‹‹በዩንቨርሲቲ ውስጥ ከሚማሩ ተማሪዎች ውስጥ ከአንድ ሳምንት ጀምሮ የተወሰኑ ተማሪዎች ባልታወቀ ሁኔታ ተሰወሩ ተብሎ ሲነገር ከረመ፡፡ ጠፉ ከተባሉት ውስጥ አንዱ ከምስራቅ ጎጃም ዳንግላ ወረዳ ሊሳ ቀበሌ የመጣው ተማሪ ሀብታሙ መለሰ አንዱ ነው፡፡ ዩኒቨርስቲውም መጥፋቱን ለማሳወቅ ፎቶ ግራፉን በማስታወቂያ ሰሌዳ ላይ ለጥፎት ነበር፡፡ ባለፈው ቅዳሜ ጠፋ የተባለው ተማሪ ጠፋ በተባለበት ዕለት የለበሰው ልብሱ በደም ተበክሎ ተገኘ፡፡ በዚህም የተነሳ ተማሪዎች ተረብሸው በመሰብሰብ ዩኒቨርስቲው ማብራሪያ እንዲሰጣቸው ጠየቁ፡፡ ምንም መልስ ባለማግኘታቸው የዞኑን ሀላፊዎች በሰልፍ ለመጠየቅ ግቢውን ለቀው ሲወጡ አድማ በታኝ ፌደራል ፖሊስ ደብድቦ ወደ ግቢ መለሳቸው፡፡ በአሁኑ ግዜ ወደ ዩኒቨርስቲው የሚወጣም ሆነ የሚገባ ተማሪ የለም፡፡ ተማሪዎች በከፍተኛ ጭንቀት ውስጥ ይገኛሉ››በማለት ገልፀዋል፡፡ ወደ ህትመት እስከገባንት ሰዐት ድረስ የአካባው ፖሊስ ሀሳብ እንዲሰጥበት ያደረግነው ሙከራ ለጊዜው አልተሳካም፡፡

## አንድነት በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ላይ ሕጋዊ እርምጃ ለመውሰድ እየተወያየ መሆኑን ገለፀ

አንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ /አንድነት/ ከሕዳር 16-18 ቀን 2004 ዓ.ም የኢትዮጵያ ሬዲዮና ቴሌቪዥን ድርጅት "አኬልዳማ" የሚል ዘጋቢ ፊልም በቴሌቪዥን ማሰራጨቱ ይታወቃል፡፡ በዚህም ፊልም ላይ የአንድነት አመራሮች ስምና ምስል አብሮ የቀረበ ሲሆን ይህንንም አስመልክቶ ቴሌቪዥን ድርጅቱ የፓርቲውን ስም አጥፍቷልና በተላለፈው ሰዓት የአየር ጊዜ ሰጥቶ ፓርቲው በተሰራው ፕሮግራም ላይ ያለውን አቋም ለሕዝብ እንዲገልፅ እንዲፈቀድለት ለኢትዮጵያ ብሮድካስት ባለሥልጣን ደብዳቤ መፃፉ ይታወሳል.....

10

## በሚዛን ተፈሪ ከተማ 41 የንግድ ሱቆች ታሽገዋል

10

## አነግ ወደ ሠላማዊ ትግል እንዲገባ ኢራፓ ጥሪ አቀረበ

11

የህዝብ ኡኡታና የሊዝ አዋጁ ባሳለፍነው ሳምንት መነጋገሪያ ሆኖ የሰነበተው በቅርቡ የፀደቀው የሊዝ አዋጅ ነው፡፡ አዋጁ በህዝብ ላይ ከፍተኛ ቁጣን ቀስቅሷል፡፡ በተለይ በአዲስ አበባ ከተማ የአዋጁን መንፈስ ለህዝብ ለማስጨበጥ በሚል ልዩ ልዩ ስብሰባዎች ተከናውነዋል፡፡ እነዚሁኑ ስብሰባዎች ዝግጅት ክፍሉ እንደሚከተለው አጠናቅረናቸዋል፡፡

# የሊዝ አዋጁን በተመለከተ ለክልሎች የተላለፈ መመሪያ የለም ተባለ

- አዋጁ ከመፅደቁ በፊት ውይይት መካሄድ ነበረበት -ተሳታፊዎች
- በተለያየ ቦታ እያወያያችሁ ያላችሁት የኢህአዴግ አባላትን እንጂ ሁሉንም ህዝብ አላከተተም ለምን?-ከተሳታፊዎች
- አዋጁ የፀደቀው የሀገሪቱን ህግ ተከትሎና ውይይት ተደርጐበት ነው- ሚኒስትር አቶ መኩሪያ ኃይሌ

የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ከመንግስት ኮሚኒኬሽን ጉዳዮች ጋር በመተባበር ጥር 4 ቀን 2004 ዓ.ም በራስ ሆቴል በአዲሱ የከተማ ቦታ ሊዝ አዋጅ ላይ በአዲስ አበባ ከሚገኙ ከተለያዩ የመንግስት ኮሚኒኬሽን ጉዳዮች ኃላፊዎች እና ከመገናኛ ብዙኃን ጋዜጠኞች ጋር ውይይት ተካሂዷል፡፡ ውይይቱም ቀኑን ሙሉ የተካሄደ ሲሆን ከተሳታፊዎች በርካታ ጥያቄዎች ተነስተው ከሚኒስትሩ ከአቶ መኩሪያ ኃይሌ ምላሽ ተሰጥቶባቸዋል፡፡




በሊዝ አዋጅ 721/2004 ዙሪያ በሚኒስቴሩ የመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ ኃላፊ አቶ እስራኤል ተስፋዬ ማብራሪያ ሰጥተዋል፡፡ በማብራሪያቸውም መሬት የመንግስት ብቸኛ ሀብት እንደሆነ ጠቅሰው በዚህም መሰረት የከተማ መሬት በሽልማት መልክ፣ በዕጣ፣ በምደባና በጨረታ ለተጠቃሚው እንደሚሰጥ ጠቁመዋል፡፡

መሬት በሽልማት መልክ የሚሰጠው አንድ ሰው ለሀገሩ በሚያበረክተው ከፍተኛ አስተዋፅዖ ሲሆን ይህም በከተማው ካቢኔና መንግስት ታምኖበት ውሳኔ ሲሰጥ ነው ብለዋል፡፡ በዕጣ የሚሰጠው መሬት ግን ለማኅበራት ሲሆን ይህም የሚሆነው በተመዘገቡበት ቅደም ተከተል መሆን እንዳለበት አስቀምጠዋል፡፡ በምደባ የሚሰጠው መሬት ደግሞ ሀገራዊ ፋይዳ ላላቸው ትላልቅ ፕሮጀክቶች እንደሆነና ይህንንም የሚፈቅዱት በክልሎች የክልል ካቢኔዎች በአዲስ አበባና ድሬዳዋ የከተማ መስተዳደር ካቢኔዎች ይሆናሉ ብለዋል አቶ እስራኤል፡፡ ሌላው የመሬት አሰጣጥ በጨረታ ሲሆን ይህም ወቅቱን ያገናዘበ፣ በግልፅና ተጠያቂነት ባለበት ሁኔታ እንደሚከናወን ተናግረዋል፡፡

በተለይ ከግንባታ ጋር በተያያዘ አንድ ሰው የከተማ ቦታ ወስዶ በ18 ወራት (አንድ ዓመት ከ6 ወር) ውስጥ ካላጠናቀቀና ግንባታው ከሚፈጀው 51% በታች የተከናወነ ከሆነ በተሰጠው የጊዜ ገደብ ሳያጠናቅቅ በመቅረቱ ለሊዝ የከፈለውና ያስያዘው ገንዘብ፣ ለግንባታው ያወጣው ወጪ፣ ጥቅም ላይ የዋለው ገንዘብ በባንክ ቢቀመጥ የሚያስገኘው ወለድና መሬቱ በመንግስት ሲወረስ ከሚገኘው ሽያጭ 5% ገንዘብ ተጨምሮ መሬቱን ወስዶ ለነበረው ለሚወረስበት አካል ካሳ ይከፈላል፡፡ መሬቱም በመንግስት ይወረስበታል ሲሉ አስረድተዋል፡፡ ነገር ግን የመሬቱ ባለ ይዞታ ከ51% በላይ ግንባታ ያከናወነ ከሆነ ባለቤቱ ለሌላ ወገን አስተላልፎ የመጠቀም ሙሉ መብት አለው፤ በዚህም ባለይዞታው በሚያገኘው ጥቅም ክፍልፋይ መንግስት መግባት አይችልም ሲሉ አስረድተዋል፡፡

አያይዘውም መሬትን በኪራይ የምንጠቀም ሲሆን ግብር የምንከፍለው ለቤት ወይም መሬቱ ላይ ላለው ንብረት ነው ብለዋል፡፡ በአሁን ወቅት በኢትዮጵያ 970 ከተሞች እንዳሉና በሊዝ የሚተዳደሩት ግን 150 ከተሞች እንደማይሞሉ ተጠቁሟል፡፡ አዋጁም የወጣው የከተማን ቦታ በአግባቡ ለማልማትና ለመጠቀም፣ ከዚህ በፊት የወጡ አዋጆች የህግ ክፍተት ስላለባቸው የሀገሪቱን ልማት ለማፋጠን ሲሉ አብራርተዋል፡፡

በመጨረሻም ከተሳታፊዎች በርካታ ጥያቄዎች የተነሱ ሲሆኑ ከተነሱትም መካከል ረቂቅ አዋጁ ከመፅደቁ በፊት ለምን ሰፊ ውይይት አልተደረገም? ምክንያቱም በአብዛኛው የኢትዮጵያ ህዝብ ደሃ ቢሆንም ያለውና የሚያወርሰው ሀብት መሬት ነውና፣ አዋጁ የወጣበት ዋና ዓላማ ምንድ ነው? መንግስት ገንዘብ ለመሰብሰብ አስቦ ነው ወይ? የሊዝ አዋጁን መውጣት ተከትሎ የክልል ከተሞች መስተዳደር ከዚህ በፊት ከመሬት ጋር ያለን ጉዳይ ማየት አቁመናል በማለትና ከፌደራል የተላለፈ መመሪያ እንዳለ እየገለፁ እንደሆነ አዋጁ ግን ከዚህ በፊት የነበረና በእንጥልጥል ያለ ጉዳይ 3 ወራት ውስጥ መጠናቀቅ እንዳለበት ተቀምጦ ሌላ መመሪያ ለምን አስተላለፋችሁ? እናንተ የምታወሩትና እታች ያሉ የከተማ መስተዳደርና ክፍለ ከተሞች ላይ ያሉ አካላት የሚያደርጉትና የሚናገሩት አይገናኝም፤ ህዝቡም በውጥረት ላይ ነውና ምን አስባችኋል? አዋጁ የፍ/ቤቶችን ሥልጣን እየነጠቀና እየተጋፋ ለከተማ መስተዳደር እየሰጠ አይደለም ወይ? የከተማ መስተዳደር የክፍለ ከተማና የወረዳ ባለሥልጣናት በዚህ የሊዝ አዋጅ ጉዳይ ለማወያየት በደብዳቤ የኢህአዴግ አባላትንና ደጋፊዎችን ጠርተዋል፡፡ ይሄ ህዝብን የሚወክልና ያሳተፈ ነው ወይ? ነዋሪው ህዝብ የበለጠ ቅሬታ እንዲሰማው እየተደረገ አይደለም ወይ? ለምን ሁሉም ነዋሪ በያለበት በማስታወቂያ አልተጠራም? ለምን ሰው ተመርጦ በደብዳቤ ሆነ? አዋጁ የበለጠ ለሙስና በር አይከፍትም ወይ ? የሚሉ ይገኙበታል፡፡

ሚኒስትሩ አቶ መኩሪያ ኃይሌም "ረቂቅ አዋጁ ከመፅደቁ በፊት ህጉን ተከትሎ ሰፊ ውይይት ተካሂዶበታል፡፡ አዋጁም አብዛኛውን ህዝብ ተጠቃሚ የሚያደርግ ነው; መንግስት ሰፊ ልማት እያከናወነ ስለሆነ አዎ ገንዘብ ያስፈልገዋል ሰፊ ልማት እያከናወነ ስለሆነ ገንዘቡ ለልማት ቢውል ምን ጉዳት አለው? ብለዋል፡፡ የሊዝ አዋጁን ተከትሎ ለክልሎች የተላለፈ ምንም ዓይነት መመሪያ የለም፣ ከዚህ በፊት ተጀምረው ያሉ የመሬት ጉዳዮች በ3 ወራት ውስጥ ሰርተው እንዲያጠናቅቁ በአዋጁ ላይ ስለተቀመጠ ያን ተከትለው የከተማ አስተዳደሮች መፈፀም አለባቸው እንጂ ስራ ማቆምና ባለጉዳይን መመለስ የለባቸውም፡፡ ምክንያቱም ከአዋጁ መመሪያና ደንብ ገና ስላልወጣ፣ ዝርዝር አፈፃፀሙ ስላልተገለፀ የተሰጣቸው መመሪያ የለም፡፡ የከተማ መስተዳደሮችና ኮሚኒኬሽን ጉዳይ ኃላፊዎች ላይ ያለውን የመረጃ ክፍተት ተገንዝበን ይህን ለመሙላትና ለማስረዳት እየተንቀሳቀስን ስለሆነ ወደፊትም ውይይት እንዳደርግበታለን፡፡ አዋጁ ከዚህ በፊት በመሬት ዙሪያ ይፈፀሙ የነበሩ የሙስና ተግባራትን ይቀንሳል እንጂ በር አይከፍትም ብለዋል፡፡

መሬት ነክ ላይ የሚፈራ ንብረት ካሳን በሚመለከት ማንኛውም ቅሬታ ያለው ሰው በይግባኝ ፍ/ቤት መሄድ እንደሚችልና በመሬት ጉዳይ ግን በፊትም ቢሆን ፍ/ቤት የማየት ስልጣን ስላልተሰጠው አዋጁ የፍ/ቤቶች ስራም ሆነ ሥልጣን አይጋፋም ብለዋል፡፡ ሌላው በዚህ በአዲሱ የመሬት ሊዝ አዋጅ በከተሞች የሚደረገውና እየተደረገ ያለው ውይይት የኢህአዴግ አባላትንና ደጋፊዎችን በደብዳቤ በመጥራት ነው የተባለው እውነት ከሆነ ትልቅ ስህተት ነው፤ ይህንንም እናጣራለን፡፡ መሆን ያለበት ማንኛውም የከተማው ነዋሪ እንዲሳተፍ እንጂ በደብዳቤ አድርጉና አወያዩ የሚል የተላለፈ መመሪያ የለም፤ መሆንም የለበትም በማለት ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ ሌላው በከተማ መሬት ሊዝ አዋጁ ዙሪያ መረጃ የሚፈልግ ካለ መልስ ለመስጠት ቢሮአቸው ክፍት እንደሆነ እና እሳቸውም ሆኑ ሌሎች የመ/ቤታቸው አመራሮች ፈቃደኛ መሆናቸውን ገልፀዋል፡፡

የመንግስት ኮሚኒኬሽን ጉዳዮች ጽ/ቤት የኢንፎርሜሽን አገልግሎት ዳይሬክተር ወ/ሮ ኃይማኖት ዘለቀ በበኩላቸው የመገናኛ ብዙኃን ጋዜጠኞች በዚህ ዙሪያ ትክክለኛውንና ሚዛናዊ መረጃ በማቅረብ የበኩላቸውን እንዲወጡ በማሳሰብ ውይይቱ ተጠናቋል፡፡

### የሊዝ አዋጅ ህዝባዊ ተቃውሞ ገጠመው

### - አሁንስ በዛብን- ነዋሪዎች

በቅርቡ በጥድፊያ የፀደቀው የሊዝ አዋጅ ህዝባዊ ተቃውሞ እንደቀረበበት ተገለፀ፡፡ ይህ የተገለፀው በአዲስ አበባ ከተማ የተለያዩ ወረዳዎች መንግስት ህዝቡን ባወያየበት ወቅት ነው፡፡ መንግስት በበኩሉ "ህዝቡ የአዋጁ የግንዛቤ ችግር አለ፡፡ አዋጁ ህገወጥ የመሬት ሽያጭንና ሙስናን ለመቆጣጠር ለልማት አመቺ መፍትሔ ነው" ይላል፡፡ የፍኖተ ነፃነት ሪፖርተሮች በተለያዩ ወረዳዎች በመዘዋወር የስብሰባውን ታዳሚዎች በማነጋገር በተገኘው መረጃ "አዋጁ የዜግነት ክብርን የሚገፍ ንብረት የማፍራት ህገ መንግስታዊ መብትን የሚጥስ አዋጅ ስለሆነ ተቀባይነት የለውም፡፡ አዋጁ እንዲሻር እስከመጨረሻው ድረስ እንታገላለን" በማለት በምሬትና በቁጣ ይገልጹታል፡፡

በቂርቆስ ክፍለ ከተማ ወረዳ ዘጠኝ የሚገኙ ስማቸው እንዳይጠቀስ ያልፈለጉ አንድ ተሰብሳቢ ከስብሰባው በኋላ አነጋግረናቸው በሰጡን አስተያየት "አዋጁ ከአወጣጡ ጀምሮ ችግር ያለበት ነው፡፡ አንድ አዋጅ ሲወጣ ከ48 ሰዓት በፊት ለህዝብ ተወካዮች መድረስ አለበት፡፡ የህዝብ ተወካዩ አዋጁን ተመልክቶ ከህዝብ አስተያየት ሰብስቦ ባለሞያ አማክሮ ወደ ም/ቤቱ ስብሰባ ይሄዳል፡፡ በረቂቅ አዋጁ ላይ አስተያየት ሰጥቶበት በቂ ውይይት ካደረገበት በኋላ ለዝርዝር እይታ ለሚመለከተው ቋሚ ኮሚቴ ይመራዋል፡፡ ቋሚ ኮሚቴው በረቂቅ አዋጁ ላይ ህዝብ እንዲወያይበት በመገናኛ ብዙኃን ጥሪ ያደርጋል፡፡ ባለሞያዎችን ይግባዛል፡፡ ያወያያል፡፡ የተሰጡ የህዝብ አስተያየቶችን የባለሞያ ምክሮችን አጠናቅሮ ረቂቅ አዋጁን አዳብሮና አሻሽሎ ለህዝብ ተወካዮች ስብሰባ ያቀርበዋል፡፡ ህዝብ ተወካዮች ም/ቤት መደበኛ ስብሰባ ተሻሽሎና ደብሮ የቀረበለትን አዋጅ በቂ ውይይት ካደረገበት በኋላ ያፀድቀዋል፡፡ ወይም አዋጁ አገርንና ህዝብን ይጐዳል ብሎ ካሰበበት ውድቅ ሊያደርገው ይችላል፡፡ መደበኛው የአዋጅ አወጣጥ አሠራር ይህ ነው፡፡ አንዳንድ ጊዜ የማይሰጡ አዋጆች ለቋሚ ኮሚቴ ሳይመራ በአስቸኳይ ሊፀድቅ የሚችልበት ሁኔታ አለ፡፡ ይህ አዋጅ በጥድፊያ የሚባልበት ምክንያት የለውም፡፡ የዜጐችን ህልውና የሚነካ ነው፡፡ የዚህን የሊዝ አዋጅ አፀዳደቅ የተመለከትን እንደሆነ የም/ቤቱ የ2004 ዓ.ም የሥራ ዘመን የተከፈተው ሰኞ ዕለት ነው፡፡ ም/ቤቱ ከሰዓት ከተከፈተ በኋላ ምሽት 12 ሰዓት ኢፌዴሪ ፕሬዝዳንት የህዝብ ተወካዮች አባላትን ራት ግብዣ አደረጉላቸው፡፡ በዚህ ወቅት ከምሽቱ 12 ሰዓት የዚህ የሊዝ ረቂቅ አዋጅ ለህዝብ ተወካዮች ም/ቤት አባላት እንደታደለ መረጃ አለኝ፡፡ በማግስቱ ጥዋት ሦስት ሰዓት ላይ ም/ቤቱ ተሰብስቦ አዋጁን አፀደቀ ተብሎ ተነገረን፡፡ ረቂቅ አዋጁ በፓርላማ አባላቱ እጅ የቆየው 15 ሰዓት አይበልጥም፡፡ ሰዓቱ ከህብረተሰቡ ጋር የሚያገኛቸው ጊዜ አይደለም፡፡ ከላይ እንደገለጽኩልህ ከ48 ሰዓት በፊት ረቂቅ መድረስ አለበት የሚለውን የፓርላማውን ህግ ጥሰው ነው በ15 ሰዓት ውስጥ ወደ ቋሚ ኮሚቴ ሳይመራ ህዝብና ባለሞያ ሳይመከርበት በጥድፊያ ያፀደቁት ፡፡

ምን መዓት መጣ? ምን የሚያጣድፍ ነገር ተፈጠረ? አዋጁ ለአገርና ለህዝብ ታስቦ ሳይሆን ለድብቅ ፍላጐታቸው ብለው ነው እስከ ዛሬ ድረስ እንዳየነው ኢህአዴግ ለህዝብና ለአገር የሚጠቅም አዋጅ ሳይሆን ለአገዛዝ የሚያመቸው ህዝብን አንገት የሚያስደፋ ለችግርና ለመከራ የሚዳርግ አዋጅ ሲያወጣ ቆይቷል፡፡ ይህም አዋጅ የዜጐችን የዜግነት መብት የሚገፍ ንብረት የማፍራት ተስፋን የሚያጨልም ነው፡፡ እኔ ከእንግዲህ አገር አለኝ ለማለት እቸገራለሁ" ብለዋል፡፡ ቦሌ ክፍለ ከተማ ወረደ 7 የተሰባሰበው ህዝብ ላቀረበው አስተያየትና ጥያቄ አሳማኝና በቂ መልስ ባለማግኘቱ ስብሰባውን ረግጦ ወጥቷል፡፡ ስብሰባውን የመሩት የወረዳው ዋና ሥራ አስፈጻሚና የክፍለ ከተማው ተወካይ በመግቢያቸው ላይ የሊዝ አዋጁ አስፈላጊነትና ጠቀሜታን በሪፖርታቸው ገልፀዋል፡፡ በ1986፣ በ1994 ዓ.ም እና በ2004 ዓ.ም የወጣውን

ወደ 11 ዞሯል

# ከሰኞ እስከ ሰኞ በሀገሪቱ የተካሄዱ ተቃውሞዎች?

ባሳለፍነው ሳምንት በመላው አገሪቱ በርካታ ጉዳዮች ተከስተዋል፡፡ የተከሰቱትን ሁኔታዎች ብዙአየሁ ወንድሙ እንደሚከተለው አቀነባብሮታል፡፡

## ምዕራብ ጐጃም አዴት ከተማ

ባለፈው ማክሰኞ ጥር 1 ቀን 2004 ዓ.ም በአዴት ከተማ ውስጥ 800 ሕገ ወጥ ቤቶች አሉ ተብሎ እንዲፈርሱ ለማድረግ ሲሞከር በተፈጠረ ረብሻ አንድ የወረዳው አመራር ሲሞት ሦስት ሰዎች ቆስለው ሆስፒታል መግባታቸውን የፍኖተ ነጻነት የዜና ምንጮች ገለጹ፡፡ እንደ ዜና ምንጮቻችን አገላለጽ "በዕለቱ በወረዳው የአነስተኛና ጥቃቅን እና በትራንስፖርና መገናኛ ቢሮ ኃላፊ በሆኑት በአቶ ይበሉ ደሴ የሚመራ አፍራሽ ግብረ ኃይል በበርካታ ተጣቂዎች ታጅቦ በከተማው ውስጥ ሕገ ወጥ ቤቶች ናቸው የተባሉ 800 ቤቶችን ለማፍረስ ሲሞከር ቤቶቹ ከሚፈርስበት አንዱ ከታጣቂዎች ላይ መሣሪያ ነጥቆ በጀመረው ተኩስ በተፈጠረው ረብሻ የቡድኑ መሪ የነበሩት አቶ ይበሉ ደሴ ሲገደሉ የአፍራሹ ግብርረ ኃየል አባል ሆነው ከመጡት ውስጥ አቶ ገበያው ደመላሽ፣አቶ እንድሪስና ፖሊስ ይልማ የተባሉ ግለሰቦች በጥይት ተመተው ሆስፒታል መግባታቸውን ገልፀዋል፡፡ በዚህ ምክንያትም የከተማው ኗሪዎች የቤቶች ማፍረስ ሂደቱ እንዲቆም ተቃውሞ አቅርበዋል፡፡

ወደ ህትመት እስከገባንበት ሰዓት ድረስ ከተማው በከፍተኛ ጥበቃ ላይ የሚገኝ ሲሆን የወረዳው አመራር በተደጋጋሚ በስብሰባ ላይ የሚገኝ ሲሆን የከተማው ሕዝብ ደግሞ ቤቶቹ እንዳይፈርሱበት በንቃት በመጠባበቅ ላይ እንደሚገኝ የመረጃ ምንጮቻችን ገለፀዋል፡፡ የወረዳው አስተዳደር ጽ/ቤት በጉዳዩ ላይ አስተያየት እንዲሰጥበት ያደረግነው ሙከራ ለጊዜው አልተሳካም፡፡

## ጅማ ኑኒቨርስቲ

ከ17 ሺ በላይ ተማሪዎች ይገኙበታል በሚባለው ጅማ ዩኒቨርስቲ በውጥረት ውስጥ መኖሩን የዜና ምንጮቻችን ይገልጻሉ፡፡እንደ ዜና መንጮቻችን ገለጻ ከሆነ "ጥር 2 ቀን 2004 ዓ.ም ከምሽቱ አንድ ሰዓት ላይ በአንድ የዩኒቨርሲቲው ሠራተኛ የተጀመረው ተማሪዎችን የማስፈራራትና የመፈረጅ እንቅስቃሴ ተማሪዎችን በማስቆጣቱ ውጥረትን ከመፍጠሩም በላይ የተለያዩ የመብት ጥያቄዎችን አስከትሏል" ብለዋል፡፡ የዜና ምንጮቻችን እንደ ሚሉት "ዩኒቨርስቲው ውስጥ ተማሪዎችን በደቡብ፣በትግራይ፣በኦሮሚኛና በአማርኛ ተናጋሪነት በአራት ቦታ በማደራጀት የኢህአዴግ ደጋፊ እንዲሆኑና አንደኛው ቡድን ከአንዱ ቡድን ጋር እንዳይግባቡ በጥርጣሬና በሥጋት እንዲተያዩ ሲደረግ ቆይቷል፡፡ በዩኒቨርስቲው ውስጥ የፀሎት ሥርዓት ተከልክሏል፡፡ ይህ በእንዲህ እያለ የዚህ የአራቱም ቡድን አስተባባሪ ነው የሚባለው አንድ የዩኒቨርስቲው ሠራተኛ ግለሰብ ጥር ሁለት ቀን ከምሽቱ አንድ ሰዓት ላይ የተወሰኑ ተማሪዎችን ለማስፈራራትና ለማሸማቀቅ በማሰብ እናንተ የብርሃኑ ነጋን ፖለቲካ ታራምዳላችሁ ብሎ በመፈረጁ ተማሪዎቹ በምን ማስረጃ ትፈርጀናለህ? እንዴት ትከፋፍለናለህ? አንተ ራስህ ማነህ? በማለት ባነሱት ጥያቄ በተማሪዎች መካከል ውጥረትን ፈጥሯል" ይላሉ፡፡ በዚሁ የተነሳ መረጃው ለተማሪዎች በመዳረሱ ተማሪዎች ተረጋግተው ትምህርታቸውን እንዳይማሩ ችግር ተፈጥሮአል" ሲሉ ያብራራሉ፡፡ በመጨረሻም "አንዳንድ ኃላፊነት የማይሰማቸውና ደካማ ግለሰቦች በኢህአዴግ ስም እየቀረቡ የሚበጣብጡን ይታቀቡልን የሚመለከተው አካልም ያስታግሥልን" በማለት ተማሪዎች ማሳሰቢያ እንደሚሰጡም ተጠቁሟል፡፡

## የጊቤ ተፈናቃዮች

የሸዋና የጅማ አዋሳኝ በሆነው ጊቤ በረሃ ውስጥ ከ20 ዓመት በፊት ሠፍረው በግብርና ይተዳደሩ የነበሩ አርሶ አደሮች መፈናቀላቸውን ምንጮቻችን ገለጹ፡፡ የዜና ምንጮቻችን እንደሚሉት "በበረሃው ውስጥ ከ20 ዓመት በፊት (ካለፈው ሥርዓት ጀምሮ) ከጐጃም፣ከወሎ፣ከሸዋና ከተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች ባዶ ቦታ ላይ ሠፍረው በግብርና ይተዳደሩ የነበሩ 126 አባወራዎች መጤዎች ስለሆናችሁ አካባቢውን ልቀቁ በማለት የአካባቢው ባለሥልጣናት በፈጠሩባቸው ጫና ከመኖሪያ ቤታቸው ተፈናቅለው ለልመና መዳረጋቸውን" ገለፀዋል፡፡

ተፈናቃይ ናቸው የተባሉ አንድ ግለሰብ ጠይቀን በሰጡን መልስ "126 አባወራዎች ተፈናቅለናል፡፡ በየሥራችን በርካታ ሴተሰብ አለን ከ20 ዓመት በላይ ሙሉ ያፈራነውን ንብረት ትታችሁ ውጡ ብለው አስለቅቀውናል፡፡ ከ20 ዓመት በፊት በረሃ ውስጥ ባዶ ቦታ በማግኘታችን በረሃውን በማልማት እንኖር ነበር፡፡ በርካታ ፍራፍሬዎችን ተክለን ለፍሬ ባበቃንበት ወቅት መሬቱ የእናንተ አይደለም፡፡ በረሃ ውስጥ ህይወታችንን ሸጠን ከአውሬ ጋር ታግለን ያፈራነውን ልማት የእናንተ አይደለም፡፡ ብለው አባረሩን፡፡ ለበርካታ የበላይ አካላት አቤቱታ ብናቀርብም መልስ አላገኘንም፡፡ በአሁኑ ወቅት መኪናመንገድ ላይ ፈሰን አላፊውን አግዳሚውን መኪና አስቁመን ለመለመን ተገደናል፡፡ ልጆቻችን አሮጊትና ሽማግሌዎች በረሃብ ሊያልቁብን ነው፡፡ የወገን ያለህ በሉልን ጩኸታችንንም ለሚመለከተው አድርሱልን" ሲሉ ጥሪያቸውን አቅርበዋል፡፡

## አዳማ ዩኒቨርስቲ

በአዳማ ዩኒቨርስቲ በተፈጠረ ግጨት በርከታ ተማሪዎች ለእስራት በመዳረጋቸው ዩኒቨረስቲው ውስጥ ውጥረት መንገሱን የመረጃ መንጮቻችን ገልፀዋል፡፡ የመረጃ መንጮቻችን አንደሚሉት "ዩኒቨርስቲ ተማሪዎች ወደ ዩኒቨርስቲው ከመግባታቸው በፊት በየክልል በነበሩበት ወቅት የሌላውን ቋንቋ በጥላቻና በጐጂነት እንዲመለከቱት ተደርጐ ስለሚያድጉ ዩኒቨርስቲ ሲገናኙ አንዱ ቋንቋ ተናጋሪ የሌላውን ቋንቋ ተናጋሪውን በጥላቻ ይመለከቱታል፤በጫወታና በአጋጣሚ የሚፈጠርን የቃላት አለመግባባት እጅግ በማጋነንና የልዩነትና የጥላቻ ትርጉም በመስጠት ግጭት እንዲፈጠር ምክንያት ሆኗል፡፡ አንዳንድ ግለሰቦችም በተማሪዎች መካከል መግባባት እንዳይፈጠር ሥራዬ ብለው የሚሠሩ አሉ" በማለት ይገለጻሉ፡፡

በማያያዝም "ዓላማቸው የማይታወቁ አንዳንድ የዩኒቨርስቲው ሠራተኞችና አንዳንድ ተማሪዎች በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ ተማሪው አንድ ቋንቋ እንዳይናገር፤ ትምህርቱን ጥሎ የገዢውን ፓርቲ ሥራ በመደገፈና በማድነቅ እንዲያራግብ ግፊት ይደረጋል፡፡ ከምንም ነፃ ሆኖ ትምህርቱን ብቻ መከታተል የሚፈልገውን ተማሪ ደግሞ ምክንያት እየፈለጉ የትንኮሳ ሥራ ይሠራሉ፡፡ በዚሁም ምክንያት በርካታ ተማሪዎች ለእስራት ተደርገዋል" በማለት ይገልጹታል፡፡

## ወለጋ ዩኒቨርስቲ

በለቀምት ከተማ የሚገኘው የወለጋ ዩኒቨርስቲ በምግብ መበላሸት በተነሳ ጥያቄ ተማሪዎች መታሰራቸውንና አንድ ተማሪ በምግብ መመረዝ ሆስፒታል መግባቱን፤በዚህ የተነሳ በተማሪዎች መካከል ከፍተኛ ውጥረት መፈጠሩን የዜና ምንጮቻችን ይገልጻሉ፡፡ እንደ መረጃ ምንጮቻችን ገለጻ "በዩኒቨርስቲው ምግብ አቅርቦት ጥራት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተበላሸ ቆይቷል፡፡ በተለይ የገና በዓል ዕለት የቀረበው ወጥ በጠቅላላ ውሃ ይዘት ያለው በመሆኑ የተማሪዎችን ቁጣ ቀስቅሷል፡፡ በዚሁ ዕለትም የምግብ መመረዝ ተፈጥሮ አንድ ተማሪ በጥና ታሞ ሆስፒታል ይገኛል፡፡ በዚህ ምክንያት ተማሪዎች ያነሱት የምግብ ጥራት ጥያቄ በዩኒቨርስቲው ኃላፊዎች ተገቢ ያልሆነ መልስ መስጠት እና ለጥያቄያቸው ትኩረት አለመስጠት ቁጣን ቀስቅሷል የትምህርት ፕሮግራሙንም አስተጓጉሏል" ይላሉ፡፡ በዚህ የተነሳ "በአሁኑ ጊዜ በዩኒቨርስቲው ውስጥ ጥያቄው ባለመመለሱና ችግሩ ባለመስተካከሉ በዩኒቨርስቲው ውስጥ ውጥረትን አስከትሏል" ሲሉ ምንጮቻችን ይገልጻሉ፡፡

## ጋምቤላ ክልል በውጥረት ውስጥ ነው

በጋምቤላ ሕዝብ አንድነት ደሞክራሲያዊ ንቅናቄና በክልሉ መስተዳድር በጋራ በመሆን ከኢህአዴግ ጽ/ቤት በሄዱ ተወካዮች አማካኝነት ሲከናወን በቆየው ግምገማ ውጥረት መከሰቱን የዜና መንጮቻችን የገልጻሉ፡፡ እንደ መረጃ መንጮቻችን ገለጻ "በተለይ በ1996 ዓ.ም በአኝዋክ ሕዝብ ላይ በተደረገው ጭፍጨፋ የተነሳ ሂስ የቀረበባቸው የክልሉ መስተዳድር አቶ ኦማት ኦባንግ አሎም በዚህ የምንጠየቅ ከሆነ እኔ ብቻዬን ልጠየቅ አይገባም፡፡ የፌዴራል መስተዳድሩ ተጠሪ የሆኑት አቶ መለስ ዜናዊ አብረው በሕግ መጠየቅ አለባቸው፡፡ ብለው በማለታቸው ከኢህአዴግ ጽ/ቤት በሄዱ የግምገማው መሪዎችና በአንዳንድ የክልሉ ባለሥልጣናት ድንጋጤና ቁጣን ቀስቅሶ በጥዋቱ ስብሰባ አቶ ኦማት ኦባንግ ከድርጅቱ እንዲባረሩ እንዲሁም ከክልሉ መስተዳድርነታቸውም እንዲነሱ ተወሰነ" ብለዋል፡፡ በመቀጠልምደ ሂደቱን ሲገልጹ "ስብሰባው ይህንን ወስኖ ለምሳ ከወጣ በኋላ በምሳ እረፍት ላይ የርዕሰ መስተዳድሩ ከድርጅቱ መባረርና ከርዕሰ መስተዳድርነት መነሳት ሊያስከትል ይችላል የተባሉ በርካታ ጉዳዮች እየተነሱ ሁሉም በየግሉ ሲነጋገርበት ቆየ፡፡ በውሳኔው ያልተደሰቱ አንዳንድ ተሰብሳቢዎች ክልሉን ለዳግም ጭፍጨፋ እያዘጋጃችሁ ነው እስከማለት እርስ በእርስ ሲጨቃጨቁ ቆይተው ወደ ስብሰባ ተገባ፡፡ በስብሰባው ላይ ጉዳዩ በድጋሚ ተነስቶ እንዲታይ ከተደረገ በኋላ ከድርጅቱ መባረሩ እንዲቀር ከኃላፊነታቸው ዝቅ ብለው እንዲሰሩ የሚል ውሳኔ ተወስኗል፡፡" ሲሉ ይገልጻሉ፡፡

የግምገማው ሂደት አሁንም ያልተጠናቀቁ ቢሆንም ከተማው በከፍተኛ ጥበቃ ውስጥ ሲሆን ውጥረቱ አለመርገቡን የዜና ምንጮቻችን ይገልጻሉ፡፡ በክልሉ የተፈጠረው ውጥረት ያሳሰባቸው የአሜሪካን አምባሳደር ጋምቤላ ተገኝተው ግምገማውን ሲከታተሉ እንደነበር የዜና ምንጮቻችን ተናግረዋል፡፡

## በደቡብ ክልል መፈናቀል እየተከሰተ ነው

በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች ክልላዊ መንግሥት የተለያዩ ዞኖች የሰብአዊ መብት ጥሰትና የዴሞክራሲያዊ መብት አፈና እንዲሁም የመሬት ነጠቃ፣እስራት፣ድብደባና ቅጣት እየተባባሰ መሄዱን በሳምንቱ የጐሉ መረጃዎች ለዝግጅት ክፍላችን ቀርበዋል፡፡ የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት /መኢአድ/ ጽ/ቤት፣የጋሞ ዴሞክራሲያዊ ሕብረት ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ በላኩልን መረጃ ገልፀዋል፡፡

የመኢአድ ሥራ አስፈጻሚና ሕዝብ ግንኙት ኃላፊ ወ/ሪት መሶበ ቅጣው እንደገለጹት "በደቡብ ክልል የተለያዩ ዞኖችና ወረዳዎች ካድሬዎችና ደህንነቶች በአባሎቻችንና በደጋፊዎቻችን ላይ ከፈተኛ ወንጀል እየፈፀሙ ናቸው፡፡ ዜጐችን በአመለካከታቸው ብቻ መሬታቸውን ይነጥቃሉ፤ ያሰራሉ፤ይደበድባሉ፤ከሕግ ወጪ እያሰሩ ይፈታሉ፡፡ በገንዘብ ይቀጣሉ፤ ዛቻ ማስፈራሪያና ወከባ ይፈጽማሉ፡፡ በሌላ በኩል የጋሞ ዴሞክራሲያዊ ሕብረት በላከልን ሰነድ እንደገለፀው በግሞ "በደቡብ ክልል የመልካም አስተዳደር እጦት፣የሙስና መስፋፋት፣የሀገርና የሕዝብን ሀብትና ንብረት ዘረፋና በሕዝብና በዜጐች ላይ የሚደርስ ግፍ፣በደልና መከራ ከሁሉም የሀገሪቱ ክፍል በላይ በጣም የከፋውና ሃይ ባይ የጠፋው በደቡብ ክልል ነው" ብሏል፡፡ በደል ደርሷል የሚላቸውና የሕዝብን ጥያቄ በመሣሪያ ለመፍታት ሕዝቡን በፌደራል ፖሊስ በመከበብ አፈና እየተፈጸመ መሆኑን በመግለጽ ድርጊቱ ተገቶ መፍትሔ እንዲፈለግ ለጠ/ሚኒስትሩ ለም/ጠ/ሚንስትሩ እና ለሰብአዊ መብትና ለፀረ ሙስና ኮሚሽን ጠይቋል፡፡

ፍኖተ -ነፃነት ጋዜጣ ሐምሌ 2003 ዓ.ም ተመሠረተ። ፍኖተ ነፃነት በአንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ (አንድነት) ሥር የሚታተም በፖለቲካዊ፣ በማህበራዊ፣ በኢኮኖሚያዊ፣ በወቅታዊ ጉዳዮችና በመዝናኛ ላይ የሚያተኩር የፓርቲው ጋዜጣ ነው።

**ጋዜጣችን እንደ ፓርቲ ልሳን ብቻ ሳይሆን እንደ አንድ ሚዛናዊ የግል ጋዜጣ ሆኖ ማገልገል ይፈልጋል የማንኛዉም ሰዉ ሀሳብና አመለካከት የሚስተናገድበትና የሚንሸራሸርበት እንዲሆን እንሻለን ሰፊ የሚዲያ ሽፋን ያለዉ ኢህአዴግም በዚህ ሚዲያ አቋሙንና ፖሊሲዉን ለማቅረብ ቢፈልግ ክፍት ነዉ**

ዋና አዘጋጅ፡-
አንዳርጌ መሥፍን
አድራሻ፡-
የካ ክ/ከተማ ወረዳ 12
የቤ.ቁ አዲስ

አዘጋጆች፡-
ብዙአየሁ ወንድሙ
ብስራት ወ/ሚካኤል

አምደኞች፡- ዶ/ር ኃይሉ አርዓያ
ኢ/ር ዘለቀ ረዲ
አንዱዓለም አራጌ
ግርማ ሠይፉ
ዳምጠው አለማየሁ
ወንድሙ ኢብሳ
ስለሞን ስዩም
ግርማ ሞገስ
ደረጀ መላኩ
ቀለሙ ሁነኛው

ኮምፒውተር ጽሑፍ፡-
የሺ ሃብቴ
ብርቱካን መንገሻ

አከፋፋይ፡-
ነብዩ ሞገስ

አሣታሚው፡-
አንድነት ለዴሞክሲና ለፍትህ ፓርቲ(አንድነት)

አድራሻ፡- አራዳ ክ/ከተማ ወረዳ 07 የቤ.ቁ አዲስ

አታሚ፡- ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት
አራዳ ክ/ከተማ ቀበሌ 07 የቤ.ቁ 984

የዝግጅት ክፍሉ

ስልክ +251 922 11 17 62
+251 913 05 69 42
+251 118-44 08 40
+251 923 11 93 74

ፖ.ሳ.ቁ፡ 4222

ኢሜይል፡- fnotenetsanet@yahoo.com
udjparty@gmail.com
andinet@andinet.org

ፋክስ ቁጥር፡- +251-111226288



# ርዕሰ አንቀፅ

## ሙሰኞችን በጀርባ አዝሎ "ልማት አካሂዳለሁ" ማለት የሚታሰብ አይደለም

ዛሬ ዜጎች የኔ የሚሉት አንዳች ነገር ስለሌላቸው "ሰርቼ ነገ ያልፍልኛል" የሚለው ተስፋቸው ተሟጦ ካለቀ ቆይቷል፡፡ በምትኩ ልመና እንደ መልካም ባህል እየተወረሰ ነው፡፡ አሳፋሪና አሸማቃቂ መሆኑ ከቀረ ውሎ አድሯል፡፡ ድሮ ድሮ አጥቶ አንደመለመን ያለ አሣፋሪና አንገት አስደፊ ነገር አልነበረም፡፡ ዛሬ ግን ሀብትና ንብረት ማጣት ብቻ ሣይሆን ክብራችንንም፣ማኅበራዊ ሞራላችንም ተገፈን ቅስማችን ተሰብሮ ሰርተው ያልደከሙ እጆች ለምፅዋት ጥየቃ ተዘርግተው ማየት እጅግ አድርጎ የሚያበሳጭና የሚያስቆጭ ጉዳይ ነው፡፡ ሕዝባችን ለዚህ አሳፋሪና ጎስቋላ ሕይወት የተዳረገው ኃላፊነት የሚሰማው መንግሥት ሊያገኝ ባለመቻሉ እንደሆነ ብዙዎች በመሬት ሲገልፁ ይሰማሉ፡፡

እንደ እውነቱ ከሆነ ኢትዮጵያ በተደጋጋሚ ሁኔታ ቡድርቅ ብትመታም ዜጎቿን የምትመግብበት በቂ የሆነ የተፈጥሮ ሀብት አላት፡፡ ያለመታደል ጉዳይ ሆኖ ግን የተፈጥሮ ሀብቷንና ድንግል መሬታችን የውጭ ሀገራት ቱጃሮች በኢንቨስተር ስም ሲቀራመቱት የኛዎቹ ትንሽ እርሾ ያላቸው ወደ ዳር ተገፍተው የበይ ተመልካች ሆነው ስናይ የኢሕአዴግ መንግሥት የውጭ አልጋ የቤት ቀጋ መሆኑን እንረዳለን፡፡

ከፍ ብለን ለመግለጽ እንደሞከርነው ኢትዮጵያ በቀዳማዊ ኃ/ሥላሴም ሆነ በደርግ አገዛዝ ዛሬም በኢሕአዴግ አገዛዝ በድርቅ ብትጠቃም ዜጎቿን ለመመገብ ግን የምትሰንፍ አገር አልነበረችም፡፡ እሷን እየመታት ያለው ድርቅ "የመልካም አስተዳደር እጦት ድርቅ ነው" መልካም አስተዳደር ከሌለ ደግሞ ፍትሕ ሊኖር አይችልም፡፡ ፍትሕ ከሌለ ደግሞ እድገት ብሎ ነገር የሚታሰብ አይደለም፡፡ መልካም አሥተዳደር እንዳይሰፍን ደግሞ ጋሬጣ የሆነው በጎሳ የተማከለ ሥርዓት በመዘርጋቱና ይህነኑ ተከትሎ ጎሰኝነት ሥር በመሥደዱ ነው፡፡

ጎሰኝነት ልዩነት ነው፡፡ ልዩነት ደግሞ አድልኦ ነው፡፡ አንዱ ሌላውን አጥቅቶ፣ከቻለም አጥፍቶ ለራሱ ተንሰራፍቶ ለመግዛት የሚደረግ ሩጫ ነው፡፡ መቸም ቢሆን አገርን በጎሣ ሥርዓት አዋቅሮ በጋራ ሰርቶ በጋራ ለመበለፀግ የሚታሰብ አይደለም፡፡ ይህንን ሀቅ ዛሬ አገራችን ያለችበት ተጨባጭ ሁኔታ ቁለጭ አድርጎ ያሳየናል፡፡

የኢሕአደግ ሥርዓት በጎሳ የተዋቀረ መሆኑ ብቻ ሣይሆን የሚመራበት መርህም "አብዮታዊ ዴሞክራሲ" በመሆኑ የችግራችን መጠንና ጥልቀት እጅግ እየከፋ መጥቷል፡፡ "አብዮትና ዴሞክራሲ" በምን መልኩ ተጣጥመው ነው መንግሥታት "ልማታዊ መንግሥት" ሊባል የሚችለው?

ሌላው አሳሳቢና አስጨናቂ የሆነው ነገር ይህነኑ የጎሳ ሥርዓት ምርኩዝ አድርጎ "ሙስና" ሥር ከመስደዱና ከመንሰራፋቱ የተነሳ አስነዋሪ መሆኑ ቀርቶ ሕግ ወጥቶለት በይፋ ባይነገርለትም ዛሬ ባገራችን ባለሥልጣናት ዘንድ የሚያኮራና የሚያስመካ ሆኗል፡፡ አንድ ባለሥልጣን ለሕሊናው ተገዥ ሆኖ ተገቢ ያልሆነን ሥራ ለማከናወን ፈቃደኛ ካልሆነና ከተቃወመ "እንደምንም አድርጋችሁ ማኖ አታስነኩትም" ይባላል፡፡ እውነትም እንደምንም ተብሎ እሱ በማያውቀው መልኩ ያስነኩታል፡፡ ከዚህ በኋላ አንገቱን ደፍቶ ተሸማቆና ሕሊናውን እየቆጠቆጠው አድርግ ያሉትን እያደረገ ለመኖር ይገደዳል፡ ፡

የኢሕአዴግ ባለ ሥልጣናት ዛሬ እያባነናቸውና እንቅልፍ እየነሳቸው ያለው ጉዳይ የዜጎች መራብና መራቆት ሳይሆን በሙስና ያካበቱትን ሀብት የት ተቀመጠው እንዴትና በምን ሁኔታ ተረጋግተውና ተደላድለው እንደሚበሉት ነው፡፡ ለዚህም ነው የሥልጣን ዘመናቸውን ለማራዘም ሲሉ ሽብር በሌለባት ሀገር የሽብር ሕግ አውጥተው ሽርተኝነትን እንዋጋለን በሚል ሽፋን የተፎካካሪ ፓርቲዎች አባላትንና በነፃው ፕሬስ ጋዜጠኞች ላይ የእስር ዘመቻና የክስ ወከባ አፋፍመው ያሉት፡፡ ለመሆኑ "ሙስና" ምንድነው?

1. ሙስና-ማሰነ፣ለፋ፣ደከመ፣ቆላ ደጋ ወጣ ወረደ ማለት ነው፡፡
2. ሙስና-ምሳና የሚባል ዛፍ አለ፤ቅርፊቱ ተቀጥቅጦ፣ቅጠሉ ተጨምቆ በውሃ ተበጥብጦ ሲጠጣ ኮሶ ያሽራል፡፡
3. ሙስና-ለዛ፣ውበት፣ መልክ፣ቁመና ማለት ነው፡፡ በዚህ ፈቸው በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል በስፋት የታወቃል፡፡
4. ሙስና-የግዕዝ ቃል ሲሆን በአማርኛ "ጥፋት" በማለት ነው፡፡ እንግዲህ ዛሬ "ሙስና" ስንል ከአራቱ ፍችዎች የትኛውን ይዘን ነው? ሙሰኞች ቢጠየቁ ግን ያለጥርጥር በተራ ቁጥር አንድ የተጠቀሰውን እንዴሚሉ ርግጠኞች ነን፡፡ ነገር ግን ለሙሰኞች ትክክለኛውና እውነተኛው ፍቺ በተራ ቁጥር አራት የተጠቀሰው ነው፡፡ በሌላ አባባል "ነቀዝ" ማለት ነው፡፡

እንደሚታወቀው ነቀዝ በልቶ የማይጠረቃ የሰብል ፀር የሆነ ተባይ ነው፡፡ በመሆኑም ነቀዝ ከጤፍ በስተቀር ጠቅላላ የሰብል አይነቶችን ዱቄት የሚያደርግ ነው፡፡ ሙስናም ለዚህ ዘመን ነቀዞች የሚመጥን ፍች ነው፡፡ በተለይም "ጥፋት" የሚለው ፍችው ለሀገር አጥፊዎችና አውዳሚዎች የሚመጥን ቃል ነው፡፡ አሁን ደግሞ "ኪራይ ሰብሳቢ" በሚል ለመተካት ተሞክሯል፡፡ ምናልባት "ጥፋት" የሚለው ፍች ከብዶም ሊሆን ይችላል፡፡ ዙሮ ዙሮ ሙስናም ተባለ ነቀዝ ወይንም ኪራይ ሰብሳቢ ያው ጥፋት ነው፡፡

ሙሰኞች የአገርን ኢኮኖሚ ብቻ በማጥፋት አይወሰኑም፡፡ ጥፋታቸው ሁለገብ ነው፡፡ የአሥተዳደር ሥርዓትን ያቃውሳሉ፤የፍርድ ሂደትን ያዛባሉ፤የዴሞክራሲን ጭላንጭል ያዳፍናሉ፤የሕዝብን አንጡራ ሃብት ይመዘብራሉ፤ሴራን በሕዝቦች መሀከል ያሰራጫሉ፤ የተረጋጋውን ማሕበራዊ ሕይወት ይበጠብጣሉ፤ዛሬ በሀገራችን ዜጎችን መተንፈሻ አሳጥቶ ሰንጎ የያዛቸው ችግር የሙስና ውጤት ነው፡፡

በመሠረቱ ሙስናና ሙሰኞችን በጀርባ አዝሎ ልማት አካሂዳለሁ ማለት የሚታሰብ አይደለም፡ ፡ "በአብዮታዊ ዴሞክራሲ" መርህ እየተመሩ "ልማታዊ መንግሥት ነኝ" ማለትም በሕዝብ ላይ እንደመቀለድ ይቆጠራል፡፡ በበኩላችን እንዲህ ያለውን ማታለል መቆም አለበት እንላለን፡፡ መፍትሄው የሕዝብን ትንፋሽ አዳምጦ፣ራስን አረጋግቶ ለለውጥ ምቹ ሁኔታን መፍጠር ሲቻል ብቻ ነው፡፡

*ጋዜጣችን "ፍኖተ-ነፃነት" ብለናታል፡፡ "ፍኖት" ማለት መንገድ ማለት ሲሆን ከነፃነት ጋር ሲጣመር "የነፃነት መንገድ" ማለት ነው!!*

# ነፃ አስተየት

## ተቋሙ የሚተዳደረው ከህዝብ በሚሰበሰብ ግብር ነው

(ተክሌ በቀለ )

እሁድ ታህሣሥ 29/2004 ዓም፡፡ የልደት በዓልን በማስመልከት የምንወደውን ጓዳችንን አንዷለም አራጌን ለመጠየቅ ወደ ቃሊቲ ማረሚያ ቤት አመራሁ፡፡ ከዚህ በፊት ሁለቴ ሄጄ መግባት አልተፈቀደልኝም፡፡ አንዴ ባለቤቱን፣ ሁለት የሚያምሩ አባታቸውን ባይናቸው የሚያማትሩ ህፃናትንና የባለቤቱን ወላጆች አግኝቼ ተመለስኩ፡፡ መልእክት ብቻ አስተላልፈን እኔና ሌላው ጓዳችን ተመለስን፡፡ ዛሬም ተረኛ ፖሊሶች እንደሚያስገቡኝ ያው የተለመደው የውስጥ ኃላፊ ግን እንደማይፈቅድልኝ አምኛለሁ፡፡ የአንዷለምን ባለቤት ካገኘኋት ለሷና ለልጆችዋ መልካም በአልን ተመኝቼ መልእክት ታደርስልኛለች በማለት በጥዋቱ ደረስኩ፡፡ በግምት 4፡30 አካባቢ ማንም ጋ ቀጠሮ አልነበረኝም፡፡ እቦታው ስደርስ ግን ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳንና የተከበሩ አቶ ግርማ ሰይፉን አገኘኋቸው፡፡ ባለቤቱ ቀድማን በመግባቷ አብረን እንገባለን ፈቃድም እናገኛለን ብየ ተስፋ አድርጌ ነበር፡፡ በቃሊቲ ማረሚያ ቤት የሆነው ሁሉ ግን አሳፋሪ ነበር!

ማረሚያ ቤቱ የራሱ የሆነ ህግና ደንብ እንደሚኖረው አምናለሁ፡፡ ሊኖረውም ይገባል፡፡ በርካታ የህግና (መንግሥት ቢክድም) የፖለቲካ እስረኞች እንዳሉት ስለሚታወቅ ተቋማዊ ህግና ደንብ ሊኖረው ግድ ይላል፡፡ ከማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ ተጽእኖ ነፃ መሆን እንዳለበት ህገ-መንግሥታችን ያዛል፡፡ መሆን አለበት ብየም አምናለሁ፡፡ ተቋሙ የሚተዳደረው ከሕዝብ በሚሰበሰብ ግብር ነው፡፡ እዚያ ያሉት ተቀጣሪ ሠራተኞች ሁሉ የህዝብ አገልጋዮች ናቸው፡፡ ባለማእረጎቹ ሁሉ የህዝብ አገልጋይነት ክብርን ትከሻቸው ላይ እንደሰቀሉ ይሰማኛል፡ ፡ በዚህም መሠረት በርካታዎቹ ፖሊሶች የሚያስተናግዱበት ሁኔታ በጣም ያስደስታል፡፡ አንድ ተረኛ የውስጥ መኮንን ግን በጣም ይለያል፡፡

ልጆች እያለን በደርግ ግዜ ባለማእረግ ፖሊሶች ስማቸውንና ማእረጋቸውን የያዘ ባጅ ያደርጉ ነበር፡፡ በዚህ ቦታ አሁን ስላላየሁ ስሙን ማወቅ አልቻልኩም፡፡ መልኩንና ማንነቱን በደንብ አውቄዋለሁ፡፡ እኛ ወደ ውስጥ ስንገባ ሲቪል የለበሰ ሌላ ሰው ደወለለትና መጣ፡፡ ምን እንዳለው አልሰማሁም፡ ፡ ስለራቀኝ እንጂ ቋንቋውን አውቀዋለሁ፡፡ ከዚያም ነጥሎ ከለከለን፡፡ አካላቱ ሁሉ ጥላቻን ይገልፃሉ፡፡ ደንቡ የሚፈቅድለት ከሆነ መከልከሉ አግባብ ቢሆንም፤ ጥላቻውና ማመናጨቁ ግን ኢትዮጵያዊ ጨዋነት የጎደለው ነበር፡፡ አቶ ግርማ ሰይፉ የፓርላማ ተመራጭ በመሆናቸው ማንንም እስረኛ የመጠየቅና የመጎብኘት መብት እንዳላቸው በመተማመን የፓርላማ መታወቂያቸውን በመስጠት ተከራከሩ፡፡ ከሰዳቢው ደጋሚው እንዲሉ አልደግመውም፡፡ ፀያፍ ስድብ የተሳደበው የህዝብ ጠባቂ ስብእና በጣም ገረመኝ ነገሮች ሲጠሩ፣ ሲረጋጉና ሲሰክኑ የሥራ ዋስትናን (ውድድሩን ስለማይችሉት) እንዲሁም ሌሎች መንግሥታዊ ጥቅማ ጥቅምን የማጣት ስሜትም እንዲህ አይነት ስሜት ይፈጥራል፡፡ በደፈረሰ አካባቢ ብቻ መኖርን የሚመርጡ ግለሰብ ሹመኞችና ባለማእረጎች ይኖራሉ ብዬ አስባለሁ፡፡ ሁኔታዎች የፈጠሩብኝ ጥርጣሬ አለ፡፡ የሆነው ሆኖ እንደነዚህ አይነት ሰዎችን በኃላፊነት ባስቀመጠው ተቋምና መንግሥትም አዘንኩ፡፡

የታመመ፣ የታሰረ፣ የወለደች አራስ፣ ሃዘንተኛ ወዘተ በጋራ በሚጠየቅበትና በሚጎበኝባት አገሬ ይህ አይነት ሁኔታ መፈጠሩ አሳዘነኝ፡፡ ማህበራዊ ትስስራችን ከፍተኛ በሆነበት ኢትዮጵያ የሰዎችን ክብር በሚነካ መልኩ መካልከላችን ከልቤ ተሰማኝ፡ ፡ እኔ ገና መደዴ ነኝ -ለነሱ፡፡ አብረውኝ ያሉት ሁለት ጓዶቼ ግን ከኋላቸው በርካታ ህዝብ አለ፡፡ ከዚህ ቀደም በመስቀል አደባባይ ባደረጉት ንግግርም ጠ/ሚኒስትሩ ይህን ሀቅ አንፀባርቀውት ነበር፡፡

ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳን ለአቅመ አዳም የደረሰ ኢትዮጵያዊ የማያውቅ ያለ አይመስለኝም፡፡ ሰውየው ምን አደረጉ ? ከ40 ዓመት በላይ ለህዝቦች ነፃነት ታገሉ፡፡ 15 ዓመታት አካባቢ አገሪቱን በፕሬዚደንትነትና በከፍተኛ የገዢው ፓርቲ አመራር አባልነት ታምነው ኖሩ፡፡ በግንባሩ እምነት ባጡ ግዜ ያገር ሀብት ሳይመነትፉ ከቤቱ ወጡ፡፡ የተቀመጠላቸውን ገደባዊ ጥቅማ ጥቅም ጥለው ህሊናቸው ባዘዘው ትግል ውስጥ ገቡ፡፡ ለበደሉት

ወደ 15 ዞሯል



ግርማሞገስ
(girmamoges1@gmail.com)

# ሰላማዊ ትግል እና ለምን ብዙዎች ለጥቂቶች ይታዘዛሉ የሚለው ጥንታዊ ጥያቄ!

## (4) ግብረገባዊ ግዴታዎች (Moral Obligation)

በማንኛውም የሰው ልጅ ማህበረሰብ ውስጥ መታዘዝን ትክክል አድርጎ የመቀበል ግብረገባዊ ስሜት አለ። ይህ የታዛዥነት ግዴታ የሚመነጨው ለማህበረሰቡ ደህንነት በማሰብ እና ማህበረሰቡ ለዜጎች ጠቃሚ ተግባሮች ይፈጽማል ከሚል እምነት ነው። ለምሳሌ ከማህበረሰብ ህጎች ውስጥ የተወሰኑት ዝርፊያ፣ ግድያ፣ በጉልበት ሴቶች መድፈርን ከመሳሰሉት ጸረ-ማህበራዊ ባህሪ ተግባራት ዜጎችን ሲጠብቁ ሌሎች ህጎች ደግሞ ማህበረሰቡ የሚያስፈልጉትን ሸቀጦች፣ ግልጋሎቶች እና የመሳሰሉ ጠቃሚ ጉዳዮች እንዲኖሩ ያደርጋሉ የሚል ስሜት አለ። አልፎም በተወሰኑ ዜጎች ዘንድ የተሻለ አማራጭ መሪ ስለሌ ለማህበረሰቡ (ለአገር) ደህንነት ሲባል በስልጣን ላይ ያለው መሪ መጥፎ ቢሆንም ሊደገፍ ይገባል የሚል ስሜት ይኖራል። እንግዲህ በዚህ ረገድ የተቃዋሚ ፓርቲ ስትራተጂያዊ ዘመቻ ግብ የማህበረሰቡ ዜጎች ገዢውን ፓርቲ ከመደገፍ ፈንታ ተቃዋሚን እንዲደግፉ ማድረግ ስለሆነ የተለያዩ ዜጎች ለገዢው ፓርቲ ትብብር የሰጡበትን ምክንያቶች በቅርበት በማጥናት ዜጎች ለገዢው ፓርቲ ታዛዥነትን የለገሱባቸው ምክንያቶች ትክክል እንዳልሆኑ እንዲያውቁ እና አሳባቸውን እንዲቀይሩ ማድረግ ነው።

## (5) አዕምልኳዊ ምክንያቶች (Superhuman Factors)

ካድሬዎች በገዢዎች ላይ አዕምልኳዊ እምነት (cult) እንዲፈጠር ከፍተኛ አጭበርባሪ ፕሮፓጋንዳ በማኪያሄድ እንዲሁም የዳዊት እና የሰለሞን አስተዳደር መንፈሳዊ ትምህርት ገዢዎችን (ነገስታቱን) የእግዚአብሔር እንደራሴ ናቸው ብሎ ስለሚያስተምሩ ህዝብ ታዛዥነቱን ለአምባገነኖች እንዲለግስ ይደረጋል። ገዢዎች ይህን አይነት ታዛዥነት እንዳያገኙ ለማድረግ መድሃኒቱ እውነትን መናገር ብቻ ነው። አንድ ገዢ ግለሰብ ካድሬዎች እንደሚያናፍሱለት በአገር ውስጥ ካሉ ዜጎች ሁሉ የተሻለ አዋቂ ሊሆን እንደማይችል እና በመሪነት ዘመኑ የፈጸማቸውን ስህተቶች በማስረጃ እያስደገፉ መናገር በቂ ነው። እንዲያውም ችሎታው ካድሬዎች እንደሚለፍፉት ሳይሆን ከብዙ ሌሎች ባደባባይ ከማይታወቁ ዜጎች ዝቅ ያለ ሊሆን እንደሚችል ማስታወቅ ያስፈልጋል። እንዲሁም እግዚአብሔርን በምድር ላይ የሚወክል የፖለቲካ መሪ እንደሌለም ህዝብ እንዲያውቅ መደረግ አለበት።

## (6) ሳይኮሎጇዊ ምክንያቶች

በአስተሳሰብ፣ በስነ ልቦና፣ በእምነት፣ በዓላማ፣ በትውልድ አካባቢ፣ በጎሳ፣ በዝምድና ወይንም በሌላ መንገድ ከገዢ አምባገነን መሪ ጋር የሚያመሳስላቸው ምክንያት ያላቸው ሰዎች የማክበር እና የመተባበር ዝንባሌ ሊኖራቸው ይችላል። እነዚህ እራሳቸውን ከገዢው ቡድን ጋር አዛምደው የሚያዩ ወገኖች የገዢውን ቡድን በስልጣን መቆየት ይሻሉ። እነዚህ ወገኖች የገዢውን ቡድን መጠናከር ከራሳቸውም ደህንነት እና ጥቅም ጋር የተሳሰረ አድርገው እንዲያምኑ ሁሉ ይደረጋሉ። ገዢው ፓርቲ እነዚህን ወገኖች የፖለቲካ መሰረቱ (Base) አድርጎ ስለሚወስድ ፍጹም ሊያጣቸው አይፈልግም። ስለዚህ ገዢው ቡድን የእነዚህን ወገኖች ድጋፍ ላለማጣት ሲል ዘወርወር ባለ አነጋገር 'እኔ ከስልጣን ከወረድኩ አለቀላችሁ' እስከማለት ድረስ ውስጥ ውስጡን በሚስጥር በመቀስቀስ ፍርሃትን እንደ ዘዴ እንደሚጠቀም መገመት አያዳግትም። ገዢው ቡድን የነዚህን ወገኖች ታዛዥነት ካጣ ከፍተኛ ችግር ውስጥ የመግባቱ ምልክት ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል።

እንግዲህ ተቃዋሚ ፓርቲ የእነዚህን ወገኖች ድጋፍ ለማግኘት በመጀመሪያ ደረጃ እነዚህ ወገኖች ገዢውን ፓርቲ እንዲደግፉ ያደረጉዋቸው ምክንያቶች ምን እንደሆኑ በዝርዝር ማወቅ እና ምክንያቶቹ ትክክል እንዳልሆኑ ለማሳወቅ ያልተቋረጠ የማስተማር ዘመቻ ማድረግ ይኖርበታል። ገዢው ፓርቲ ይህን ወገን ከቀረው የአገሩ ህዝብ ነጥሎ ለፖለቲካ ስልጣኑ መጠቀሚያ እንዳያደርግ ተጨማሪ ጥረት ማድረግ ያስፈልጋል። ለምሳሌ፥ (ሀ) በሙብት መከበር እና በእድገት መስኮች ከሌሎች የአገራቸው ህዝብ የተለየ ያገኙት ጠቀሜታ እንደሌለ ማሳወቅ፣ (ለ) የኢትዮጵያ ህዝብ የመንግስት ስልጣን ባለቤት መሆን ማለት የእነሱም የመንግስት ስልጣን ባለቤት መሆኑን በማሳወቅ በሰላማዊ ትግሉ እንዲሳተፉ ማድረግ፣ እና (ሐ) ገዢው ቡድን ለዚህ ወገን በገሃድ እና በሚስጥር ውስጥ ውስጡን የሚሰብከውን ሃሰተኛ ፕሮፖጋንዳ እየተከታተሉ ማክሸፍ ያስፈልጋል።

## (7) ገደቦች ያሉት ደንታ ቢስነት (Zone of indifference)

የተወሰኑ ሰዎች ህግን የሚያከብሩበት ምክንያት አለማክበር ሊያስከትል ከሚችለው ችግር ለመገላገል ሲሉ ነው። ህጎች አላፈናፍን ሲላቸው ግን ዜጎች ደንታ ቢስ መሆናቸው ሊያበቃ ይችላል። ለምሳሌ በኢትዮጵያ የታወጀው የሽብር አዋጅ እንዲሁም በሲቪክ ድርጅቶች እና በነፃ ፕሬስም ላይ የተደነገጉት አፋኝ ህጎች ነፃነት ገዳቢ እና ዲሞክራሲያዊ ምህዳር አጥባቢ መሆናቸውን እነዚህ ዜጎች እንዲያውቁ ከተደረጉ በደንታ ቢስነት በማየታቸው ለገዢው ቡድን የለገሱትን ታዛዥነት ሊነፍጉ ይችላሉ። ስለዚህ ተቃዋሚ ኃይሎች አፋቸውን እና ጉልበታቸውን አንድ አድርገው እነዚህ ዜጎች ስለህጎቹ ጎጂነት አውቀው እንዲሻሻሉ ትግል እንዲያደርጉ ማበረታት አለባቸው።

## (8) በራስ እምነት ማጣት (Absence of self-confidence)

በተለያዩ ምክንያቶች የተነሳ የተወሰኑ ሰዎች በራሳቸው ላይ ያላቸው እምነት ዝቅተኛ ወይንም ምንም ነው። እነዚህ ወገኖች ህጎችን አመዛዝነው በግላቸው ውሳኔ ላይ የመድረስ አቅም ያንሳቸዋል። እነዚህ ወገኖች የራሳቸው የሆነ አሳብና እምነት ስለማይኖራቸው የገዢውን አሳብ እና እምነት በጭፍን መቀበል ይቀላቸዋል። ስለሆነም ለመንግስት ታዛዥነታቸውን ይለግሳሉ። ይህ ትብብራቸው ግን የማይለወጥ አይደለም። በዚህ ላይ ትግሉ ሞቅ እና ደራ ሲል ደግሞ አብዛኛውን ህዝብ መከተል ይጀምራሉ።

## መደምደሚያ፥

ብዙው ህዝብ ለምን ለጥቂቶች ይታዘዛል? ለሚለው ጥያቄ አንድ ወጥ፣ የተሟላና ቀላል መልስ የለም። ለምሳሌ ገበሬው እና የፋብሪካ ሰራተኛው ክፍል ታዛዥነትን ለአምባገነኖች የሚለግሱባቸው ምክንያቶች ከፊሉ ሊመሳሰሉ እና የቀረቱ ምክንያቶች ላይመሳሰሉም ይችላሉ። እንዲሁም የአንድ ሰው ምክንያት ከፍ ብለው ከተዘረዘሩት ስምንት ምክንያቶች ውስጥ አንድ ብቻ ሊሆን ይችላል። የሌላው ሰው ምክንያቶች ደግሞ ከአንድ በላይ ሊሆኑ ይችላሉ። እንግዲህ እገሌ ለምን ነፃነቱን አስረክቦ መገዛትን መረጠ ለሚለው ጥያቄ የሚገኘው ምክንያት አይነት እና ቁጥር ከሰው ሰው ሊለያይ ይችላል ማለት ነው። በምርጫ ፖለቲካም ቢሆን ግለሰቦች ገዢ ፓርቲን የሚመርጡበት ምክንያት አንድ አይነት ነው ማለት አይቻልም። የተወሰኑት የሚወራውን የልማት ፕሮፖጋንዳ እምነው ሊሆን ይችላል። የቀሩት የሚረባ ተቃዋሚ የለም በሚል ይሆናል። ሌሎች ደግሞ ቅንጅት በፈጸመው ስህተት ተናደው ተቃዋሚውን ለመቅጣት ብለው ይሆናል። ስለዚህ ተቃዋሚ ፓርቲ የህዝብን ድጋፍ ለማግኘት የእያንዳንዱን የህብረተሰብ ክፍል እና በእያንዳንዱ ህብረተሰብ ክፍል ውስጥ የሚገኙ ግለሰቦችን ምክንያቶች በቅርበት በዝርዝር ማጥናት እና ምክንያቶቻቸው ትክክል እንዳልሆኑ ለማሳወቅ ብሎም አሳባቸውን ለማስቀየር የሚያስችል ቀጣይነት ያለው የማስተማር ስትራተጂያዊ ዘመቻ ማድረግ ያስፈልጋል ማለት ነው።

የሆነው ሆኖ እስከዚህ ድረስ ባደረግነው ጥናት ህዝብ ለአምባገነን ገዢዎች የሚታዘዝባቸውን ስምንት ምክንያቶች አስተውለናል። ለአምባገነኖች አሜን ብሎ መታዘዝ የሰው ልጅ ተፈጥሮአዊ ወይንም ከላይ ከእናት እና ካባት በደም የሚተላለፍ እንዳልሆነ አውቀናል። ታዛዥነት በአብዛኛው የልማዶች፣ የፍርሃት እና የጥቅም ቅይጥ ነው። ልማዶች እና የግል-ጥቅሞች የማይለወጡ ሳይሆኑ የሚለወጡ ናቸው። ለመለወጥ ግን ስትራተጂያዊ ዘመቻዎች ያስፈልጋሉ።

ብዙው ህዝብ ለምን ለጥቂቶች ይታዘዛል? ለሚለው ጥያቄ አንድ ወጥ፣ የተሟላና ቀላል መልስ የለም። ለምሳሌ ገበሬው እና የፋብሪካ ሰራተኛው ክፍል ታዛዥነትን ለአምባገነኖች የሚለግሱባቸው ምክንያቶች ከፊሉ ሊመሳሰሉ እና የቀረቱ ምክንያቶች ላይመሳሰሉም ይችላሉ። እንዲሁም የአንድ ሰው ምክንያት ከፍ ብለው ከተዘረዘሩት ስምንት ምክንያቶች ውስጥ አንድ ብቻ ሊሆን ይችላል። የሌላው ሰው ምክንያቶች ደግሞ ከአንድ በላይ ሊሆኑ ይችላሉ። እንግዲህ እገሌ ለምን ነፃነቱን አስረክቦ መገዛትን መረጠ ለሚለው ጥያቄ የሚገኘው ምክንያት አይነት እና ቁጥር ከሰው ሰው ሊለያይ ይችላል ማለት ነው። በምርጫ ፖለቲካም ቢሆን ግለሰቦች ገዢ ፓርቲን የሚመርጡበት ምክንያት አንድ አይነት ነው ማለት አይቻልም። የተወሰኑት የሚወራውን የልማት ፕሮፖጋንዳ ...

አቶ ወንድወሰን ፀጋዬ አሰለጥ የአንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ /አንድነት/ ሥራ አስፈጻሚና የኢኮኖሚ ጉዳይ ኃላፊ ናቸው፡፡ ስለግላቸው፣ ስለ ፓርቲያቸው፣ ስለወቅቱ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች እንዲሁም ስለ አጠቃላይ አገሪቱ ተጨባጭ ሁኔታ ባልደረባችን ብዙአየሁ ወንድሙ አነጋግሮአቸዋል፡፡



# በፓርቲያችን የፕሮፓጋንዳ ፍረጃ ሲፈፅሙ ጠንካራ ፓርቲ እንዳለን የሚጠቁም ነው !

- መቼና የት ተወለዱ? የት አደጉ? የት ተማሩ?

የተወለድኩት በ1971 ዓ.ም እዚሁ አዲስ አበባ ልዩ ሥፍራው አዲስ ከተማ በሚባል ቦታ ተወለድኩኝ፡፡ ያደኩት ኮልፌ ነው፡፡ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርቴን ከፍተኛ ሰባት በሚባል ት/ቤት ተምሬ አጠናቀኩኝ፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ገብቼ የመጀመሪያ ዲግሪ በኢኮኖሚክስ ተመርቄአለሁ፡፡ ሁለተኛ ዲግሪዬን /ማስተርሴን/ ከአ.አ ዩኒቨርስቲ በኢኮኖሚክስ ፖሊሲ አናሊስስ ተቀብዬአለሁ፡፡

- የሥራ ህይወትዎስ ምን ይመስላል?

የተለያዩ መ/ቤቶች ሠርቼአለሁ፡፡ በመንግስት፣ መንግስተዊ ባልሆኑ ድርጅቶች እንዲሁም በተባበሩት መንግስት ድርጅት በጥናት አጥኚነት እንዲሁ በኢኮኖሚስትነት ሰርቼአለሁ፡፡

- ወደ ፖለቲካው ህይወት መቼ እና እንዴት እንደገቡ ሊገልጹት ይችላሉ?

ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው ኑሮ በራሱ ፖለቲካ ውስጥ ይከትሐል፡፡ በአገራችን በአሁኑ ጊዜ በርካታ ነገሮች አያስደስቱህም፡፡ እነዚህ አስከፊ ነገሮች መቀየር አለባቸው፡፡ እንዲቀየሩ ደግሞ እያንዳንዱ ዜጋ የራሱ የሆነ ግዴታ አለበት፡፡ እኔም የሚጠበቅብኝን ለመወጣት በቀጥታ ከዛሬ አምስት ዓመት ጀምሮ ቀጥተኛ የሆነ የፖለቲካ ተሳትፎ ማድረግ ጀመርኩኝ፡፡ አንድነት ፓርቲ ሲመሰረት ጀምሮ የፓርቲው አባል ሆኜ ስታገል ቆይቼአለሁ፡፡

- አንድነት ከተመሠረተ ጀምሮ አባል ከሆኑ በምን በምን ላይ ተሳትፈው ያውቃሉ?

በጥናትና ምርምር ዘርፍ ውስጥ ነበርኩኝ፡፡ የተሰጠኝን ሥራ ሳከናውን ቆይቼአለሁ፡፡ በህዝብ ግንኙነት ዘርፍ ውስጥም እንዲሁ አገልግዬአለሁ፡፡ የአገራችን የፖለቲካ ሥርዓት እንዲሻሻል የበኩሌን አስተዋፆ ሳደርግ ቆይቻለሁ፡፡

- እስካአሁን ድረስ በከፍተኛ አመራርነት ውስጥ አልነበሩም፡፡ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ አንድነት ፓርቲ በተለያየ መልክ ሲወነጀል፣ ከአመራሩ እስከ አባሉ ሲታሰሩ ይታያል፡፡ አንዳንድ ግለሰቦችም ከፓርቲው ጋር ከታየን በሽብርተኝነት እንፈረጃለን፡፡ ችግር ይገጥመናል፡፡ በሚሉበት ወቅት እርስዎ እንዴት ደፍረው ወደ አመራር ሊመጡ ቻሉ?

ይሄ በአንድነት ላይ እየተፈፀመ ያለው ፕሮፓጋንዳና ፍረጃ ለእኔ ሁለት ነገሮችን ያመላከተኛል፡፡ የመጀመሪያው አንድነት ፓርቲ ትክክለኛው አማራጭ ይዞ ወደ ተቃውሞ የገባ ጠንካራ ፓርቲ በመሆኑ የኢህአዴግ ፍርሐት የፈጠረው ጭንቀት ነው፡፡ ስለዚህ ኢህአዴግ የፓርቲውን እንቅስቃሴ ለመግታት የሚሰራው ነው ብዬ አምናለሁ፡፡ በተዘዋዋሪ ግን ምን ያህል ጠንካራ ፓርቲ እንዳለን የሚጠቁም ነው፡፡ ሁለተኛ የሚያሳየኝ ነጥብ ለበለጠ ትግል ለበለጠ መስዋዕትነት የሚጋብዝህ ነው፡፡ ተራ ፕሮፓጋንዳ እንዲሁም በሰላማዊ መንገድ የሚታገልን ፓርቲ አባላቶችን ማንገላታትና የፓርቲውን ስም የማጥፋት ተግባር ጥንካሬህን ይጨምርልሐል፡፡ ስለዚህ በአንድነት ፓርቲና በአባላቱ ላይ እየተፈፀመ ያለው ግፍና በደል የበለጠ ስለአነሳሳኝ የድርሻዬን ለመወጣት ተዘጋጅቼአለሁ፡፡ እኔን ብቻም አይደለም ይህ ተራ ፕሮፓጋንዳ የአገሪቱን ህዝብና ወጣት ለበለጠ ትግል አነሳስቶታል ብዬ አምናለሁ፡፡

- ኢህአዴግ “ልማት ላይ አተኩሬ እየሰራሁ ነው፡፡ ተቃዋሚዎች የልማት እንቅፋት እየሆኑብኝ ነው፡፡ ለመቃወም ብለው ብቻ ልማትንም ይቃወማሉ” በማለት ይከሳል፡፡ እርስዎ በዚህ ላይ ያልዎት አመለካከት እንዴት ነው?

ልማትን ማንም አይቃወምም፡፡ ፓርቲዬም አበክሮ የሚሠራው ለአገርና ለህዝብ ልማት ነው፡፡ የተሻለ የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚና የማህበራዊ ስርዓትና ልማት እንዲኖር እንሰራለን፤ ሁላችንም ልማት እንፈልጋለን፡፡ ተቃዋሚዎችም ልማትን አንቃወምም፡፡ እኛ የምንቃወመው በልማት ስም የሚፈፀመውን ድህነት ነው፡፡ በልማት ስም የሚፈፀመውን ሙስና ነው፡፡ ኢህአዴግ 20 ዓመት አገር አስተዳድሮ ይህ ነው የሚባል ልማትን ማስመዝገብ አልቻለም፡፡ አሁንም አገሪቱ ድህነት አረንቋ ውስጥ ነው ያለችው ልማት ችግርን አይወልድም፡፡ ልማት ካለ ረሃብ የለም፡፡ ልማት ካለ የዜጐች ኑሮ ይሻሻላል፡፡ ልማት ካለ ሠላም አለ፡፡ የሚታየው ግን ከዚህ የተለየ ነው፤ አሁንም ከድህነት ንቅንቅ አላልንለም፡፡

የሥራ አጥ ቁጥር ከዕለት ዕለት ጨምሯል፡፡ ኢህአዴግ እየሰራ ያለው ልማት ላይ ሳይሆን ሥልጣኑን ለህዝብ ላለመስጠት አበክሮ ይሰራል፡፡ ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶችን ለማፈን ቀንና ለሊት

## ቆይታ

አበክሮ ይሰራል፡፡ የአፈና ተቋማትን ያደራጃል፡፡ ኢህአዴግ በልማት ስም በርካታ አገርንና ህዝብን የሚጐዳ ሥራ ላይ የተሠማራ ድርጅት ነው፡፡ ሐሳቡን ለማጠቃለል፤ ልማትን አንጠላም፤ አንቃወምም፡፡ የምንቃወመው በልማት ስም የኢህአዴግን ኢ-ዴሞክራሲያዊና ኢ-ሰብአዊ ሥራ ነው፡፡ ኢህአዴግ ሥራዬ ብሎ የያዘው የመሰብሰብ መብትን በማፈን ህጋዊና ሠላማዊ ተቃዋሚዎችን በማሸመድመድ፣ የዜጐችን መብት በመግፈፍ የአገሪቱን ሀብት ለጥቂት ግለሰቦች ለማዛወር ይሰራል፡፡ በሩ ለሙስና ክፍት ነው፡፡ በዚህ መካከል ዜጐች በችግር ውስጥ ይገኛሉ፡፡

- ➢ ተቃዋሚዎች አቅም የላቸውም፡፡ አገር ለመምራት አማራጭ ፖሊሲም የላቸውም፡፡ እርስ በእርሳቸውም አይስማሙም፡፡ አገር ለመምራት ዝግጁ አይደሉም ይባላል፡፡ ምን አስተያየት አልዎት?

አንድነት በምንም መስፈርት ከኢህአዴግ የተሻለ እንጂ የሚያንስ ድርጅት አይደለም፡፡ አገራዊና ህዝባዊ አጀንዳ የያዘ፤ አገራዊና ህዝባዊ ራዕይ ያለው፤ ግልጽ የሆነ የአገር ሉዓላዊ አጀንዳ ያለው ነው፡፡ ህዝብ የሥልጣኑ ባለቤት እንዲሆን ይሰራል፡፡ ህጋዊና ሠላማዊ በሆነ ትግል ስልጣን ከኢህአዴግ ወጥቶ ወደ ህዝብ እንዲዛወር ይፈልጋል፡፡ ይህንንም ለማሳካት ብዙ አቅም ያላቸው ግለሰቦችና ምሁራን በአንድነት ውስጥ ተሠባስበው በመስራት ላይ ናቸው፡፡ ከዚህ በተለየ ሁኔታ ደግሞ ኢህአዴግ ሌት ተቀን የተቃዋሚ ፓርቲዎችን በማጥላላት ስም በማጥፋት አባላትን በማስፈራራት አገሪቷ ውስጥ ጤነኛ የፖለቲካ ስርዓት እንዳይኖር ይሰራል፡፡ ተቃዋሚዎች ጠንካራ በመሆናቸው ነው የኢህአዴግን ከፍተኛ ጫናና አፈና ተቋቁመው የሚንቀሳቀሱት፡፡ ኢህአዴግ ተቃዋሚዎችን አሽመድምዶ የህዝብን መብትና ጥቅም ገፎ አገር አስተዳድራለሁ፤ ብሎ ማሰቡን አቁሞ፤ በቅንነት አስቦ፤ ተቃዋሚዎችን በፈጠራ ወንጀል ለመምታትና ለማጥፋት ከማሴር ይልቅ ይህች አገር የጋራችን መሆኑን ተገንዝቦ ከተቃዋሚዎች ጋር ቁጭ ብሎ ቢነጋገር ለአገራችን ይበጃል፡፡ ዛሬ ኢህአዴግ በሚሰራው ሥራ ምሁሩ ደስተኛ አይደለም፡፡ በተቃዋሚዎች አፈና ህዝብ አይደሰትም፡፡ ከአፈና፣ ከሙስና ከወንጀል ተግባር መታቀብ አለበት፡፡ ተራ ፕሮፓጋንዳ የትም አያደርሰውም፡፡

- ➢ ኢህአዴግ ተቃዋሚዎችን ለማሽመድመድ ይሰራል ሲባል በምን ይገለጻል?

ህጋዊና ሠላማዊ ታጋዮችን፣ ጋዜጠኞችን በፈጠራ ወንጀል ያስራል፡፡ የመንግስት ሚዲያዎች ህግ የያዘውን ጉዳይ በማያገባቸው ገብተው የሐሰት ፕሮፓጋንዳ ይነዛሉ፡፡ የሀገር ሀብት ለሐሰት ፕሮፓጋንዳ ይውላል፡፡ ህገ መንግስታዊ መብት የሆነውን የመሰብሰብ የመደራጀት፣ የመናገር፣ የመጻፍ መብት ይጥሳል፡፡ ነፃነቱን ይገፋሉ፡፡ ካድሬውና ደህንነቱ በየዕለቱ የተቃዋሚ ፓርቲ አባላትን በማስፈራራት ሲላቸው በጥቅም ለመደለል ይሞክራል፡፡

- ➢ ወጣት ምሁራን ይፈራሉ፡፡ በአገራቸው ጉዳይ አይሳተፉም ይባላል፡፡ ምን አስተያየት አልዎት?

በእርግጥ ወጣት ምሁራን የሚፈልግባቸውን እያከናወኑ ናቸው ማለት አይቻልም፡፡ ለምሳሌ የኢህአዴግ አጋር ካልሆንክ በስተቀር ህገ መንግስታዊ መብትን በመጠቀም በነፃነት መደራጀት አይቻልም፡፡ ዜጐች በነፃነት እየኖሩ አይደለም፡፡ ኑሮን መቋቋም ተስኖት ይባዝናል፡፡ መ/ቤቶች ያለፍላጐቱና ያለዕምነቱ የኢህአዴግ አባል እንዲሆን ካልሆነ ግን ለመስራትም ለመቀጠርም የሥራ ዕድገት ለማግኘትም ከባድ ያደርጉበታል፡፡ ከአንድነት ፓርቲ ጋር መሥራት የሚፈልጉ በርካታ ወጣት ምሁራን እንዳሉ አውቃለሁ፡፡ ሆኖም ግን ሥጋት አለ፡፡ ሁሉም የመንፈስ ጥንካሬ ፈጥሮ ነፃነቱን በትግሉ እንደሚቀዳጅ አምኖ ተሰባስቦ ለፍትህና ለዴሞክራሲ መታገል አለበት ብዬ አስባለሁ።

- ➢ ተቃዋሚ ውስጥ ሆኖ ከመታገል ይልቅ ኢህአዴግ ውስጥ ሆኖ በመታገል የሥርዓቱን ችግሮች ማስተካከል አይቻልም?

አይቻልም፡፡ ኢህአዴግና አንድነት የዓላማ ልዩነት አላቸው፡፡ ኢህአዴግ ችግሩ የአፈጻጸም ብቻ አይደለም፡፡ የፖሊሲ ችግር አለበት፡፡ ኢህአዴግ ፖሊሲዬ የሚቀየረው በከርሰ መቃብሬ ላይ ነው ብሎ ያምናል፡፡ ኢህአዴግ ስህተቱን ለማየት ፍቃደኛ ያልሆነ ድርጅት ነው፡፡ 20 ዓመት የተዘረጉ ፖሊሲዎች የአገሪቱን ዜጐች ለረሃብና ለእርዛት ዳርገውታል፡፡ ህዝብን ለመስማት አማራጭን ለማድመጥ አይፈልግም፡፡ እኔ የምላችሁን እያጨበጨባችሁ ተቀበሉ፡፡ አድንቁኝ፡፡ አሞጉሱኝ የሚል ድርጅት ነው፡፡ እዚህ ድርጅት ውስጥ ሆነህ የምታመጣው ለውጥ የለም፡፡ በምትኩ በተቃዋሚ ፓርቲ መሳተፍ ማለት በአንድ በኩል አገሪቷ ውስጥ የበሰለና ትክክለኛ የፖለቲካ ስርዓት እንዲኖር እየሠራህ ነው፤ በሌላ በኩል ኢህአዴግ ከሚከተለው ፖሊሲና አሠራር ውጭ አማራጭ ሀሳብ እያስቀመጥክ ነው፡፡ ለዚህ ነው በአማራጭ ፖሊሲ መታገል ያስፈለገው፡፡ ለዚህም ነው በተቃዋሚ ፓርቲ መሳተፍ ማለት ለፍትህ ለነፃነት እና ለዴሞክራሲም የሚደረግ ትግል ነው የምለው፡፡

- ➢ የወቅቱ ዋና ችግር ምንድነው ይላሉ?

የአገሪቱ የፖለቲካ ምህዳር በጣም በጣም ጠቧል፡፡ ጤናማ የፖለቲካ ሥርዓት የለም፡፡ ሰብአዊና ዴሞክራሲዊ መብት ጥሰት በግልጽ ይፈፀማል፡፡ ህጋዊና ሠላማዊ ሆኖ መኖር አይቻልም፡፡ ዜጐች በነጻነት አይኖሩም፡፡ ኢኮኖሚው በማያቋርጥ ግሽበት ውስጥ ነው፡፡ በገጠር የረሃብተኛ ቁጥር ከዕለት ተዕለት ጨምሯል፡፡ ረሃብ በከተማው ውስጥም ተንሰራፍቷል፡፡ የሥራ አጥ በጣም ቁጥሩ እየጨመረ ነው፡፡ ኑሮ ውድነቱ የህዝቡን ማህበራዊ ኑሮ አመሰቃቅሎታል፡፡ ሙስና ተንሰራፍቷል፡፡ ከመኖሪያ እና ከሥራ መፈናቀል ቀጥሎአል፡፡ ወደፊትም ዜጐች ንብረት የማፍራት መብታቸውን እያጡ ነው፡፡ ኢህአዴግ የአገሪቱን መሬት በጠቅላላ የእኔ የግል ሀብቴ ነው ብሎ በድፍረት እየሰራ ነው፡፡ የሚታይ ተስፋ ሰጪ ነገር የለም፡፡ በጥቂት የኢህአዴግ ሰፈር ኑሮና ነፃነት ፌሽታ ነው፡፡ ህዝብ ግን በድህነትና በሥጋት ይኖራል፡፡ የመንግስት መረጃዎች እንደሚያሳየው /የመረጃ አሰባሰብ ችግር እንዳለ ሆኖ/ ኢኮኖሚው በተወሰኑ አካባቢ መሻሻል እንዳለ ያሳያል፡፡ ሆኖም ግን በገጠሩም ሆነ በከተማው ነዋሪ ህይወት ላይ ይህ ነው የሚባል ለውጥ በግልጽ የሚታይ ነው፡፡

ይህ ስርዓት እንዲሻሻልና በአገሪቱም ኢኮኖሚያዊም ማህበራዊ ልማት እንዲመጣ ሁሉም ኢትዮጵያዊ ሁሉ የሚጠበቅበትን ሊያደርግ ይገባል፡፡ መብቱንና ጥቅሙን ለማስከበር የዜግነቱን ክብር ለማስጠበቅ የድርሻውን ሊወጣ ይገባል፡፡

- ➢ በቅርቡ በተደረገው የፓርቲው ብ/ም/ቤት ሰብሰባ እንደፀደቀው እርስዎ የኢኮኖሚ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ ሆነው ተመድበዋል፡፡ ይህ መዋቅር አዲስ ነው፡፡ የዚህ ቋሚ ኮሚቴ ኃላፊነትና ተግባር ምንድነው?

በአገሪቱ ኢኮኖሚ ላይ ጥናት ማካሄድ፣ በኢኮኖሚ ዙሪያ የፓርቲውን አማራጭ ማዘጋጀት፣ በወቅታዊ የአገሪቱ ኢኮኖሚ ላይ የፓርቲውን አቋም ማንጸባረቅ፣ ከፓርቲው ሥራ አስፈጻሚዎች ጋር በመተባበር የምርጫ ማኒፌስቶ ማዘጋጀት፣ ሥልጠናዎችን መስጠት እና የመሳሰሉት ጉዳዮችን የሚመለከት ተግባርና ኃላፊነት አለው፡፡

- ➢ በመጨረሻ ማስተላለፍ የሚፈልጉት ነጥብ



ይኖራል፡፡

ኢህአዴግም እኛም የዚች አንድ አገር ዜጐች ነን፡፡ ማሰብ ያለብን አገርንና ህዝብን ማዕከል አድርገን ነው፡፡ ኢህአዴግ ጥቂት አለአግባብ ተጠቃሚዎችን አሰባስቦ ብዙኃኑን ዜጋ አግልሎ የሚፈጽመውን አግባብ ያልሆነ ሥራ ማቆም አለበት፡፡ አገሪቱ የሁላችንም መሆኗን ማወቅ ይጠበቅበታል፡፡ ስለአገሪቱ የሚያገባው ኢህአዴግን ብቻ አይደለም፡፡ እኛንም ያገባናል፡፡ በአገራችን ጉዳይ እኩል ተቀምጠን የመምከር የመወያየት በጋራ የመወሰን መብት እንዳለን የማወቅ ግዴታ አለበት፡፡ በጠመንጃና በጡንቻ የሚታሰብበት ወቅት አይደለም፡፡ የመጠላለፍ ሥራ መቆም አለበት፡፡ ለዕለት የፖለቲካ ትርፍ ተብሎ ጊዜውን ጠብቆ ሊፈነዳ የሚችል ቂም መትከሉ ለማንም አይበጅም፡፡ ጥሩ የፖለቲካ አስተሳሰቦችን መፍጠር ያስፈልጋል፡፡ ጤናማ የፖለቲካ ስርዓት መዘርጋት ለአገሪቱም ልማት ቁልፍ ሚና ይጫወታል፡፡ የተሻለ የፖለቲካ ስርዓት የሁሉን መብት ያከበረ ይሆናል፡፡ በዚህ ሁኔታ ውስጥ የተቃዋሚ መኖር የሚያስደነግጥና የሚያስበረግግ አይሆንም፡፡ ከዚህ በተለየ የጤናማ ክርክር እና ውይይት ከዛም የተሻለ አማራጮች ማፍለቂያ ይሆናሉ፡፡ ተቃዋሚዎች ለኢህአዴግ ጥሩ አማራጭ ሆነው ሊታዩት ይገባል፡፡ ኢህአዴግ ተቃዋሚዎችን ማቅረብና ማበረታታት አለበት፡፡ የማሽመድመድና የመጉዳት ሥራ መሥራት መቆም አለበት፡፡ ለአገርም ለህዝብም ለኢህአዴግ ለራሱም አይጠቅመውም፡፡ ተቃዋሚዎችም ጥግ ይዞ ወይም ጫፍ ወጥቶ ከመታገል በመቀራረብ ለውጥ ለማምጣት መሥራት አለብን ብዬ አምናለሁ፡፡ ወጣቱ፣ ሴቱ፣ ምሁሩ፣ የዜግነት ኃላፊነቱን ይወጣ፡፡ ነፃነቱን መብቱን ከማንም አይጠብቅ፡፡ ራሱ ያልተሳተፈበት ትግል ውጤት እንደማያመጣ ማወቅ አለበት እላለሁ፡፡

## “አብነት” የግጥም መድብል ተመረቀ

በደራሲ ከተማ ሞሬታ የተዘጋጀው አብነት የተሰኘ የግጥም መድብል በሥራ ሕይወት ላይ ያሉ አብነቶችን የሚያሳይና ዕውቅ ሰዎችን የሚያወድስ ነው፡፡ ደራሲው የኢትዮጵያ ደራሲያን ማህበር አባልናቸው፡፡ ከዚህ በፊት አልበም የተወሰነ ልቦለድ አሣትመው ለአንባቢ አቅርበዋል፤ አብነት የግጥም መድብል ጥር 6 ቀን 2004 በኢትዮጵያ በሔራዊ ቴያትር ሲመረቅ አንጋፋ ደራሲያን፣ ገጣሚያን፣ የባለሀብቶች ጥሪ የተደረገላቸው አርቲስቶች ተገኝተዋል፡፡ በዝግጅቱም ግጥም፣ ወግ፣ መነባነብ የሙዚቃ ስራዎች ቀርበዋል፡፡

## “ዲፕሎማት” ተመረቀ

በመቅዲ ፕሮዳክሽን ኃ/የተ/የግ/ማህበር ፕሮዲውስ የተደረገው በደራሲና ዳይሬክተር ናኦድ ጋሻው የተሰራው “ዲፕሎማት” በዓይነቱ ለየት ያለ ልብ አንጠልጣይ ፊልም ጥር 6 ቀን 2004 ዓ.ም በአዲስ አበባ በ8፡00 በ10፡00 እና 12፡00 ሰዓት ለህዝብ እይታ ያበቃል፡፡

በሁሉም የመንግስት ሲኒማ ቤቶች በግል ተመርቋል፤ በሁሉም በልዩ ፕሮግራም በ8፡00 ሰዓት ታዋቂ ግለሰቦች፣ አርቲስቶች፣ ባለሀብቶች፣ ጋዜጠኞች ጥሪ የተደረገላቸው የኪነ-ጥበብ ቤተሰቦች በተገኙበት በደመቀ ስነ-ስርዓት ሲመረቅ በዚሁ ፊልምና ማህሌት ሹመቴ፣ ሜሮን ጌትነት፣ ታጠቅ ነጋሽ፣ ማህደር አሰፋ፣ አንተነህ አስረስ፣ እንድርያስ አስናቀው፣ ሙክታር ዓሊ፣ ተመስገን ከበደ፣ ኤፍሬም ለማ፣ መሐመድ አህመድ መስከረም ተፈራ፣ ሰለሞን ታፈስ እና ሌሎችም 62 በላይ ተዋናዮች ተውነውበታል፡፡ የፊልሙ ርዝመት 1፡30 ደቂቃ ሲወስድ ፊልሙን ሰርቶ ለማጠናቀቅ 1 ዓመት ከ8 ወር ጊዜ ወስዷል፡፡ የፊልሙ ታሪክ ቅድስት ተመስገን የፀረ አሸባሪ ልዩ ሀይል መሪ በዲፕሎማት ፖስፖርት ወደ ሀገር የገቡትን አደገኛ ቦምብ ይዘው የግብፅ አሸባሪዎችን በቁጥጥር ስር ለማዋል የምታደርገውን ግብግብ በዚህ መሀከል አሸባሪዎቹ ከ20,000 በላይ ኢትዮጵያውያን ከመግደል ባሻገር ያላቸውን ዕቅድ ለማወቅ የሚደረግ ውጣውረድ ያሳያል፡፡

# “በጣም የሚያሳዝነኝ የበቀለ ነመራ ገጠመኝ ነው”

ከብሩክ ከበደ

የቀድሞው ክቡር ዘበኛ በኋላም ማዕከላው ዕዝ ሥር ከነበረው የሙዚቃ ክፍል በሀገራቸው የሙዚቃ ታሪክ ውስጥ ሁነኛ አሻራ አስቀምጠው ያለፉ በርካታ ድምፃውያን፣ የግጥምና ዜማ ደራሲዎች፣ የተለያዩ ሙዚቃ መሣሪያ ተጫዋቾችን በማፍራት ግንባር ቀደሙን ሥፍራ ይዞ ከሚገኙት ሙዚቃ ባንዶች ውስጥ የክቡር ዘበኛ ባንድ አንዱ ነው፡፡

ይህው የሙዚቃ ክፍል ካፈራቸው በርካታ ድምፃውያን መካከል ጌታቸው ተካ አንዱ ነው፡፡ ጌታቸው ይጫወትበት የነበረው ክፍል ከደርግ ውድቀት ማግስት ቢፈርስም አሁንም አንዳንድ ሠርግ ቦታዎች እየተገኘ ስሜቱን ለመወጣት ያገደው የለም፡፡ ጌች ራሱንና ቤተሰቡን በአሁን ሰዓት የሚያስተዳድረው በጥበቃ በሚያገኘው ገንዘብ ቢሆንም ይህቺ አንዳንዴ ብቅ ጥልቅ የምትለው ሙያውም መጠነኛ ድጎማ ታደርግለታለች፡፡ ለመሆኑ ጌታቸው ተካ ማነው? ለሚልም መልሱን ከንባብ ቆይታው የሚያገኙት ይሆናል፡፡



➢ ወደ ሙዚቃው አለም የገባህው መቼ ነው?

ልጅ እያለሁ ነው፡፡ ምናልባት 14 ዓመት ቢሆነኝ ነው፡፡

➢ ዘመኑ መቼ ነው?

1960-1961 ዓ.ም ውስጥ ነው፡፡

➢ ለመግባት መነሻ የሆነህ ምክንያት ምንድ ነው?

ቀበና ኮከበ ጽባህ የሚባል ት/ቤት እማር ነበር፡፡ አሳዳሪዎቼ በገቢ ደካማ ስለነበሩ ለደብተር እርሣስና ስክሪብቶ መግዣ የሚሆነኝን ሣንቲም የማገኘው የሠፈሩን ከብት ወደ ዱር ወስጄ በማገድ ነበር፡፡

➢ አሳዳጊዎቼ ስትል?

ወላጆቼ ተጣልተው በመለያየታቸው የምኖረው ከአያቶቼ ጋር ስለነበር ነው፡፡ የእረኝነቱንም ሥራ እየሰራሁ እንዳለ ዘወትር ቅዳሜ ጃንሜዳ ከሚገኘው መድፈኛ ክፍል ጀርባ የክቡር ዘበኛ የሙዚቃና ቲያትር ክፍል ለቤተሰባቸው ሙዚቃ ያቀርባሉ፡፡ ከድምፃውያኖቹ መሀል ጥላሁን ገሠሠን በጣም ነበር የምወደው፡፡ በተለይ አንዲት ሙዚቃ አለችው፡፡ እሷን ሲዘፍን ነፍሴ ነው የሚጠፋው፡፡

➢ ምን የምትለው ዘፈኑ ነች

ጽድቅና ኩነኔ ፍቺው አልገባኝም
የኔ ነፍስ አንቺ ነሽ ትርፍ ህይወት የለኝም
የዓላማዬ ግብ ነሽ የኑሮዬ ቁልፍ
ነይና አስደስቺኝ ከዓለም ላይ ሳላልፍ
ልቤን ገልፀሽ እይው
የግልሽ ነው ተስፋ ስጪው፡፡

እያለ የሚዘፍናት ይህቺን ሙዚቃ እንደሰማሁ ከብቶቹን ትቼ በቀጥታ መድፈኛ ግቢ ገብቼ ሙዚቃዋቹን ስከታተል ቆይቼ ማምሻውን ወደ ከብቶቹ ስመለስ ግማሾቹ ተበታትነው በየጫካው ገብተዋል፡፡ ቤታቸውን የሚያውቁት ወደ ቤታቸው ሄደዋል፡፡ ከብቶቻቸው ያልገቡላቸው ባለንብረቶችም ቀጥታ ወደቤት በመምጣት ከብቶቹን መጠየቅ ያዙ፡፡ እኔማ ስፈልግ አምሽቼ ወደ ቤቴ ገባሁ፡፡ አያቶቼም ተቆጡኝ፡፡ በማግስቱም ማለዳ ተነስቼ ወደ ጫካው ብገባ ከብቶቹ በጅብ ተበልተዋል፡፡ በዚህን ጊዜ ዋናው እረኛ ባገኘኝ ቁጥርም እየመታን ስላስቸገረኝና በአጋጣሚም ሁለቱም አያቶቼ ተከታትለው በመሞታቸው ሠፈሩን ለቅቄ ወደ ፈረንሣይ ለጋሲዮን ገባሁ፡፡ እዛም እንደገባሁ ከገዛህኝ ደስታ ጋር ተገናኘን፡፡

➢ ገዛኸኝ ደስታ ማለት የመድረክ መሪው ፺/ አለቃው ነው?

አዎን፡፡ እሳቸውን እግዚሐብሄር አገናኘን፡፡ እኔ ዘንድ ተቀምጠህ መማር ትችላለህ ሲሉም አበረታቱኝ ፺ / አለቃ የሙሉ ወንጌል እምነት ተከታይ ነበሩ፡፡ እሣቸው ጋም ተቀምጬ ትምህርቴን መከታተል ያዝኩ፡፡ ማታ ማታም ጨፌ ጠጅ ቤት እነ ጥላሁን ገሠሠ፣ እሣቱ ተሰማ፣ ተዘራ ኃ/ሚካኤል፣ ተፈራ ካሣ ስለሚመጡ የማደንቃቸውን ድምፃውያን በቀርበት ለመመልከትና ለማድነቅ በቃሁኝ፡፡ በተለይ ጥላሁን ፊት ተቀምጬ አወራሩን አጠጣጡን ሣይ በእጅጉ ነበር የምደሰተው፡፡

➢ ጥላሁን ይዘፍን ነበር?

በፍጹም አይዘፍንም፡፡ እነሱ ልክ እንደወጡ እኛ እዛ የተሰበሰብነው የምግብ ማቅረቢያ ትሪውን እንደድራም እየተጠቀምን እንዘፍናለን እንጫወታለን፡፡ በዚህ መሀል ነው እንግዲህ ፲/አለቃ እስጢፋኖስ ካሣ የሚዚቃው ስሜት ካለህ ለምን አላስቀጥርህም ሲል ጥያቄ አቀረበልኝ፡፡ እሺታዬንም ገለፀኩለት፡፡

➢ ፲ /አለቃው ሙዚቀኛ ነበር?

የክቡር ዘበኛ የሁለተኛው ኦኬስትራ ከበሮ መቺ ነበር፡፡ እሺ ማለቴንም ካረጋገጠ በኋላ ይዞኝ ወደ ክፍሉ ወሰደኝ፡፡ እግዚአብሄርም ተጨምሮበት የህክምና ምርመራ እንድወስድ ተደረገ፡፡ አለፍኩኝ፡፡

➢ ወደ ሙዚቃው ሙያ ከገባህ በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ የተጫወትከውን ሙዚቃ ታስታውሰዋለህ?

በወቅቱ ማሕሙድ አህመድ ክፍሉን ለቆ የወጣበት ጊዜ ነበርና ዲያፍሪክ ሆቴል በተዘጋጀ ሠርግ ላይ ማይክ ጨበጥኩ፡፡

➢ ምንም ልምምድ ሣታደርግ ነው ማይክ የጨበጥከው? የዘፈንከውስ የራስህ የሆነ ዘፈን ነው ወይስ. . . ?

“የሺ ሀረጊቱ የክቲቱ የኔ ዘረ ብዙ” የሚለውን የመሐሙድን ዘፈን ነበር፡፡ ወዲያው ጌቾ በርታ!! በማሕሙድ ቦታ የተተካውን ልጅ ጥሩ ድምፅ አለው፡፡ የሚሉና የመሳሰሉ አበረታች ምላሾችን ሳገኝ የልብ ልብ ተሰማኝ፡፡ እኔም ተኮፈስኩ . . .(ሳቅ)፡፡ ክፍሉ ለሙዚቀኛው የእንግሊዝ ሱፍ ነው የሚያስፋው፡፡ እኔ ግን አዲስ ስለሆንኩ ነው መሠል ሪጋ (መሥመር) ያለው ብልጭልጭ ልብስ እንድለብስ ተደረገ፡፡ ልብሱን የለበስኩ ቀን ደስታዬ ወሰን አልነበረውም፡፡ እነዚያ ጠጅ ቤት የማደንቃቸው ታዋቂ ድምፃዊን ጓደኛ በመሆኔ ተደሰትኩ፡፡ ኮት ትከሻ ላይ ተሰቀለ ተወኝ!!

➢ ጌቾ ምን ያህል ሥራዎች ተጫውተሀል?

በውል ይሄን ያህል ነው ብዬ ላስቀምጥልህ ያዳግተኛል፡

## የአደባባይ ምስጢሮች

### የቁጩ ፍ/ቤት

ከአንድ ሃያ ዓመታት በፊት ቁጭ በሉ የሚባል የማታለልና የመዝረፊያ ዘዴ ነበር። የመንገደኛውን ፍላጐት ከተረዱ በኃላ እኔ እጨርስልዎታለሁ፤ እኔ አመጣልዎታለሁ፤ ይህንን ጉዳይ የማውቀው እኔ ብቻ ነኝ፤ ወዘተ በማለት ባለጉዳዩን እዚህ ቁጭ ብለው ይጠብቁኝ ብሎ ባለ ጉዳዩ የያዙትን ገንዘብና ንብረት ይዞ የመሰወር ሌብነት ነበር። በዚህ ዓይነትና በሚመሳሰል ሁኔታ ሰዎችን የሚያታልሉ ሁሉ “ቁጭ በሉ ቁጩ” እየተባሉ ሲጠሩ መስማት የተለመደ ነው። በአንዳንድ ሰፈር በየለቅሶ ቤቱ የሚቋቋሙ የእንብላው ፍ/ቤቶችም የቁጩ ፍ/ቤቶች ይላቸዋል። የቁጩ ፍ/ቤቶች ሥልጣንና ኃላፊነታቸው በየለቅሶ ቤቱ ገንዘብ ማሰባሰብና ለተለያየ ወጪ መጠቀም ነው። ለቡና መግዣ፣ ለጫት መግዣ ለመሳሰሉት የሚውል ነው። በአንድ ወቅት በአንድ ሐዘን ቤት/ለቅሶ ቤት/ የገጠመኝን ላካፍላችሁ።

ለቅሶ ቤቱ ገብቼ አንድ 15 ደቂቃ እንደተቀመጥኩኝ አንድ ቤቱን ታደምቅ ከነበሩት ሴቶች ውስጥ ተነስታ ዝም በሉ አለች። አድምጡ ቤቱ ሥርዓት አጥቷል።ደንብና ህግ ሲጣስ ዝም ብለን ማየት የለብንም። አጥፊዎች በህግ ሊጠየቁ ይገባል። ማንም ከህግ በላይ አይደለም፡፡ እዚህ ቤት በተደጋጋሚ ከፍተኛ ወንጀል እየተፈፀመ ነው። ስለዚህ ፍ/ቤት ይቋቋም። ፖሊስም ይመረጥ፤ ዳኛም ይሾም አለች። በሀዘኑ ቤት ከነበሩት አብዛኛው ትክክል ነው። ብለው አጨበጨቡ። እኔ ግን አልገባኝም፡፡ ሴትየዋ ተነስታ መናገር ስትጀምር አንድ ሴትና አንድ ወንድ ተጠቃቅሰው ለቅሶኛውን ሳይሰናበቱ በፍጥነት ቤቱን ለቀው መውጣታቸውን አስታውሳለሁ። በፍ/ቤቱ መቋቋምና በፖሊስ መመረጡም ስምምነት ላይ ተደረሰ፡፡ በሉ በቅድሚያ ፖሊስ ምረጡ አለች። በርካታ እጆች ወጡ። ሁሉም እኔ እኔ እያሉ ይጮሐሉ። እሺ አንተ አለቺው በራሷ ሥልጣን ሰብሳቢ የሆነቺው ሴትየ።

ብድግ አለና ፖሊስ መሆን ያለብኝ እኔ ነኝ። በማለት ራሱን ጠቆመ። የተወሰነ ሲስቅ ብዙዎቹ ተቃወሙት። አንዷ ተነሳችና ግብዳው ይሻላል። ፖሊስ መሆን ያለበት ግብዳው ነው አለች። አብዛኛው ሰው አጨበጨበ። ግብዳው ደረቱን ገልብጦ ብድግ አለ። እጁን ጨብጦ ደረቱን መታ መታ እያደረገ ተንጐማለለ። ውፍረቱ ረዝመቱ የገደል ቅራፊ ያክላል። በግብዳው ፖሊስነት ስምምነት ላይ ተደረሰ። ከአሁን ሰዓት ጀምሮ እያንዳንድሽ ሥነ ሥርዓት ትይዢያለሽ። እንቢ ካልሽ ዋ አለና በእጁ ወደ አንድ ጥግ አሳየ። እስር ቤት መሆኑ ነው። ሂደቱ ወደ ዳኛ መምረጥ ተኬደ። አሁን ዳኛ ምረጡ ተባለና ሦስት ሰው ተመረጠ። ሦስቱ ዳኞች ቦታቸውን ያዙ። የግራ ዳኛው የፍ/ቤቱን ሥልጣንና ተግባር አሳወቀ። ፍ/ቤቱ ይግባኝ የሌለው ነው። የችሎቱ ስም እንብላው ፍ/ቤት ይባላል። የተከሰሰ ሰው ቅጣት ሲወሰንበት የተወሰነውን ቅጣት መክፈል እንጂ አልከፍልም። አላጠፋሁም ማለት አይቻልም። አሉ። መድረኩን ስትመራ የነበረቺው ያለ ጥቆማ ያለ ምርጫ ራሷን ዐቃቢ ህግ አድርጋ ሾመች።

ዐቃቢ ህግ የመጀመሪያውን ክስ በአንዱ ታዳሚ ላይ ከፈተች። በትላንትናው እለት ከምሽቱ አንድ ሰዓት ላይ ወደ ቤቴ ስሄድ ይህ ሰውዬ ልብሴን ይዞ ጐትቶብኛል። ምን ፈልገህ ነው? ስለው ወደ እኔ ቤት እንሂድ ብሎ ሊያስገድደኝ ሞክሯል። ይቀጣልኝ አለች። ተከሳሽ እኔ ትላንት አዲስ አበባ አልነበርኩም። የመጣሁት ዛሬ ነው። በማለት መልስ ሰጠ። ሳትይዛት እንዲህ ብላ አትከስም አጥፍተሃል። 10 ብር ተቀጥተሀል። በማለት ተፈረደበት። ከተከራከርክ ይጨመርብሐል አሉት፡፡ የተወሰነበትን በፍጥነት ካልከፈለ ቅጣቱ ይጨምራል ስለተባለ ከፍሎ ቁጭ አለ። በሦስተኛ ደረጃ እኔ ተከሰስኩ፡፡ እዚህ ሐዘን ቤት መጥቶ እግሩን አደራርቦ ተቀምጧል። ከቅድም ጀምሮ በአይኑ ይጠቅሰኛል። ስለዚህ ይቀጣልኝ፤ በማለት ከሰሰቺኝ። ተነስና መልስ ስጥ አለና ግብዳው ከተቀመጥኩበት በአንድ እጁ አንጠልጥሎ አነሳኝ፡፡ መብቴ መደፈሩን ብረዳም ቤቱን ለመመሳሰል ስል እግሬን አነባብሬ መቀመጥ ለምዶብኝ ነው። ማንንም ለመድፈር ፈልጌ አይደለም። በአይኑ ጠቀሰኝ ያለቺው ሐሰት ነው አልኩኝ። እሷማ ከሜዳ ተነስታ አትልህም። እንዲሁም ሲያዩህ እንደምታደርግ ታስታውቃለህ። 20 ብር ተቀተሐል በማለት ፈረዱብኝ። ቅጣቴን ከፈልኩኝ። ሴትየዋ ገና ተነስታ ዝም በሉ ስትል ለካስ እነዚያ ወንድና ሴት ለቅሶ ቤቱን ጥለው በፍጥነት የወጡት ግብዳው ፖሊስ ሳይመረጥ የእንብላው የቁጩ ፍ/ቤት ሳይቋቋም ለማምለጥ ነው። እኔ መቼ ገባኝ? እያሉ እያሉ ገንዘብ ሲሰበስቡ በማየቴ ገረመኝ። ይኸ የቁጩ ፍ/ቤት 20 ብር ቀማኝ አልኩኝ። ከጐኔ ለተቀመጠው። ኸረ እንዳይሰሙህ ችሎት መድፈር ብለው መቶ ብር እንዳያከናንብህ አለኝ፡፡ ከቁጩ ዘመን ከቁጩ ፍ/ቤት ይጠብቃችሁ።

# እግር ኳሳችን ያላያቸው . . .



ውብሸት ተሾመ
Stgtb7@yahoo.com

ሀገራችን ኢትዮጵያ እንደ ታሪክ ከምታወራቸው ታላቅ ነበርን፤መሥራች ነበርን፤እያልን ስለያኔው እያወራን እለት እልት በጣም ከውጤት እየራቅን ካለንባቸው ነገሮች መካከል አንዱ የሀገራችን የእግር ኳስ ጉዳይ ነው::

ቀደም ብለው የነበሩ የእግር ኳሱ አመራር አካላት ስለኳስ ባወሩ ቁጥር "ያኔ የነበረንን ውጤት ዳግም ለማምጣት ጠንክረን እንሠራለን" ይሉ ነበር:: አሁንም የተሾሙት በዚህ ጉዳይ ሲናገሩ "መሥራች እንደ መሆናችን በላቀ የተነሳሽነት መንፈስ ወደ ቀድሞ ብቃታችን ለመመለስ ከምን ግዜውም በላይ መሥራት አለብን" ይላሉ::

ሁለቱም ዛቻና ተሰፋ የተቀላቀለበት ንግግር ይናገራሉ:: የመጣ ውጤት ግን የለም:: ወደ መፍትሔ ለመሄድ ወሳኙ ነገር የሚያማምሩ አማርኛዎችን በየሚዲያው መናገር ሳይሆን መፍትሔው ያልታዩትን ማየት፣ስህተቶችን ማረም ለመፍትሔው አብዝቶ መሥራት ነው:: እኔ በዚህ ጽሑፍ ስለ ሀገራችን እግር ኳስ መፍትሔ ለመናገር ፈልጌ አይደለም፤ሌላ ጊዜ በሰፊው እመለስበት ይሆናል:: ዛሬ በዚህ ርዕስ ሥር ከምንወደው እግር ኳስ ጀርባ ያሉ የጀርባ አጥንቶች ለእግር ኳሱ መኖር፣ለውጤቱ፣ለገቢው ወሳኝ ስለሆኑ ሰዎች ጥቂት ልል ፈልጌ ነው:: የእግር ኳሱ አመራሮች ያላያቸው ወሳኞች ናቸውና:: የእግር ኳሱ የጀርባ አጥንት ደጋፊው ተመልካቹ ነው:: ደጋፊው ገብቶ በሚደግፍበት ወቅት ከገቢ ምንጭነቱ በተጨማሪ ተጫዋቾቹ በሚሰጣቸው ሞራል ለተሻለ ብቃት ይነሱ ዘንድ ወሳኝ ሚና አለው:: ወደ አዲስ አበባ ስቴድየም የኢትዮጵያ ቡናን ጨዋታ ለመመልከት የገባ ተመልካች ይህንን በደንብ ያስተውላል::

በአዲስ አበባ ስቴድየም ሚስማር ተራ ተብሎ የሚጠራው ቦታ በቡናው አስጨፋሪ በአዳነ እየተመራ መላውን እስቴድየም እንደሚያናጋው ያየ ያውቀዋል:: በ2003 ዓ.ም የኢትዮጵያ ፕሪምሪየር ሊግ የኢትዮጵያ ቡና ለመጀመሪያ ጊዜ የሊጉን ዋንጫ ሲያነሳ ለውጤት ካበቁት ነገሮች መካከል አንደኛውና ወሳኙ ተብሎ የተጠቀሰው "የደጋፊው ከወትሮው ለየት ባለ መልኩ መነሳሳት" ተብሎ ተገልጿል:: ወሳኙ ነገር ይህ ነው:: አንድ ክለብ ወይም ብሔራዊ ቡድን ደጋፊውን አክብሮ ማጫወት ከቻለ ውጤታማነቱ የሚታይ ይሆናል:: በቅዱስ ጊዮርጊስ እሰፖርት ክለቦች ውስጥ የምናያቸው ታላላቅ ተጫዎቾች በደጋፊዎቻቸው "እደግ ተመንደግ" በርታ" ተብለው የመጡ ናቸው::

ስለእነ አቼኖ፣አዳነ፣ደረጀ በብዙ ሚዲያዎች ትንሽም ቢሆን ተብሏል:: እኔ በዚህ ጽሑፍ ከአዲስ አበባ ወደ ደቡብ የሀገራችን ክፍል ወደ ሀላባ ልዩ ወረዳ ወስጃችሁ ከከነማው ደጋፊ ከረጅሙ ተስፋዬ አደም ጋር ላስተዋውቃችሁ ነው:: ለዚህ ጽሑፍ ስኬት የረዱኝን ሁሉ አመሰግናለሁ::

2003 ዓ.ም ሻሸመኔ የመጨረሻ ወሳኝ ጨዋታ በዚህ ጨዋታ የአላባ ከነማ ካሸነፈ ወደ ፕሪሚየር ሊግ ማለፉን ያረጋግጣል:: በሻሸመኔው ሁለገብ ስቴድየም አንድ ረጅም ድካም የማይታየበት ወጣት ለጉሮሮው ሳይሰስት ያስጨፍራል:: ዘጠና ደቂቃውን በሙሉ ይጮህል፤ ሰዓት አለቀ ያለምንም ጐል የዚህን የተስፋዬ አደምን እልህ ንዴት ማንም ሊያበረደው አልቻለም፤ መሬት ላይ ወድቆ ተንከባለለ- - - - - - - - - - - - - ::

ከአዲስ አበባ ሻሸመኔ ሄደው የነበሩ ሰዎች በአጋጣሚ ጨዋታውን ለማየት ያለው አጨፋፈር ውስጣችንን ገዛው ብለው አዲስ አበባ ስቴድየም ውስጥ ሲያወሩ አጠገባቸው ሆኜ ሰምቼ ነው ይህንን ጽሑፍ ለማዘጋጀት የተገደድኩት:: አንደኛው እንደዲህ አለ "እንደ ተጫዎች ደጋፊን ማስፈረም ቢቻል ኖሮ ተስፋዬ አደምን አስፈርሞ ወደ አዲስ አበባ ማምጣት ይቻል ነበር:: ብለዋል::

እኔም ከእነሱ ይህችን መረጃ ይዤ የተለያዩ መረጃዎችን መፈለግ ጀመርኩ:: እነሆ የዚህ ወጣት የስፖርት ፍቅር ብቻ ሳይሆን ጨዋነት በጣም አስደሳች ነው:: ደጋፊ በጣም ወሳኝ መሆኑን ከእንግሊዙ ፕሪምየር ሊግ አሳልጣኝ ከማንችስተር ዩናይትዱ ሰር አሌክስ ፈርጉሰን ንግግር ብዙ መረዳት እንችላለን:: በ2010/11 የአውሮፓ ሻምፒዮንስ ሊግ ጨዋታ ከቼልሲ ጋር በተገናኙበት ወቅት አጣብቂኝ በሆነው የጐል ውጤት ውስጥ ገብተው ደጋፊዎች አብዝተው ረድተዋቸው ለድል ከበቁ በኋላ አሰልጣኙ ሲናገሩ "ደጋፊዎቻችንን በፈለግናቸው ሰዓት በጨነቀን ሰዓት አገኘናቸው" ነበር ያሉት፤ይሄ ወሳኝ ነገር ነው::

ሲረግጡት እምቦጭ የሆነው የሀገራችን እግር ኳስ ትልቁ ችግሩ ደጋፊውን ስለማይሰማ ነው:: ባደጉት ሀገራት በእግር ኳሱ ማለቴ ነው:: እንደ ዘሪፍ፣ፋኑ ፋኑ፣የሚጠቀሙት ንግግር "በደጋፊ ፊት መሸነፍ ነውር ነው" አክብረው አስከብረው ስለሚጫወቱ ነው:: የፌዴሬሽን አካላት፣የስፖርት ሰዎች፣አሰልጣኞች፣ተጫዎቾች ደጋፊን ሊሰሙ ሊያከብሩ ሊያስከብሩ ይገባል::

እንደ ተስፋዬ አደም ያሉ ደጋፊዎች ፌዴሬሽኑ ለከነማው ከሚልከው ትጥቅና ድጎማ የሚብስ ድጋፍ ለከነማው ይሰጣሉ:: ዛሬ ተስፋዬ ግጥም እየገጠመ በርታ እደግ ያለው ተጫዎች ነገ የሀገሪቱ ብሔራዊ ቡድን ተጫዋች ሲሆን የተስፋዬ ዋጋ ቀላል ነው? የህንን ነው እኛ ማሰብ የተሳነን፤ከተለያዩ ክፍለ ሀገሮች መጥተው በብሔራዊ ቡድን ደረጃ የሚጫወቱ ተጫዋቾች ትናንት ክፍለ ሀገር እያሉ እንደ ተስፋዬ አደም አይነቱ የስፖርት ወዳድ በርታ ባይላቸው መች እዚህ ይደርሱ ነበር:: አዳነ ሳይኖር ሚስማርን አስቡት፣ኦቼኖ ሳይኖር ካታንጋን አስቡት፣ተስፋዬ አደም ሳይኖር የአላባውን ሁለገብ እስቴድየም አስቡት:: ሜዳ ውስጥ ተጫዋቾች ከሚያሳዩት እንቅስቃሴ በተጨማሪ የደጋፊዎች ዝማሬ ምን ያህል የድል መንፈስ እንዳለው ስፖርቱን ቀረብ ብሎ የሚያይ ያውቀዋል::

የዓለማችን ታላላቅ ብሔራዊ ቡድኖች በሜዳቸውም ሆነ ያለሜዳቸው ያልተጠበቀ ሽንፈት ሲገጥማቸው ሁል ጊዜ የሚሉት "ደጋፊዎቻችንን ይቅርታ እንጠይቃለን፤ተሳስተናል እንክሳለን" ይህንን ነው ምን ጊዜም የሚሉት፤ፌዴሬሽኑን፣መንግሥትን አይደለም:: ይቅርታ የሚሉት የኳሱን የጀርባ አጥንት የሁሉም ስብስብ የሆነውን ደጋፊውን ነው:: የደጋፊ ዋጋው ምን ያህል እንደሆነ ማየት ተገቢ ነው::

አሰልጣኞች ከተጫዋች ዝውውር ወሬ፣ከደሞዝ ጭማሪ፣ከተጫዎች ቅጣት ከዋንጫ ክብር በፊት ደጋፊውን ሊያውቁ፣ሊያሳውቁ ሊያከብሩና ሊያስከብሩ ይገባል:: ፌዴሬሽኑም ብዙ መፍትሔዎችን፣ጥቅሞችን፣ደካማጎኖችን አንጥሮ አይቶ መፍትሔ ለማምጣት ከወገቡ ዝቅ ብሎ ሁለቱንም አይኖቹን ጆሮዎቹን ወደ ደጋፊዎች ሊያዞር የገባል:: ምክንያቱም እዛጋ ብዙ ዓይን አለ::

ከአዲስ አበባ 315 ኪ.ሜ ርቀት ላይ ከመትገኘው የሀላባ ከተማ ነገ ለሐገራችን እግር ኳስ መፍትሔ የሚኑ ልጆች ሊወጡ ይችላሉ:: እነዚህ ልጆች በቂ የሆነ ክፍያ፣የላብ መተኪያ እንደሚያገኙ ግለፅ ነው:: ታዲያ ለእኚህ ልጆች ደሞዛቸው፣የላብ መተኪያቸው እንደ ተስፋዬ አደም ያሉ ቅን የስፖርት ደጋፊዎች ናቸው::

ስለ ተስፋዬ መረጃ የሰጠኝ አንድ ወጣት "ሀላባ ሆነህ የብሔራዊ ቡድን ጨዋታ ስታይ ተስፋዬ ደጋፊ አዲስ አበባ እስቴድየም ያለህ ነው የሚመስልህ፤ደግሞ ደጋፊ ብቻ አይደለም ጨዋነትም ጭምር እንጂ" ብሎኛል:: ለእንደዚህ ያሉ ደጋፊ እነ እንግሊዝ፣ስፔን ከፍለው ነው ይዘዋቸው ጨዋታ ባለበት ሁሉ የሚሄዱት እኛ ባንከፍላቸውም እንኳን ዋጋቸው ከባድ ነውና እናክብራቸው፤እናበረታታቸው:: ተመልካች የቡናውን የአዳነን ዋጋ ያውቃል:: ለዚህም ገና አዲስ አበባ እስቴድየም ሲገባ "አዳነ ለቡና ይሰራል ገና" እያለ የቀበለዋል:: የኔ ጥያቄ የቡና ስፖርት ማሕበርስ የአዳነን ዋጋ ያውቀዋል?

ተመልካቹ የአቼሃን ዋጋ ያውቃል፤ለዚህም ገና ካታንጋ ሲገባ ብድግ ብለው ይቀበሉታል:: የኔ ጥያቄ የቅ/ጊዮርጊስ ስፖርት ማሕበር የአቾኖን ዋጋ ያውቀዋል? ተመልካቹ ብቻ ሳይሆን አይደለም የሀላባ ሰው በዝና አዲስ አበባባም ያለ ሰው የረጅሙን የማይደክመውን የሀላባ ከነማ አስጨፋሪ የተስፋዬ አደምን ዋጋ ያውቃል:: የኔ ጥያቄ ስኬታማው የከነማው አሰልጣኝ ሚሊዮንም ሆነ የሀላባ ከነማ ስፖርት ማሕበር የተስፋዬን ዋጋ ያውቃሉ ወይ?

ሁሉም ይህንን ጥያቄ በተረጋጋና በሰከነ መንፈስ ሊመልሰው ይገባል ይህን ጠያቄ በተረጋጋ መንፈስ የመለሰ አካል ለውጤት ለስኬት ቅርብ መሆኑን ሊረዳ ይገባል:: የእነ ተስፋዬ አደምን፣አዳነን፣አቼኖን - - - ዋጋ በገንዘብ ልንተመነው አንደፍርም ምክንያቱም ዋጋቸው ውድ ነው:: አንድ ክለብ ውጤት እምቢ ሲለው ጎል አልገባ ሲለው ተጫዎቾች ወደ ደጋፊዎች ዞረው ሊያነሳሱ እናያለን ለምን - - - ?

የጋራ የማይቻልን ነገር እንዲቻል ያደርጋልና፤አንባብያን በሌላ ጊዜ በዚሁ ማስታወሻዬ ተስፋዬን ቃለ መጠይቅ አድርጌው ለማቅረብ እሞክራለሁ እስከዛው መልካሙን ሁሉ እመኛለሁ::

# "በጣም የሚያሳዝነኝ . . .

: ምክንያቱም በአመት አንድ ድምፃዊ አንድ ወይም ሁለት ሙዚቃዎችን ይይዛል:: ምናልባት ጥላሁንና ብዙነሽ አራትና ሦስት ቢይዙ እነ ተዘራ ሁለትና ሦስት ቢይዙ፣ የባህሉ ዘፋኝ አንድ ቢይዝ እየተባለ በደረጃ እየወረደ ይመጣል:: ያኔ ልቡና ቀልቡ ቢኖር እነዛ ዘፈኖች በካሴት ተቀርፀው ለታሪክ ቢቀመጡ ኖሮ እጅግ በጣም ደስ ይለኝ ነበር:: ግን አልሆነም::

- በሸክላም በካሴትም የተቀረፀ የለህም?

አይይ . . . ማን አስተውሎት:: አንዳንድ በወቅቱ በሸክላ የተቀረጹ ቴሌቪዥንና ሬዲዮ ጣቢያ ይገኙ ይሆናል:: ለምሳሌ እንደነ ማርዬ ማር ወለላ

ማርዬ ማር ወለላ
እጥፍ ዘርጋ እንዳለንጋ
ተወርወሪ እንደ ሎሚ የመሣሠሉት ይኖራሉ::

አልፎ አልፎ ሲዘፈኑ እሰማቸዋለሁ::

- ይህቺ ያንተ ሥራ ነች?

ዜማውን የሠጠኝ ሥምረት ለገሠ የሚባል የጦር ሠራዊት መገናኛ ሠራተኛ ነው:: ጨፌ ጠጅ ቤት በአጋጣሚ ሲመጣ ጓዳ ስንጨፍር ይመለከትና ይሄን ዜማ ይሰጠኛል:: እኔም ከተጫወትኩ በኋላ ም/ጦሮች ይዘፍኑትና በሁለታችን መሀል ጭቅጭቅ ይፈጠራል:: ም/ጦሮች በባንድ ደረጃ ሙዚቃውን ተጫውተውታል:: ይህ የሆነው ዜማው ጥሩ ስለሆነ ነው::

- የሙዚቃ መሣሪያ ትጫወታለህ? ግጥምና ዜማስ ትደርሳለህ?

አልጫወትም:: ግጥምና ዜማ በተመለከተ ክፍሉ አንድ ባህል አለው:: ግጥምም ሆነ ዜማ ተጨንቀህና ተጠበህ ጽፈህ ስታመጣ "ቀሽም ናት ትቀመጥ" ስለምትባል ብዙ አትደፍርም:: መባል የነበረበት አይዞህ በርታ፣ በዚህ ቀጥል፣ ነገ ታሻሽላለህ የሚል መሆን ነበረበት:: በቦታው ላይም ምርጥ የግጥምና የዜማ አውጪዎች ነበሩ:: ስማቸውን መጥቀስ ካስፈለገ እነ ሻለቃ ሣህሌ ደጋጎ፣ በመጨረሻ ኰሎኔል ሻ/አፈወርቅ ዮሐንስ፣ ጋዜጠኛ ስለምን ተሰማ፣ ተዘራ ኃ/ሚካኤል፣ አየለ ማሞ፣ ዘውገ ገ/መድህን የመሣሠሉትን ማንሣት ይቻላል::

- በክፍሉ ውስጥ በርካታ ዓመትትን አስቆጥረሀልና ምን ትዝታ አለህ? ሳላደርገው አልፌያለሁ ብለህ የምትቆጭበት ነገር ሳይኖር ይሆን?

በአንድ ወቅት አስመራ የሚገኘው የቃኘው ሻለቃ ግቢ በፈንጂ በተመታ በሦስተኛው ቀን ቦታው ደርሰን ነበር:: ማረፊያችንንም እዛው አድርገን በአካባቢው ላለው ሠራዊት የተለያዩ ዝግጅቶችን እያቀረብን እንመለሣለን:: በአንድ ወቅትም ከረን ደርሰን ስንመለስ ምሳ ለመብላት እየተጣደፍን እንዳለ ምሣ እምባይ ሶራ ሆቴል ነው የምትበሉት የሚል ትዕዛዝ መጣልንና ወደዛው ሔድን:: በሆቴሉም ጥሩ መስተንግዶ ተደረገልን:: ምሳችንንም በልተን እንደጨረስን የሁላችንም ሀሳብ "ሞልቃቃው፣አትጨቅጭቀኝ፣ ላውንቸር . . ."እየተባለ በቁልምጫ የሚጠራውን መሎቲ ቢራ ለመጠጣት ነበር:: ነገር ግን እንደ ሀሣባችን ሣይሆን ቀረና በአስቸኳይ ወደ መንደፈራ እንድትንቀሳቀሱ ተባልን:: መቼም ወታደር ነንና እምቢ ማለት አንችልም ትዕዛዙን ተቀብለን ለመሄድ ተዘጋጀን:: በዚህን ጊዜ የቴሌቪዥን ካሜራ የነበረው በቀለ ነመራ አብሪያችሁ ካልሄድኩኝ አለ:: ጧት ብዙ ሠርተሀል ይበቃሀል ብንለው ፈጽሞ እሺ ሊለን አልቻለም:: ጉዞ ጀምረንም መንደፈራ ለመድረስ 5 ኪ.ሜ.ሲ ቀር ባለች መታጠፊያ ላይ መኪናችን በተቀበረ ፈንጅ ትመታለች:: የበቀለ ነመራ አይንም ይጠፋል:: በዚህ አሳዛኝ አደጋ መንበረ በየነ የምትባል ተወዛዋዥ (ድምፃዊ አይደለችም) ህይወቷ ሲያልፍ፣ ደምሴ የሚባለው እግሩ ተቆረጠ:: በቀለን በፊት ጊዜ መንገድ ላይ አየው ነበር አሁን ከአየሁት ቆይቷል:: በህይወቴ የሚቆጨኝ ነገር ቢኖር ተው ተመለስ እያልነው አደጋ ላይ መውደቁ ነው:: በጣም የሚያሳዝነኝ የበቀለ ነመራ ገጠመኝ ነው::

- ክ/ዘበኛ የቲያትርና የሙዚቃ ክፍልን ስታስበው ምን ይሰማሀል?

ክፍሉ አንድ ኃይል ያለው ነው የሚመስለኝ:: ሌሎቹ እንደ ም/ጦር፣ ብሔራዊ ቲያትር፣ ሀገር ፍቅር፣ ማዘጋጃ የመሳሰሉት ሁሉ ተወዛዋዥም መሣሪያ ተጫዋችም አላቸው ይሄኛው ክፍል ግን ከነገርማ ሞገስ እጹብድንቅ ሥራው:: ምናልባት ሰለሞናዊ ጥበብ ያረፈባት ስለሆነ ይሆን? ብለህም ለመጠየቅ ትገደዳለህ? የሚገርምህ በዘመን መለወጫ የተለያዩ የቲያትርና የሙዚቃ ክፍሎች ዝግጅቶቻቸውን ካቀረቡ በኋላ መዝጊያ የምንሆነው እኛ ነን:: ምክንያቱም ተመልካቹ ቁጭ ብሎ እንዲጠብቀን ይገደዳልና::

ሕዝቡ እንዳይወጣ እንደመያዣነት እንደሚጠቀሙባችሁ ጋሼ ዘውገ ገ/መድህንም በአንድ ወቅት አጫውቶኛል:: ይኸውልህ ጐሽ እንኳንም አልዋሸሁ:: ብቻ . . . ሣቅ . . . የባህሉን እነ ተዘራ ኃ/ሚካኤል፣ እሳቱ ተሰማ ዘፍነውት ሲጨርሱት በቅጽል ስሙ "የማይሰበረው ሽምበቆ" የሚባለውም ማሕሙድ አህመድ፣ የሙዚቃው ንጉስ ጥላሁን ገሠሠ፣ ብዙነሽ በቀለ ይቆጣጠሩታል:: ህዝቡ ስሜቱን መቆጣጠር እያቃተው መድረክ ላይ ስለሚወጣ ከመድረክ የሚወርደው በፀጥታ ኃይሎች ጥረት ነው:: የክቡር ዘበኛ ቴነርና አልቶ ሳክስ፣ ድራም፣ ጊታር ሁሉ ያወራል::

- ቅጽል ስም አለህ ይባላልና ስለ እሱ ብታጫውተኝ::

ይህቺን እንኳን ዝም ብለህ ነው ያነሣሁት:: ሣቅ . . . ለደቂቃዎች ካመነታ በኋላ "ቱሜ" የምትባል ቅጽል ስም አለችኝ:: ዝርዝር አፈታቱን ግን አልገባበትም:: ነፍሱን ይማረውና ጋሽ ጥላሁንም ጐደሎው እያለ ሲጠራኝ እኔም አዝሙ እያልኩ ነበር የምጠራው::

- አዝሙ ምን ማለት ነው?

አዝማሪ ማለት ነው::

- አንቆለጳጵሰህ መጥራትህ ነው?

አዎን ጥላሁን በሄደበት ሁሉ አብረህ መሄድና መታየት ላንተ እጅግ አስደሳች የኩራት ስሜት ይፈጥርልሀል:: የሚገርምህ ከእሱ ጋር አንድ ቡና ቤት ስትገባ ተከፍሎልሀል ነው የምትባለው:: ማን እንደከፈለ ግን አታውቅም::

- ሳይጠየቅ ሲከፈልለት ጥላሁን አይበሳጭም?

በጣም ይቆጣል:: ይናደዳል:: እኛ ግን ያው እንደምታውቀው . . .ነንና (ረጅም ሳቅ) ጋባዦች ጥላሁንን ነጥለው መጋበዝ ስለማይፈልጉ አብሮት ያለው ሁሉ ይጋበዛል::

- ከሱ ዘፈን ይበልጥ የምትወዳው የትኛውን ዘፈኑን ነው?

ትርፍ ህይወት የለኝም የምትለውን ነው::

- አንባቢ ማየት እንጂ መስማት ባለመቻሉ አሁን ያን ጐረጐርክልንን ማድመጥ ባይችልም እኔ ግን ግሩም ድምፅ እንዳለህ ለመመስከር እችላለሁና ሙዚቃ አቁመሀል ማለት ይችል ይሆን?

ድምጼ ሸረሪት እንዳያደራበት ጓደኞቼ ሠርግ ሥራ ሲያገኙ ይጠሩኝና እዛ ላይ እጫወታለሁ::

- ጌቾ መደበኛ ስራህ ምንድነው?

6 ኪሎ የሚገኘው መስከያ ሀዙናን መድሐኒያዓለም ገዳም ት/ቤት በጥበቃ ሥራ ላይ እገኛለሁ::

- ዕድሜህ ስንት ደርሷል?

ዕድሜዬ እንደምንም 60 ደርሷል::

- ቤተሰብ መሥርተሀል? ልጆች አሉህ?

አዎን አራት ልጆች አሉኝ:: 3 ሴት 1 ወንድ

- ከልጆችህ መሐል ወደ ሙዚቃው የተሳበ አለ?

ከልክያቸው እንጂ ይፈልጉ ነበር:: ምክንያቱም በኛ ጊዜ ምንም ነገር ስለሌለው ባዶአቸውን እንዲቀሩ ስለማልፈልግ አጥብቄ ነበር የምከለክላቸው::

- አሁን ቢሆንስ?

አሁንማ ምን ትጠይቀኛለህ:: ሙዚቃ ለገንዘብ አሁን ተሠራች:: ተወኝ . . . ባክህ!

- አመሰግናለሁ

እኔም አመሰግናለሁ::

# በአወሊያ ኮሌጅ ትምህርት ተቋርጧል

በዓለም አቀፍ እስላማዊ ድርጅት ይተዳደር የነበረው የአወሊያ ትምህርት ቤት ከጥር 1 ቀን 2004 ዓ.ም ጀምሮ ለተወሰኑ ቀናት ትምህርት ተቋርጦ እንደነበር ይታወሳል፡፡ ተማሪዎችም "ጥያቄዎቻችን እስካልተመለሰ ድረስ ከግቢ አንወጣም፣ የተባረሩ የግቢው ሰራተኞችም ካልተመለሱ ትምህርት አንጀምርም" የሚልና ሌሎች ጥያቄዎችን ለኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ም/ቤት አቅርበው ምላሽ እንዳላገኙ፤ መንግስትም ለጥያቄያችን ትኩረት ሰጥቶ ጉዳዩን በጥልቀት እንዲያይልን ሲሉ መጠየቃቸው አይዘነጋም፡፡

ይሁን እንጂ ከሚመለከተው የእስልምና ጉዳይ ጠቅላይ ም/ቤት የተወሰኑ ምላሾች የተገኙ በመሆናቸው የ2ኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች ትምህርታቸውን መጀመራቸውንና፤ ሁሉም ተማሪ ከግቢ የወጣ መሆኑ ቢገለፅም የኮሌጅ ተማሪዎች ትምህርት ግን አለመጀመሩ ተገልፃል፡፡ የተማሪ ተወካዮችም ከትምህርት ሚኒስቴርና ከእስልምና ም/ቤት ጋር ትናንት ሰኞ ጥር 7 ቀን 2004 ዓ.ም የጋራ ውይይት ማድረጋቸው የተጠቆመ ሲሆን ተማሪዎቹ "ጥያቄያችን አሁንም ቢሆን አልተመለሰልንም፣ ትምህርታችንም ተቋርጧል፣ መቼና በምን መልኩ እንደምንጀምር የተገለፀ ነገር የለም፡፡" ማለታቸውን ምንጮቻችን ገልፀዋል፡፡ ይህንንም በኮሌጁ ግቢ ሄደን ትምህርት አለመጀመሩን ለመረዳት ችለናል፡፡ የዚህንም ምክንያት ለማጣራት ያደረግነው ሙከራ ለጊዜው አልተሳካም፡፡

# "በሽብርተኝነት" የተከሰሱት በድጋሚ ተቀጠሩ
## እነ በቀለ ገርባ ዛሬ ፍ/ቤት ይቀርባሉ

"በሽብርተኝነት" ተጠርጥረው ጉዳያቸው በፍ/ቤት በመታየት ላይ የሚገኙት ሁለቱ የክስ ፋይሎች ለፍርድ ውሳኔና ለብይን በድጋሚ ሲቀጠሩ ሦስተኛው የክስ መዝገብ የዐቃቢ ህግ የምስክር ቃል ለማድመጥ ለዛሬ ተቀጥሯል፡፡

በዚሁ መሠረት በእነ ኤልያስ ክፍሌ የክስ መዝገብ ተከሰው ጉዳያቸውን በመከታተል ላይ ከሚገኙት አቶ ዘሪሁን ገ/እግዚሐብሄር፣ ጋዜጠኛ ውብሸት ታዬ ወ/ሮ ሂሩት ክፍሌና ጋዜጠኛና መምህርት ርዕዮት ዓለሙ ባለፈው ጥር 1 ቀን 2004 ዓ.ም ለፍርድ ውሳኔ ተቀጥረው የቀረቡ ቢሆንም መዝገቡ ተመርምሮ ውሳኔ መስጠት ባለመቻሉ በድጋሚ ለጥር 10 ቀን 2004 ዓ.ም /ከነገ በስቲያ ለሐሙስ/ ተቀጥሯል፡፡ በተያዘው ቀጠሮ መሠረት በሚቀጥለው ሐሙስ የፍርድ ውሳኔ ይሰጣል ተብሎ ይጠበቃል፡፡

በእነ አንዱዓለም አራጌ የክስ መዝገብ የተከሰሱት አንዱዓለም አራጌ፣ ናትናኤል መኮንን፣ ዮሐንስ ተረፈ፣ የሺዋስ ይሁንዓለም /ሻምበል/፣ ክንፈ ሚካኤል ደበበ፣ ምትኩ ዳምጤ፣ እስክንድር ነጋና አንዱዓለም አያሌው የአቃቢ ህግ ምስክሮች እና ማስረጃዎች ተደምጠው በመጠናቀቁ ጥር 4 ቀን 2004 ዓ.ም ለብይን ተቀጥሮ ነበር፡፡ ሆኖም ግን ከታህሣስ 19 ቀን 2004 ዓ.ም በኋላ ያለው የምስክሮች ቃል ተገልብጦ ከማህደሩ ጋር አልተያያዘም በሚል በድጋሚ ለጥር 14 ቀን 2004 ዓ.ም /ለሚቀጥለው ሰኞ/ ለብይን ተቀጥሯል፡ ፡

በሌላ በኩል ደግሞ በእነ በቀለ ገርባ የክስ መዝገብ የተከሰሱት 1ኛ ተከሳሽ የኦሮሞ ፌዴራላዊት ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ /ኦፍዴን/ም/ሊቀመንበር አቶ በቀለ ገርባ, የኦሮሞ ህዝብ ኮንግረስ ሥራ አስፈጻሚና የጽ/ቤቱ ኃላፊ አቶ አልባና ሌሊሳን ጨምሮ 9 ሰዎች ላይ 18 የዐቃቢ ህግ ምስክሮች የምስክርነት ቃላቸውን የሰጡ ሲሆን ቀሪዎቹ 7 ሰዎች በዛሬው ዕለት የምስክርነታቸውን ቃል ይሰጣሉ ተብሎ ይጠበቃል፡፡ በተያዘው ቀጠሮ መሠረት ዛሬ ከሰዓት በኃላ በ8 ሰዓት ላይ ፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት 3ኛ ወንጀል ችሎት ይቀርባሉ፡፡

# በሚዛን ተፈሪ ከተማ 41 የንግድ ሱቆች ታሽገዋል

ብሥራት ወ/ሚካኤል

በደቡብ ክልል በምዕራብ ኢትዮጵያ ቤንች ማጂ ዞን በሚገኘው ሚዛን ተፈሪ ከተማ 41 የንግድ ሱቆች በህገ-ወጥ መንገድ ታሽገዋል ሲሉ ነዋሪዎች ገለፁ፡፡ ሱቆቹ ከታሸጉ ከ15 ቀናት በላይ እንደሆናቸው፤እርምጃው የተወሰደው አዲሱ የመንግሥት ቤቶች አከራይና ተከራይ አዋጅን መሠረት አድርጐ እንደሆነ እንደተነገራቸውና ህገ ወጦች ናችሁ ተብለን ነው ሲሉ ነጋዴዎቹ ቅሬታቸውን ገልፀዋል፡፡ ነጋዴዎቹም "እኛ በኮንቴይነር ሱቅ ውስጥ ሕጋዊ ውል ፈፅመን፣ተከራይተን፣በምንሰራበት ሱቅ ሕጋዊ ንግድ ፈቃድ አውጥተን እየሰራን ሳለ ምክንያቱ ባልታወቀበት ውጡ ብለው ዕቃችን ላይ አሽገው ከ15 ቀናት በላይ ሆኖናል" ሲሉ የተሰማቸውን ቅሬታ ገልፀዋል፡፡ ነገር ግን ምክንያቱ ሳይገለፅ አርብ ጥር 4 ቀን 2004 ዓ.ም "ነጋዴዎች በ9 ቀናት ውስጥ ዕቃዎቻችሁን እንድታወጡ" የሚል ማስታወቂያ ከማዘጋጃ ቤት ተፅፎ ተለጥፏል ሲሉ ነዋሪዎቹ ገልፀዋል፡፡

ይህንንም ለማጣራት የከተማው ንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮ ኃላፊ የሆኑት አቶ ልጅዓለም ታደሰ ስለሁኔታው ጠይቀናቸው "ኮንቴይነር ሱቅ ለጥቃቅንና አነስተኛ የተሰራ ሲሆን በኪራይ ለ3ኛ ወገን ማስተላለፍ አይፈቀድም፡፡ በኤች አይ ቪ እና በተያያዥ ጉዳዮች ችግር ያለባቸውና ያከራዩ 5 ሰዎች ሰኞ እንዲከፈትላቸው አርብ ባደረግነው ውይይት ወስነናል ነጋዴዎቹም ህጋዊ ውልም ሆነ ፈቃድ የላቸውም" ሲሉ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

በተጨማሪም ጉዳዩ ይመለከታቸዋል የተባሉትን የሚዛን አማን ክፍለ ከተማ ሥራ አስኪያጅ አቶ ሙሉቀን ደጀኔን ስለ ጉዳዩ ጠይቀናቸው "የንግድ ሱቆቹን ለማሸግ የወሰነነው ከንቲባውን ጨምሮ ከሚመለከታቸው የከተማ መስተዳደሩ ጋር ከተነጋገርን በኋላ ነው፡ ፡ ነጋዴዎቹ ሕጋዊ የንግድ ፈቃድ ቢኖራቸውም ለተፈጠረው ችግር ተጠያቂ መሆን ያለበት ፈቃድ የሰጠው አካል እንጂ እኛ አይደለንም፡፡" ሲሉ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ በዚህ ላይ ማብራሪያ እንዲሰጡን የከተማው ማዘጋጀ ከንቲባው ጽ/ቤት ደውለን ጉዳዩ የሚመለከተው ክፍለ ከተማውን ነው በማለት ምላሽ ሰጥተውናል፡፡

ሱቃቸው የታሸገ ነጋደዎች በበኩላቸው "እኛ ሕጋዊ የኪራይ ውልና የንግድ ፈቃድ ያለንንና ተገቢውን የአገር ውስጥ የመንግሥት ግብር እየከፈልን ለዓመታት ሰርተናል፡፡ አሁን ያለሥራ ሱቃችን ታሽጐ ከ15 ቀናት በላይ በመሆኑ ለከፍተኛ ችግር ተጋልጠናል፣የሚመለከተው የመንግሥት አካል በአፋጣኝ መልስ እንዲሰጠን እንጠይቃለን፡፡" ሲሉ የተሰማቸውን ገልፀዋል፡፡

# በሀዲያ ዞን ሙስናው ተጧጡፏል

ብሥራት ወ/ሚካኤል

በሀዲያ ዞን ሆሣዕና ከተማ በዞኑ ባለሥልጣናት 600 ያህል የተለያዩ ቦታዎች ህገ-ወጥ ወረራ መካሄዱ ተጠቆመ፡፡ በተለይም አዲሱን የከተማ ቦታ ሊዝ አዋጅ ገና ሳይተገበር በከተማው ባሉ ሴች ዱና፣አዲስ ከተማና ጐፈር ሜዳ ክፍለ ከተሞች አዋጁን ተገን አድርገው ከከተማው ፕላን ውጭ ባለሥልጣናቱ ለግል ጥቅማቸው ወረራ መፈፀማቸውን ምንጮቻችን ጠቁመዋል፡፡ በሕገ-ወጥ መንገድ የተወረረውንም ቦታ ሕጋዊ ለማድረግ ባለሥልጣናቱ ጉዳዩን እንዲያስፈፅሙ በድብቅ ኮሚቴ ማዋቀራቸውንና ለአስፈፃሚዎቹም ለእያንዳንዳቸው 5 ሺህ ብር እየተሰጠ እንደሆነ የውስጥ ምንጮቻችን የገለፁ ሲሆን ይህንንም የዞኑ ፀረ-ሙስና ኮሚሽን እና የሆሣዕና ከተማ መስተዳደር ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ኤጀንሲ ጥቆማው ደርሷቸው እየተንቀሳቀሱ እንደሆነ ተገልጿል፡፡

ይህንንም ለማጣራት የከተማ መስተዳደሩ ፀረ ሙስና ኤጀንሲ ኃላፊ ወ/ሮ ደስታ ዘርፉ በመሬት ዙሪያ ከፕላን ሽንሽና ውጭ ያለውን የሙስና ተግባር ጥቆማ እንደደረሳቸውና ጉዳዩን እየተከታተሉት እንደሆነ ገልፀው ባለሥልጣናቱ ፈፀሙት ለተባለው የመሬት ወረራ ግን መረጃ በግልፅ ማን ምን እንዳዳረገ የታወቀ ነገር እንደሌለና እንዳልደረሳቸው ክትትሉን ግን እንደሚቀጥሉ ገልፀውልናል፡፡

በተያያዘ ዜና በዛው በሀዲያ ዞን ሶሮ ወረዳ ጊምቢቹ ከተማ አመራሮቹ ከህግ አግባብ ውጭ ቤት ሰርተው በውድ ዋጋ ለሚሰሩበት ለተለየየ የመንግሥት መስሪያ ቤት በማከራየት ህገ-ወጥ የግል ጥቅም እያካበቱ እንደሆነና ይህም መንግሥትን ለአላስፈላጊ ወጪ በመዳረግ የወረዳው ካቢኔዎች ሙስና እየፈፀሙ እንደሆነ ከሥፍራው የደረሰን መረጃ ያመለክታል፡፡ የዞኑ ባለሥልጣናት ሕገ-ወጥ የመሬት ወረራንና የሶሮ ወረዳ ካቢኔዎችን ሙስና ተግባር ለማጣራት የሀዲያ ዞን ፀረ-ሙስና ኤጀንሲ ኃላፊ አቶ ተመስገን ኤሌሮን ጠይቀን በተጠቀሱት የሙስና ተግባራት የደረሳቸው ጥቆማዎች እንደሌለ፣መሬት ነክ ሙስና ተግባራትን በሚመለከት የክልሉ ፀረ ሙስና ኮሚሽን የሥነ ምግባርና ደንብ ክትትል ሥራ እንደሆነ ገልፀውልናል፡ ፡ ነዋሪዎቹ በበኩላቸው በዞኑ የሙስና ተግባር ተጧጡፏል፣ የሚመለከተው የክልልም ሆነ የፌደራል መንግሥት በመሬትና በአስተዳደር ጉዳዮች ክትትል አድርገው መፍትሄ እንዲሰጡ ጥሪ አቅርበዋል፡፡ በተለይ ነዋሪዎቹና አንዳንድ ስማቸው እንዳይጠቀስ የፈለጉ የመንግሥት ሠራተኞች በዞኑና በከተማው የተለያዩ ሙስና ተግባሮችን ጥቆማ ብናደርግም ምንም ዋስትና ስለሌለንና በተደጋጋሚ ችግር ላይ ስለወደቅን የበላይ አካል የዞኑን ችግር በጥልቀት እንዲያየው እንሻለን ሲሉ ጠይቀዋል፡፡

# አንድነት በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ላይ ሕጋዊ እርምጃ ለመውሰድ እየተወያየ መሆኑን ገለፀ

አንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ /አንድነት/ ከሕዳር 16-18 ቀን 2004 ዓ.ም የኢትዮጵያ ሬዲዮና ቴሌቪዥን ድርጅት "አኬልዳማ" የሚል ዘጋቢ ፊልም በቴሌቪዥን ማሰራጨቱ ይታወቃል፡፡ በዚህም ፊልም ላይ የአንድነት አመራሮች ስምና ምስል አብሮ የቀረበ ሲሆን ይህንንም አስመልክቶ ቴሌቪዥን ድርጅቱ የፓርቲውን ስም አጥፍቷልና በተላለፈው ሰዓት የአየር ጊዜ ሰጥቶ ፓርቲው በተሰራው ፕሮግራም ላይ ያለውን አቋም ለሕዝብ እንዲገልፅ እንዲፈቀድለት ለኢትዮጵያ ብሮድካስት ባለሥልጣን ደብዳቤ መፃፉ ይታወሳል፡፡

የኢትዮጵያ ብሮድካስት ባለሥልጣንም የኢትዮጵያ ቴሌቪዥን የሀገሪቱ የመገናኛ ብዙሃን ሕጐችና የጣቢያው ኤዲቶሪያል ፖሊሲ በሚፈቅደው መሠረት ፓርቲውን እንዲያስተናግድ ግልባጭ ለፓርቲው በጻፈው ደብዳቤ ገልፆ ነበር፡፡ ይሁን እንጂ የኢትዮጵያ ሬዲዮና ቴሌቪዥን ድርጅት ለብሮድካስት ባለሥልጣን ምላሽ እንደሰጠ ቢገልፅም ለፓርቲው ግልባጭ ደብዳቤ ባለመድረሱ ለረጅም ጊዜ የጣቢያውን መልስ ፓርቲው እየጠበቀ ምላሽ እንደላገኘ ተገልጿል፡፡ በመጨረሻም አንድነት ፓርቲ ጥር 2 ቀን 2004 ዓ.ም ለኢትዮጵያ ሬዲዮና ቴሌቪዥን ድርጅት ዋና ሥራ አስኪያጅ "አፋጣኝ መልስ እንዲሰጠን ስለመጠየቅ" በሚል ደብዳቤ ጽፎ ምላሽ ካላገኘ ሙብቱን በህግ ለመጠየቅ እንደሚገደድ አስታውቆ ነበር፡፡

የኢትዮጵያ ሬዲዮና ቴሌቪዥን ድርጅት ጥር 4 ቀን 2004 ዓ.ም "መረጃ ስለ መስጠት" ብሎ ለአንድነት "ፓርቲያችሁ ጥር 2 ቀን 2004 ዓ.ም የላከው ደብዳቤ ደርሶናል፡፡ ቅሬታችሁን በተመለከተም ቀደም ሲል በብሮድካስት ባለሥልጣን በኩል ተጠይቀን በወቅቱ ምላሻችንን የሰጠን መሆናችንን እናስታውቃለን፡፡" ብቻ የሚል መልስ ከጣቢያው ዋና ዳይሬክተር ጽ/ቤት እንደተላከና ምላሹም በቀጥታ ለፓርቲው መላክ ሲገባው ከዚህ ውጭ መልስ እንዳልተሰጠ ፓርቲው ገልፆ፤ከዚህ በኋላ ሕግን ተከትለን ሕጋዊ እርምጃ ለመውሰድ እየተወያየን ነው ሲሉ የፓርቲው ሊቀመንበር ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ በተለይ ለዝግጅት ክላችን ገልፀዋል፡፡

የብሮድካስት ባለሥልጣን ጥር 4 ቀን 2004 ዓ.ም በላከው ደብዳቤ የኢትዮጵያ ቴሌቪዥን በላከው ምላሽ የፓርቲውን ስም እንዳላጠፋና የአየር ሰዓት መድቦ ለማስተናገድ የሚያስችል ሕጋዊ ምክንያት እንዳላገኘ ገልጿል ሲል ባለሥልጣኑ ምላሽ መስጠቱ ተጠቁሟል፡፡

# በሰሜን ጐንደር አንድ ሱፐርቫይዘር ራሱን ሰቀለ

በሰሜን ጐንደር ደንቢያ ወረዳ ቆላድባ ከተማ የትምህርት ቤቶች ሱፐርቫይዘር የነበረው መምህር መልኬ ፈንታሁን በሚሰራበት ወረዳ ድብደባ ተፈፅሞበት በውስጡ በተፈጠረ ደም መፍሰስ ወላጅ እናቱ ጋ ጐንደር ሄዶ እንደነበር ምንጮቻችን ገልፀዋል፡፡

መ/ር መልኬ ጐንደር ከተማ ቀበሌ 12 ቀጠና 3 ትናንት ሰኞ ጥር 7 ቀን 2004 ዓ.ም ከጠዋቱ 4፡30 ሰዓት ላይ ራሱን ሰቅሎ መሞቱ ተገለፀ፡፡ መምህሩም በሚሰራበት ወረዳ በፖለቲካ ምክንያት ከፍተኛ በደል ይፈፀምበት እንደነበር የተጠቆመ ሲሆን ከቀኑ 10 ሰዓት ላይ ትናንት በአባ ጃሌ አቡነ ተ/ኃይማኖት ቤ/ክርስቲያን የቀብር ሥነ-ሥርዓቱ መፈፀሙን ከሥፍራው መረጃ ምንጮቻችን ያገኘነው መረጃ ጠቁሟል፡፡ ይህንንም አሟሟት ለማጣራት ሕትመት እስከገባንበት ድረስ ወደ አካባቢው ፖሊስ ሙከራ ብናደርግም አልተሳካም፡፡

ዜና

# በደቡብ ክልል እጅግ በጣም የከፋ ግፍ በደልና መከራ እየተፈጸመ መሆኑን ጋዴህ ገለጸ

በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የመልካም አስተዳደር እጦት፣ የሙስና መስፋፋት የሀገርና የህዝብ ሀብትና ንብረት ዘረፋ እና በህዝብና በዜጎች ላይ የሚደርስ ግፍ፣ በደልና መከራ እየከፋ መሆኑን የጋሞ ዴሞክራሲያዊ ሕብረት/ጋዴህ/ ገለፀ፡፡ ፓርቲው ይህንን የገለፀው ሰሞኑን "ሀገርን መበደል፣ ዜጎችን ማሰቃየት የሀገርና የህዝብ ሃብትና መዝረፍ ይቁም!!" በሚል ርዕስ ባወጣው መግለጫ ነው፡፡ መግለጫው እየደረሰ ነው ያለውን በዝርዝር ከገለፀ በኃላ ባለ አምስት ነጥብ የአቋም መግለጫና ባለ አምስት ነጥብ ንዑስ ነጥቦችን በመዘርዘር ይገልጻል፡፡

በሌላ በኩል ፓርቲው በአድራሻ ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ለአቶ መለስ ዜናዊ ፣ ለም/ጠ/ሚኒስትሩና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ለአቶ ኃ/ማሪያም ደሳለኝ፣ ለኢህአዴግ ጽ/ቤት፣ በግልባጭ ለኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት ኮሚሽን፣ ለህዝብ እንባ ጠባቂ ኮሚሽንና ለስነ ምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን በላከው 12 ገጽ ደብዳቤ በክልሉ እንዲደርስ ያለውን ግፍ፣ በደልና መከራ በዝርዝር ገልጾታል፡፡ አስፈላጊው እርምት እንዲወሰድ ጥሪውን አቅርቧል፡፡

እንዲሁም ያለ አግባብ ድብደባ፣ እስራት የገንዘብ ቅጣት፣ መሬታቸውን የተነጠቁ ሰዎች ዝርዝር አቅርበዋል፡፡ በቀረበውም ዝርዝር ከ6 ዓመት እስራት እስከ ቀላል እስራት ያለፍርድ ለረጅም ጊዜ መታሰር ያለምንም ጥፋት ረጅም ጊዜ አስሮ ደብድቦና አሰቃይቶ መልቀቅ እየተፈፀመ መሆኑን በመዘርዘር ተጐጂ ናቸው ያላቸውን የ51 ሰዎች ጉዳታቸውን በመዘርዘር ያብራራል፡፡ የፓርቲውን መግለጫ በገጽ 15 ይመልከቱ፡፡

# ኦነግ ወደ ሠላማዊ ትግል እንዲገባ ኢራፓ ጥሪ አቀረበ

ብዙአየሁ ወንድሙ

"የኦሮሞ ነፃነት ግንባር /ኦነግ/ የግንባሩ ትግል የኦሮሞን ህዝብ በማስገንጠል ተልዕኮ ላይ የተመሠረተ ሳይሆን ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነትን ማዕከል በማድረግ ለኦሮሞ ህዝብና ለቀሩትም ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች እንደ አንድ ህዝብና እንደ አንድ ሀገር ለዴሞክራሲያዊ ስርዓት ለፍትህና ለነፃነት ለዜጐች መሠረታዊና ዴሞክራሲዊ መብቶች ለእኩልነትና ለጋራ ብልጽግና የጋራን ቤት በጋራ ለመገንባት የወሰደው እርምጃ የሰላምንና በአብሮነት ወይም በቤተሰባዊነት የመኖርን ተስፋ የሚያለመልም ወሳኝ ክንውን ተደርጎ መቀበልና በንፁህ ሕሊና መመልከት አግባብነት ያለው ቢሆንም ይህ የኦነግ መሠረታዊ የፖሊሲ ለውጥ እወጃ በተወሰነ ደረጃ ለህጋዊና ፖለቲካዊ ወይም ድርጅታዊ ጥያቄዎችና ጥርጣሬዎች በቂ መልስ የሰጠ አይመስልም፤" ሲል የኢትዮጵያ ራዕይ ፓርቲ /ኢራፓ/ አስታወቀ፡፡ ኢራፓ ይህንን ያሳወቀው "የወቅቱ የኦነግ መስመር ቢጠራ መልካም ነው" በሚል ርዕስ ሰሞኑን ባወጣው መግለጫ ነው፡፡

ፓርቲው ኦነግ ሰሞኑን በአሜሪካን አገር ሜኒሶታ ከተማ ተሰብስቦ መገንጠልን ከትግል መስመሩ ማውጣቱን መሠረት አድርጌ ያወጣሁት መግለጫ ነው በማለት ይዘረዝራል፡፡ ህጋዊነትንም በተመለከተ ባለ አራት ነጥብ ዝርዝሯል፡፡ ኢራፓ አያይዞም በአገሪቱ ውስጥ ብሔራዊ መግባባት እንዲፈጠር እውነተኛ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት እንዲገነባ ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች እንዲከበሩ ሁሉም በግልጽነት በቅንነት ርብርቦሽ እንዲጀመር ጥሪውን አቅርቧል፡፡

በተያያዘ ዜና ከአምስት ወር በፊት ወደ ሰሜን አሜሪካን አቅንተው የነበሩት የፓርቲው ፕሬዝዳንት ሥራቸውን አጠናቀው መመለሳቸውን የፓርቲው ጽ/ቤት ለዝግጅት ክፍላችን ገልጾል፡፡ እንደ ፓርቲው ጽ/ቤት መረጃ የፓርቲው ፕሬዝዳንት አቶ ተሻለ ሠብሮ ወደ አሜሪካን አገር የተጓዙት የፓርቲያቸውን ዓለማና ፕሮግራም በተለያየ ቦታ ለሚገኘው ዲያስፖራና ሚዲያዎች ለማስተዋወቅና የድጋፍ ሰጪ ቻብተሮችን ለማደራጀት ነው ተብሎአል፡፡

ስለ ጉዞአቸው የጠየቅናቸው አቶ ተሻለ ሠብሮ እንዳሉት "በሰሜን አሜሪካንና በካናዳ ሞቶሪያል ስቴት ተገኝቼ በተዘጋጁ መድረኮች ጋር ከበርካታ ኢትዮጵያኖች ጋር የፓርቲውን ደንብና ፕሮግራም ገለጻ አድርጌአለሁ፡፡ የፓርቲውን ዓላማ ግልጽ ባልሆኑ ቦታዎችና ብዥታ በነበረበት ቦታ ሁሉ የፓርቲውን የጠራ ዓላማ አሰጨብጫአለሁ፡፡ በተለይ በዋሽንግተን ዲሲ፣ በዋሽንግተን እስቴት ስያትል ከተማ፣ በደቨር ኮሎራዶ በመገኘት ማብራሪያ ሰጥቼአለሁ፡፡ በአገሪቱ ወቅታዊ ሁኔታም ላይ ለተነሱ ጥያቄዎች ማብራሪያ አቅርቤአለሁ፡፡ የተለያዩ የአማርኛ ሬዲዮ ፕሮግራሞች፣ በአንድ ቴሌቭዥን ጣቢያ፣ ስለወቅቱ የአገሪቱ ሁኔታ ተጋብዤ መልስ ሰጥቼአለሁ፡፡ በሁለት ቴሌ ኮንፍረንሶች በመቅረብ የፓርቲውን የፖለቲካ መስመሩንና የኢትዮጵያን ተጨባጭ የፖለቲካ ሁኔታ ለማስረዳት ሞክሬአለሁ" ብለዋል፡፡ የጉዞአቸውን አጠቃላይ ሁኔታ ሲያጠቃልሉ አቶ ተሻለ እንዳሉት "በሄድኩባቸው ሥፍራዎች የፓርቲውን ቻብተር ጥንስስ ጥለናል፡፡ የተሳካ ሥራ አከናውነናል፡፡ ከእንግዲህ ፓርቲው ጠንክሮ ይሠራል ብለን ተስፋ እናደርጋለን፡፤ ተመሳሳይ ዓላማ ካለን ፓርቲዎች ጋር በጥምረትና በቅንጅት ለመታገል አቅደናል" በማለት መልስ ሰጥተውናል፡፡

# አስደንጋጭ መረጃ 39% ኢትዮጵያዊ ስለቲቢ በሽታ ምንም አያውቅም

ብሩክ ከበደ

የሣምባ ነቀርሳ (T.B) በሽታ አመጣጥ፣ አሠረጫጨቱና ሌሎች ተያያዥ ጉዳዮችን በተመለከተ በኢትዮጵያ ሕዝብ 39% በመቶ የሚሆኑት ምን ሰምተው አያውቁም፡፡ KAP (Knowledge attitude and practice) እ.ኤ.አ 2010ና 2011 ያደረገውን ዳሰሳ ጥናት ይፋ አደረገ፡፡

ይህው እ.ኤ.አ ከጥቅምት 2010 እስከ ሰኔ 2011 እ.ኤ.አ በተደረገውና 4670 ዕድሜያቸው በ15 ና ከዛ በላይ የሆኑ በገጠር፣ በከተማ አርብቶ አደሩና በጠቅላላው በሀገሪቷ ላይ በሚኖሩ ዜጐች ላይ በተደረገው ጥናት ዋንኛ መመዘኛ የነበረው ዕውቀት፣ አመለካከት፣ መገለልን ጨምሮ ጤና ሠራተኞችና በጠቅላላው ህብረተሰቡ በበሽታው ላይ ያለውን ጠቅለል ያለ ግንዛቤ ዕውቀት ያካተት ነበር፡፡

በዚሁ መሠረት በ63 የገጠር፣ በ214 ከተሞች፣ በ8 አርብቶ አደሮች ውስጥ በተደረገው ዳሰሳ 39% በህይወታቸው ስለ ሣንባ በሽታ ሰምተው የማያውቁ ሲሆን፣ 61% ሰምተው እንደማያውቁ 75% ሳል የበሽታው ዋንኛ ምልክት መሆኑን እንደሚያውቁ ሲገልጹ ሌሎች 52% በሳልና ማስነጠስ በሚወጡ ፈሳሾች በሽታው እንደሚተላለፍ ሲናገሩ ሌሎች 11% ከበሽተኛው ጋር በአንድ ሣህን መመገብ በሽታው ይተላለፋል ብለው እንደሚገምቱ መረጃው ይጠቁማል፡፡

ሌላው በተመረጡ 4579 ሰዎች ላይ በተደረገው የተለያዩ መጠይቂያዊ ጥናቶችም 35% ሣንባ በማህበራዊ ግንኙነት ላይ እንቅፋት እንደሆነ ሲያመለከቱ 41.5% ማህበረሰቡ እንደሚያገላቸው 65% በጥንዶች ላይ ችግር እንደሚያመጣ 64.4% ለመጋባት እንቅፋት እንደሆነባቸው ጥናቱ የተካሄደባቸው እንደገለጹና ይህም የሚያሣየው ሣንባ በማህበራዊ ግንኙነት፣ በጋብቻ፣ በቤተሰብ ትስስር ላይ ከፍተኛ ተጽእኖ እንደሚያመጣ ጥናቱ በግል አስቀምጦታል፡፡

KAP ጥናቱንም ሲያጠናቅቅ ሕብረተሰቡ በሣንባ ላይ ያለው ዕውቀት አናሣ መሆኑና ከላይ በተቀመጡትና በተዘረዘሩት ምክንያቶች በግልጽ ያሣወቀ መሆኑ በብሔራዊ የሣንባ ቁጥጥር ፕሮግራም ላይ የማስጠንቀቂያና የማንቂያ ደውል መሆኑን መገንዘብ እንዳለበት አሣውቋል፡፡

# የሊዝ አዋጁን በተመለከተ . . .

ከ 2 የዞረ

የሊዝ አዋጅ ዳሰዋል፡፡ አከናወንን ያሉትን ልማቶችም ዘርዝረዋል፡፡ አጭበርባሪዎችና ደላሎች በፈጠሩት ህገወጥ የመሬት ግብይት የሊዝ አዋጁ ሊወጣ ችሎአል፡፡ አዋጁ ለምናከናውነው ልማትና የመሬት ሽያጭና ዝውውርን ሥርዓት ለማስያዝ ይጠቅማል" በማለት የመግቢያ ንግግር አድርገዋል፡፡

ተሰብሳቢዎች ሪፖርቱን በማጣጣል በቀጥታ በሊዙ ላይ አስተያየታቸውን ሰጥተዋል፡፡ ተሰብሳቢዎች ባቀረቡት አስተያየት "የሊዝ አዋጁ ኃላፊነት በጐደለውና በማን አለብኝነት አጽድቃችሁታል፡፡ በፀደቀ አዋጅ ላይ ለምን ልታወያዩን ፈለጋችሁ? ለምንስ በፀሐይ ታንቃቁናላችሁ? ለምን አዋጁ ከመውጣቱ በፊት አለወያየናችሁም? እስከዛሬ በመሬት ላይ ወንጀል ሲፈጽሙ የቆዩት መንግስት በየቦታው ያስቀመጣቸውና ኢንቬስተሮች ናቸው፡፡ እነሱ በፈፀሙት ወንጀል ከአያት ቅድመ አያት የመጣውን የደሃውን መሬት ለመቀማት ለምን አዋጅ ማውጣት አስፈለገ? ወደፊት መሬት እገዛለሁ፣ ንብረት አፈራለሁ ብሎ ተስፋ ያደረገ ዜጋን ህይወቱን ለምን ታጨልሙበታላችሁ? እያንዳንዱ ሰው እስከ 150 ካሬ ሜትር በነፃ መሬት ያገኛል የሚለው መመሪያ በአፈጻጸም ችግር ሳይፈፀም ቀረ፡፡ ስለዚህ አዋጁን አንቀበልም፡፡ መንግስት አማካሪም የለውም፡፡ በመንግስት መዋቅር ውስጥ ከላይ እስከታች ያሉት ለህዝብ አመራር የማይመጥኑ ናቸው፡፡" በማለት ሐሳብ ሰጥተዋል፡፡ ለረጅም ሰዓት በመድረክ መሪዎቹና በተሰብሳቢዎች መካከል መግባባት ባለመቻሉ ተሰብሳቢው አዳራሹን ለቆ ወጥቷል፡፡

በተያያዘ ዜና አዲሱን የከተማ ቦታ ሊዝ አዋጅን አስመልክቶ በአዲስ አበባ ከተማ መስተዳደር በሚገኙ በተለያዩ ክፍለ ከተሞች በሚገኙ ወረዳዎች ውይይት ተካሂዷል፡፡ አወያዮችም አመራሮች ሲሆኑ ስለአዋጁ ጠቀሜታም ሲያብራሩ ከሊዝ በሚገኘው ገቢ ዩኒቨርስቲዎች፣ ሆስፒታሎችና ጤና ጣቢያዎች፣ ት/ቤቶች፣ መንገድ፣ ውሃ እና ኮንዶሚኒየም ቤት እንደሚሰራ በዚህም ህብረተሰቡን ተጠቃሚ እንደሚያደርግ ገልፀዋል፡፡ ነገር ግን በውይይቱ ተሳታፊዎች ከፍተኛ ተቃውሞ ቀርቦባቸዋል፡፡ ተሳታፊዎችም "ግብር የምንከፍለው ለምንድ ነው? የተጠቀሱትን ልማቶች ለማሰራት አይደለም እንዴ?" ሲሉ ተደምጠዋል፡፡

በተንቀሳቀስንባቸው እና ከተለያዩ ቦታ የተገኙ ሪፖርቶች እንደሚያመለክቱት ከሆነ አዲሱ አዋጅ ከፍተኛ ተቃውሞ ገጥሞታል፡፡ ይህም በኢቴቪ 2 (በአዲስ ቴሌቪዥን) ፕሮግራም ላይም በዕለቱ ተዘግቧል፡፡ በተለይ በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ ወረዳ 9 በድንኳን ውስጥ በነበረው ውይይት ተሳታፊዎች "እኛ በቀድሞ ፕሬዝዳንት መንግስቱ ኃይለማርያም የቤት ባለቤት እና የነባር ይዞታ ባለቤቶች ነን፡፡ ያለንም ቦታ 144 ካሬ ሜትር ሲሆን ይህን ቦታ ለልጆቻችን እናውርስ ብንል ስለማይበቃ የግድ ሸጠን ገንዘቡን ማከፋፈል ነው ያለብን፡፡ ነገር ግን በአዲሱ አዋጅ ነባር ይዞታ ሲሸጥ ወደ ሊዝ የሚተላለፍ እንደሆነና በዚህም ተጠቃሚው ባለይዞታው ሳይሆን መንግስት ነው፡፡ እና ማውረስ ይቻላል ያላችሁት ምኑን ነው? አዋጁ ከመፅደቁ በፊት ለምን ለህዝብ ውይይት አልቀረበም? ካፀደቃችሁት በኋላስ መወያየቱ ምን ጥቅም አለው?" የሚሉ ጥያቄዎች ሲነሱ ከተሳታፊው የሞቀ ጭብጨባ ለማየት ችለናል፡፡ ሌላ አንድ ተሳታፊም "አዋጁ የህዝብን ተጠቃሚነት ያረጋግጣል" ብሎ አስተያየት ሲሰጥ ከፍተኛ ተቃውሞ ከህዝቡ ሲቀርብበት ሐሳቡን ሳይቋጭ ተቀምጧል፡፡ በመጨረሻም ከተሳታፊው በርካታ እጆች "ጥያቄ አለኝ" የሚሉ እና ዕድል ያልተሰጣቸው ቢታዩም አወያዮቹ ቀድመው ለቀረቡት ጥያቄ መልስ የሰጡ ሲሆን ተሳታፊዎችም "ጥያቄያችን አልተመለሰም፣ ለምን አለባብሳችሁ ትዘጉናላችሁ?" የሚል ተቃውሞ ቢሰማም አወያዮቹ ውይይቱ መጠናቀቁን ገልፀዋል፡፡ ተሳታፊዎችም የተቃውሞ ድምፅ እያሰሙ ሲወጡ ተስተውሏል፡፡ በተለይ አንድ አዛውንት "ደርግ የመሬትና የቤት ባለቤት አደረገን፣ ኢህአዴግ ቀማን" እያሉ በብስጭት እየተናገሩ ሲወጡ ተስተውሏል፡፡

በተመሳሳይም በወረዳ 11 በነበረው ውይይት ተሳታፊው ህዝብ ከፍተኛ ተቃውሞ ያሰማ ሲሆን "መጀመሪያ ያላወያያችሁትን ካፀደቃችሁ በኋላ ምን እንድናደርግ ነው የምታወያዩን? እስከመቼስ በጠብመንጃ ትገዙናላችሁ? ከዚህ በኋላ ምን ቀረን? ሀገርም ዜግነትም የለን፣ እያየን ግን መሬታችንን አንቀማም፣ አሁንስ አበዛችሁት ትዕግስታችን ተሟጧል" ሲሉ የተደመጠ ሲሆን ከዚያም በብስጭት ህዝቡም ውይይቱን አቋርጦ ወጥቷል፡፡

በቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 13 በነበረው ውይይትም ከህዝቡ ተመሳሳይ ተቃውሞ የተሰማ ሲሆን በተለይ የአንድነት ፓርቲ ከፍተኛ አመራር ወደ ውይይቱ ሲገቡ ህዝቡ የእንኳን ደህና መጡ ከፍተኛ ጭብጨባ በማሰማት ቦታ ሊጧቸው ሲረባረቡ የታየ ሲሆን አወያዮችም በወቅቱ መደናገጥ ታይቶባቸዋል፡፡ ከተሳታፊዎችም "ይህ የሊዝ አዋጅ በህገ መንግስቱ የተቀመጠውን የህዝቡን ሉዓላዊነት ይጥሳል፣ ይዳፈራል፣ አዋጁ ከመፅደቁ በፊት ወረውን የወከሉት የፓርላማ አባል ለምን አላወያዩንም? አዋጁ የተድበሰበሰና ግልፅነት የጐደለው ነው፣ አወያዮች የምታወሩትና አዋጁ አይገናኝም፣ ህዝብ ቀድሞ ሊወያይበት ሲገባ ካፀደቃችሁ በኋላ ምን እንድናደርግ ነው?" የሚሉ ሐሳቦችና ጥያቄዎች የተደመጡ ሲሆን ከአወያዮችም መልስ እየተሰጠ ሳለ አጥጋቢ መልስ አልተሰጠንም በማለት ተሳታፊዎች ውይይቱን አቋርጠው ወጥተዋል፡፡

የወረዳው ነዋሪ የሆኑት የአንድነት ከፍተኛ አመራር በውይይቱ እንዲሳተፍ ለሎች ጐረቤቶቻቸው ሲሰጥ ለእሳቸው እንዳልደረሳቸውና የወረዳው ነዋሪ ውይይቱ ላይ መገኘት አለብዎት ብለው እንደጋበዟቸው ገልፀውልናል፡፡ የተለያዩ አወያዮችም አዋጁ ከመፅደቁ በፊት ውይይት ባለመደረጉ መንግስት ይቅርታ ይጠይቃል፤ ግለ ሂስም እናደርጋለን ሲሉ የተደመጡም እንዳሉ ለመታዘብ ችለናል፡፡ በተመሳሳይም በልደታ ክፍለ ከተማ ወረዳ 9 ሜክሲኮ በሚገኘው ተግባረ ዕድ አዳራሽ ውይይት የተካሄደ ሲሆን ተሳታፊዎችም "ደርግ በገጠር 10 ሄክታር በከተማ ለሚኖሩት ደግሞ 500 ካሬ ሜትር ቦታ የዜግነት መብታችሁ ነው ብሎ በነፃ ሰጥቶ ነበር፡፡ እናንተ ግን የህዝቡን መሬት መንጠቅ ነው እንጂ ከኢህአዴግ አመራሮች ውጭ የዜግነት መብቱ የሆነውን መሬት ያገኘ ሰው የለም፤ አዋጁ ከፀደቀ በኋላ ለምን መወያየት አስፈለገ?" ሲሉ ጥያቄ እንዳነሱ ተገልፃዕል፡፡ በመጨረሻም ውይይቱን የሚመሩ ባለስልጣናት አስቀድመው ፅፈው የመጡትን የህዝቡ የድጋፍ አቋም መግለጫ ብለው ሊያነቡ ሲሉ ህዝቡ ከፍተኛ ተቃውሞ በማሰማት ውይይቱን ረግጦ መውጣቱ ተጠቁሟል፡፡

በጉለሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 9 ደግሞ ለውይይቱ የመጡ ሰዎችን ሲገቡ አስፈርመው ውይይቱ ሳይካሄድ ተጠናቋል ተብሎ ህዝቡ መመለሱን የወረዳው ነዋሪና ሊወያዩ የሄዱ ሰዎች የተሰማቸውን ቅሬታ ገልፀዋል፡፡

በኮልፌ ቀራኒዮ ክፍለ ከተማ ልዩ ስፍራው ካራቆሬ በሚባል በወረዳ 3 በነበረው ውይይት ደግሞ በከፍተኛ ታቃውሞና ውዝግብ ህዝቡ ውይይቱን ረግጦ መውጣቱ ተገልፃዕል፡፡


ከተስፋዬ ጋንታ

# ስንት ዓመት በአምባገነንነትና በብልጣብልጥነት መግዛት ይቻል ይሆን?

አምባገነኖች ወደ ስልጣን የሚመጡት የህዝብን ቋንቋ እየተናገሩ ነው፡፡ የአገርንና የህዝብን ችግር መነሻ አድርገው የህዝብ ተቆርቋሪ ለህዝብ መብትና ጥቅም የተቆጩ መስለው ይጮሐሉ፡፡ የህዝብን መብትና ጥቅም ለማስጠበቅ እንደሚታገሉ ህዝብ ከጐናቸው እንዲቆም ይለፍፋሉ፡፡ ሥልጣኑን ከያዙ በኋላ ህዝቡን ይረሱታል፡፡ ተገልብጠው ህዝብን ይሳደባሉ፡፡ በመሳደብ ሳያቆሙ ያስራሉ ይደበድባሉ ይገላሉ፡፡ የአገርንና የህዝብን ሀብት ለግላቸው ይዘርፋሉ ያዘርፋሉ፡፡ በተለያየ ዘመን በዓለማችን ላይ የተነሱት አምባገነኖች ያስተማሩን ይህንኑ ነው፡፡

በአገራችን የተንሰራፋው የኢህአዴግ አምባገነናዊ መንግስትም እየፈፀመ ያለው ይህንኑ ነው፡፡ አርቴፊሻል የዴሞክራሲያዊ ተቋማትን በማቋቋም እጅግ አደገኛ የሆኑ የአፈናና የሰብአዊ መብት ረገጣ ተቋማትን ሲገነባ ቆይቷል፡፡ የህዝብን ሀብት እየነጠቀ ወደ ተለያዩ የኢህአዴግ ኩባንያዎች ለኢህአዴግ አባላት ያድላል፡፡ ዜጐችን ከመኖሪያና ከሥራቸው እያፈናቀለ ለረሃብ ለቤት ችግርና ለእርዛት ዳርጓል፡፡ ህገ መንግስቱን ተማምነው ሥርዓቱን በህጋዊና ሠላማዊ መንገድ የሚታገሉ የሠላም አርበኞችና ነፃ ጋዜጠኞች እጣ ፈንታቸው በፈጠረ ክስና በማስገደድና በማስፈራራት ምስክሮች የሚሰጡትን ቃል እያየን ነው፡፡

አምባገነኖች የሚያደምጡት ራሳቸውን ነው፡፡ ለአገርና ለህዝብ የሚጐዳ ተግባራቸው ሁሉ ለሥልጣናቸውና ሀብት ለመሰብሰብ እስከ ጠቀማቸው ድረስ ቅዱስ ነው፡፡

ማሰርም፣ መግደልም፣ ማስራብ እና ቤት ማሳጣት እርዛት መፍጠር ለአምባገነኖች ምናቸውም አይደለም፡፡ የህዝብ እንባና ሮሮ አያስበረግጋቸውም፡፡ እንዲያውም የበለጠ ልባቸውን ያደነድናቸዋል፡፡ ትናንት የሚናገሩት የህዝብ ቃል ሥልጣን ከያዙ በኋላ አያውቁትም፡፡ ኢዲያሚን ዳዳ፣ ቦካሳ፣ ጋዳፊ ያሳዩን ይህንኑ ነው፡፡ ተቃዋሚዎቻቸውን ተቺዎቻቸውን አስረዋል፣ ገለዋል፡፡ ህዝብን ይሳደባሉ፡፡ እነሱ ያሉትን ያልተቀበሉ ሁሉ በእነሱ ሚዛን ወንጀለኞች ናቸው፡፡ የኢህአዴግ መሪዎችም የሚፈጽሙት ይህንኑ ነው፡፡ ዛሬ በየወረዳው በየቀበሌው የተንሰራፋው አስተዳደር ፍትሐዊነት የጐደለው ነው፡፡ ህዝብ የሚያውቃቸው የህዝብ አስተዳዳሪዎች ከየት ተሹመው እንደሚመጡም አይታወቅም፡፡

ተልዕኮአቸው የህዝብ ጥያቄን መፍታት አይደለም፡፡ የአፈና ሥራ መሥራት እና ዝርፊያ ማከናወን ነው፡፡ እያንዳንዱን ጉዳይ የሚመለከቱት ከአገርና ከህዝብ ጥቅም ሳይሆን ከኢህአዴግ ሥልጣንና ከግል ጥቅማቸው አንፃር ነው፡፡ የኢህአዴግ ሠላም ህሊናን ለኢህአዴግ ዘረኛ አስተዳደር፣ ለኢህአዴግ ሙስና አስተዳደር፤ ለኢህአዴግ ኢ-ዴሞክራሲዊና ኢ-ሰብአዊ አስተዳደር፤ ለኢህአዴግ ፍርደገምድል ዳኝነት፣ ለኢህአዴግ ተቋማዊ ዝርፊያ አሚን ብሎ መገዛት ነው፡፡ ዛሬ በኢትዮጵያ ህጋዊና ሠላማዊ ሰው ነው ለመባል የኢህአዴግን ወንጀል ልማት አድርጐ መቀበል ነው፡፡

ኢህአዴግ የህዝብ ጥያቄን ሁሉ ጊዜ በብልጣብልጥነትና በአምባገነናዊ የአፈና ሥልት ማለፍ ይፈልጋል፡፡ ግን እስከመቼ? ስንት ዓመት ዜጐችን ማታለል ይፈልጋል፡፡ 20 ዓመት ሙሉ በጠብመንጃ ተገዝተናል፣ 20 ዓመት ሙሉ በሐሰት ፕሮፓጋንዳ ነፍዘናል፡፡ ይህ አልበቃ ብሏቸው ሌላ 40 ዓመት እንገዛችኋለን እያሉን ነው፡፡ ምኞታቸው ቀላል አይደለም፡፡ ዴሞክራሲ ህገ መንግስት እነሱ ዘንድ ትርጉም የሚሰጣቸው ለመድረክ ማድመቂያ ለወንበራቸው ማስጠበቂያ ብቻ ነው፡፡ ሥልጣናቸው የሚመጣው ከኮሮጆ እንዳልነበረ ሁሉ ወደ ፊትም ከኮሮጆ እንዳንጠብቅ እየነገሩን ነው፡፡ ማንኛውም ሰው ሰው በመሆኑ የማይደፈርና የማይገሰስ መብት አለው የሚለው ህገ መንግስት አንቀጽ 14 የአይን ቀለሙ እስካላማራቸው ድረስ የኢህአዴግ ሎሌዎች ያሻቸውን ማድረግ ይችላሉ፡፡

መፍትሔው አንድ ነገር ብቻ ነው፡፡ መላውን የአገሪቱን ህብረተሰብ ነፃነቱ እንዲያስከብር ማደራጀት ነው፡፡ ህጋዊና ሠላማዊ ትግል ለድል እንደሚያበቃ ማመን ነው፡፡ መብትንና ጥቅምን ራስ እንጂ ማንም ሊያስከብር አይችልም፡፡ የትም አገር መንግስት ዴሞክራሲን ገንብቶ አያውቅም፡፡ ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብት በህዝብ ትግል ይከበራል፡፡ ከአምባገነንና ከብልጣብልጥ ድርጅት መጠበቅም አይገባም፡፡ ዘላለም በአባገነንነትና በብልጣብልጥነት አገር አይመራም፡፡


ከሙሉጌታ በሪሁን
/የሕግ ባለሙያና ጠበቃ/

# "ጾሮን ሲያታልሏት በመጫኛ ጣሏት!"

የከተማ ቦታ ይዞታን በተመለከተ ከሕዝብ ይዞታ አውጥቶ የመንግሥትን ባለርስትነት ለማረጋገጥ የታወጀው አዋጅ ሕዝብን በስፋት እያነጋገረ ነው፡፡ በመሠረቱ መንግሥት የተቋቋመው ሕዝብን በሁለንተናዊ መልኩ ሊጠብቅና ሊንከባከብ ነው፡፡ በሠለጠኑት ሀገራት መንግሥት የሕዝብን የበላይነትና የሥልጣን ባለቤትነት ያውቃል፤ በማወቁም መብቱንም ያከብራል፤ጥቅሙንም ይጠብቃል፡፡ በአፍሪካ ግን መንግሥት የሚገዛው በሕግ ሳይሆን በአፈሙዝ ነው፡፡ ሕዝብ የበታችና ተዋራጅ ነው፡፡ መንግሥት ግን የተከበረና የተፈራ ከመሆኑ የተነሳ የፈለገውን ማድረግ ይችላል፡፡ ዜግነትንም እስከ ማሳጣት ድረስ ይራመዳል፡፡ ያገራችን ተጨባጭ ሁኔታም ይህንን ሀቅ ቁልጭ አድርጎ የሚያሳይ ነው፡፡

ለዚህ ጽሑፍ መነሻ የሆነኝ በሀገራችን ከቅርብ ጊዜ ወዲህ እያንዳንዱን ዜጋ እየከነከነው ስላለው የሊዝ አዋጅ ጉዳይ እንደ ዜግነቴም፣እንደ ተበዳይነቴም የሚከተለውን መጣጥፍ ላንባቢያን ማቅረብ እወዳለሁ፡፡

ባለፈው ሕዳር ወር የአዲስ አበባ ሬዲዮና ቴሌቪዥን በአዘጋጀው ፕሮግራም ላይ የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ አቶ ኩማ ደመቅሳና የከተማ ልማት ሚንስትሩ አቶ መኩሪያ ኃይሌ መ/ቤቶቻቸውን በመወከል የከተማ ቦታ ከሕዝብ ባለይዞታነት ወጥቶ በመንግሥት ቁጥጥር ሥር መሆን አለበት ሲሉ የተከበሩ አቶ ግርማ ሰይፉና አቶ ሙሼ ሰሙ የከተማ ቦታ ይዞታ ረቂቅ አዋጅ የሕዝብን የይዞታ መብት የሚያሳጣና የሚጋፋ ነው በማለት አጥብቀው ተቃውመዋል፡፡ ሰሚ ግን አላገኙም፡፡

በመሠረቱ አዲስ አበባ የሚለውን መጠሪያ ከማግኘቷ በፊት በባላባቶች የዞታ ሥር እንደ ነበረች ብዙ ማስረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ ለምሳሌ የአፄ ምኒልክ ቤተ መንግሥትና አካባቢው የአቶ አዳ ዱላ የተባሉ አዛውንት ይዞታ እንደነበር ይነገራል፡፡ ንጉሠ ነገሥቱ ከእንጦጦ ወደታች መውረድ በፈለጉ ጊዜ ለነህ ባላባት በይዞታቸው ምትክ ዛሬ አሮጌው አይሮፕላን ማረፊያ 6 ጋሻ መሬት ተሰጥቷቸው እንደነበር ማስረጃ ማቅረብ ይቻላል፡፡ ከዚህ በኋላ ንጉሠ ነገሥቱ ለራሳቸውና ለደጃዝማቾቻቸው እያከፋፈሉ በመሥጠት ለኗሪዎቹ ደግሞ በመትኩ ሌላ ትክ እየተሰጠ ቀስበቀስ አዲስ አበባ ያሁኑን ቅርፅ ያዘች፡፡

መኳንንቱ እየተመሩ ለያዙት ይዞታም ዘመኑና ጊዜው በሚፈቅደው መሠረት ለመንግሥት ግብር ይገብሩ እንደነበር ያሁኖቹም ገዥዎች ይጠፉቸዋል ወይንም አያውቁትም ለማለት ያስቸግራል፤ይህ የሚያመለክተንም ሕዝብ ለይዞታው ማረጋገጫ ለመንግሥት ግብር ይገብራል፤ ይህም መብቱም ነው፡፡ ግዴታውም ነው፡፡ መንግሥት በበኩሉ ከሕዝብ የመሬት ግብር በመሰብሰብ ለተለያዩ ግዳጆች ያውላል፡፡ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ያለው ወግና ሥርዓት የተጠቀሰውን ይመስል ነበር፡፡ የዜግነት ማረጋገጫና የአገር ትርጉሙም ይህ ነው፡፡

በ1928 ዓ.ም ፋሽስት ኢጣሊያ ኢትዮጵያን ከተቆጣጠረች በኋላ ዋና መቀመጫዋን አዲስ አበባ ማድረጓ የሚታወቅ ነው፡፡ በመሆኑም መርካቶንና የመርካቶዙሪያእንደሮማከተማየተዋበችለማድረግ "አዲስ ከተማ" ብሎ በመሰየም ባለይዞታዎችን ያላንዳች የካሣ ክፍያ እያስለቀቀች ለባንዳዎችና ሶልዳቶዎች እንዲሁም አፍቃሪ ኢጣሊያኖች ሰጥታ ነበር፡፡ ዳሩ ግን እድሜ ላርበኞቻችን መስዋእትነት ኢጣሊያ ድል ሆና ቀ.ኃ/ሥላሴ ከስደት ተመልሰው ከሥልጣን ላይ ሲቀመጡ፡፡ "ይዞታህ ያላንዳች የካሣ ክፍያ በኢጣሊያ ተነጥቀህ የነበርክ ሁሉ የቀድሞ የይዞታ ማረጋገጫህን እያቀረብክ ወደ ቀድሞ ቦታህ እንድትመለስ አድርገናል" የሚል አዋጅ በማወጅ ይህንን የሚያጣራም ሐምሌ 16 ቀን 1933 ዓ.ም ኮሚቴ ተቋቁሞ ማስረጃቸውን እያቀረቡና እየተጣራና እየተመረመረ ያለአግባብ የተነጠቁ ሁሉ ያለ ግምት ቦታቸውን እንደተረከቡ የእድሜ ባለደጎች ሁሉ የሚመሠክሩት ሀቅ ነው፡፡ ዛሬም ይኸ አቅምና ችሎታን ያላገናዘበ የሊዝ ዋጋ እየጫኑ መክፈል ያቃታቸውን ከይዞታቸው ላይ ማፈናቀል በኔ እምነት የዜግነትንም መብት ጭምር እንደመግፈፍ ይቆጠራል፡፡ ለመሆኑ የዜግነትና የኢትዮጵያዊነት መለኪያ ሚዛኑ ከእንግዲህ ምን ሊሆን ነው? ይህንን ደግሜ ደጋግሜ እጠይቃለሁ፡፡ በቂ የሆነ መልስም ካንድ ጉዳዩ ከሚመለከተው ከፍተኛ ባለሥልጣን እጠብቃለሁ፡፡ ይኸ ብዙሃኑን ሕዝብ እየነቀሉና ከኖረበት ይዞታው እያስለቀቁ በመትኩ ጥቂት ደጋፊዎችን መትከል ለጊዜው ደስ ሊያሰኝና ጥቅምም ሊያስገኝ ይችል ይሆናል? አርቆ ሊያስጉዘን ግን አይችልም፡፡ ከላይ የጠቀስኩትን መሳሌ ሊያስከትል የሚችል ርምጃ ነው እየተወሰደ ያለው፡፡ ያዘነም የሚደሰትበት፣የተደሰተም የሚከፋበት ጊዜ ወደ ፊት ርቀን ሣንሄድ ሊመጣ ይችላል፡፡ የሚበጀው መንግሥት እንደ መንግሥትነቱ ለዜጎቹ መጨነቅ እንጂ የገቢ መንጭ ሊያስገኝልኝ ይችላል በማለት ዜጎችን ማስጨነቅና ማበሣጨት ተገቢና የዘለቄታ መፍትሄ ሊሆን አይችልም፡፡

ውድ ወገኖች የሊዚ ማነቆ ካነቃቸው መካከል አንዱ ነኝ፡፡ ከአምሳ ዓመት በላይ ገዝቸ በስሜ ካርታ አስነስቸ እየገበርኩ ቤት ሰርቸ ልጆች አፍርቸ፣ የኖርኩበትን ቦታ በሊዝ መግዛት አለብህ ተብዬ በግድ ውል ገብቻለሁ፡፡ ገንዘቡን ከየት አንደማመጣው ግን እግዜር ይወቅ፡፡

አቶ መለስ ባንድ ወቅት "የአዲስ አበባ ከተማ ኗሪ አሁን ባለው የግብር አከፋፈል ሁኔታ መቀጠል አይችልም፡፡ የግብር አከፋፈል ለውጥ ይዘረጋል፡፡ ያንዬ መክፈል ያቃታቸው ይዞታቸውን እያስረከቡ ይሄዳሉ" ማለታቸው አይዘነጋም፡፡ አሁን እየተተገበረ ያለው የሳቸው ቃል ለመሆኑ ጥርጥር የለውም፡፡ በሕዝብ ላይ በገጠርም ሆነ በከተማ በየምክንያቱ የሚጣለው ግብርና ታክስ የዜጎችን አቅመና ችሎታ ያመጣጠነና ያመዛዘነ አይደለም፡፡ የምንግደለሽና እጅግ አድርጎ ኃላፊነት የጎደለው ነው፡፡ የዚህ ማስረጃው በገጠር የማዳበሪያ እዳ ሲሆን በከተማ ደግሞ በቅርብ ጊዜ የወጣው የሊዝ አዋጅ አስጨናቂና ሱሪን ባንገት አውልቁ የሚል ነው፡፡

ገዥዎቻችን ግን በርእሴ ላይ ለመጥቀስ እንደሞከርኩት "ጾሮን ሲያታልሏት በመጫኛ ጣሏት" እንዲሉ "ግብር የምንጥለው ለልማት ነው፡፡" ይሉናል፡፡ ይህ እውነት ቢሆን ልማትን ማን ይጠላል? 20 ዓመታት ሙሉ የጠገብነው ግን የፕሮፖጋንዳ ጋጋታ እንጂ የልማት ትሩፋት አይደለም፡፡ ተከዜን ጨምሮ ያልተገደበ የኤሌትሪክ ማመንጫ የለም፡፡ እኛ ግን "ሺ ቢታለብ ያው በገሌ" እንዳለችው ድመት ከፈረቃ አልዳንም፡፡ ምናልባት ጅቡቲና ኬንያ ተሳክቶላቸው እንደሆነ አላውቅም፡፡ በግብርናውም ቢሆን ከልመና አልተላቀቅንም፡፡ በየዓመቱ የርሃብ ሠለባ ነን፡፡ ጠግበን የምናድረው የቃላት ጋጋታ ብቻ ነው፡፡

ወደ ራሴ ብሶት ልመለስ፡፡ አሁን በይዞታዬ ሥር ላለው ቦታዬ በ1961 ዓ.ም ካርታ ሳስነሳ የከፈልኩት ገንዘብ ብር 23.00 ነበር፡፡ ዛሬ የንጉሱ ዘመን ካርታ መለወጥ አለበት ተብዬ አዲሱን ካርታ ስወስድ የከፈልኩት ገንዘብ ብር አሥራ ስምንት ሺ አራት መቶ አምሳ ሰባት ብር ከ10 ማንቲም ነው (18,457.10) እዳው በዚሁ ቢበቃ ባልከፋ ነበር፡፡

የከተማ ልማት ሚንስትሩ አቶ መኩሪያ ኃይሌ "ከአዋጁ በፊት በይዞታቸው ላይ ቤት ሠርተው ማስረጃቸውን ካቀረቡ የቦታ ኪራይና የቤት ግብር እየከፈሉ በይዞታቸው ይቀጥላሉ" ነበር ያሉት፡፡ ይህ ንግግራቸው ግን አየር ላይ መክኖ፤ወይንም እሳቸው አለበለዚያም ሕዝብ ተንቆ በ1948 ዓ.ም የገዛሁትን ቦታና ሰገብርበት የኖርኩትን አቅመና ችሎታየ የማይመጥነውን የገዛ ቦታዬን በሊዝ ዋጋ ማለትም በሦስት መቶ ሺ ብር (300,000) ብር እንድገዛ ግዴታ ገብቻለሁ፡፡

ውድ አንባቢያን አስቀድሞ ትንቢት የተነገረበት በመጨረሻው ሰዓት የሚመጡት ጧት የተናገሩትን ማታ የማይደግሙ ወይንም የሚሽሩ በምላሳቸው ጡንቻ የሚኖሩ ናቸው የተባለው በመፈፀሙ ብዙም አልገረመኝም፡፡ የገረመኝና በእጅጉ ያዘንኩበት አባቴ ማይጨው ድረስ ዘምቶ ከኢጣሊያን ወራሪ ኃይል ጋር ተናንቆ ከፋኛም ቆስሎ ለኔ ለልጁ አገር አስከነ ሙሉ ክብሯ አስረክቦኝ ነበር፡፡ ያገር ትርጉሙም ይኸው ነበር፡፡ እኔ ለልጆቼ ግን ቤት የሚሰሩበት ክንድ መሬት እንኳን ማቆየት ላልችል ነው፡፡ አሁንም ደግሜ እጠይቃለሁ፡፡ አንድ ዜጋ እንዳቅሙ ጎጆ ቀልሶ የሚኖርባት ቁራጭ መሬት ከሌለው ሰው ነው ተብሎ የዚህች ሀገር ዜጋ ነው የሚባለው በምን ሁኔታ ነው? የቻይናዎችን፣የሕንዶችን፣የዐረቦችንና የቱርኮችን ያህል እንኳን እንዴት መብት እናጣለን?

አንድ መንግሥት ለሚያስተዳድረው ሕዝብ እንደ መልካም አባት ነው መቆጠር ያለበት፡፡ አንዱን ወገን ከፍ ሌላውን ዝቅ ወይንም አንዱን ልጅ ሌላውን የንጀራ ለጅ አድርጎ በክፉ ዐይንና በጥላቻ መመልከት የኋላ ኋላ መዘዙ የከፋ ነው የሚሆነው፡፡ መንግሥት ከሚያስተዳድረው ሕዝብ ጋር ሆድና ጀርባ ከሆነ ውጤቱ አያምርም፡፡ ኢሕአዴግ ቆመ ብሎ ደጋግሞ እንዲያስብ ጊዜው አላለቀበትም፡፡ ከቀዳማዊ ኃ/ሥላሴም ሆነ ከደርግ ውድቀት ብዙ የሚማራቸው ቁምነገሮች አሉት፡፡ እነዚህን ቁምነገሮች ሣይንቅ ሊጠቀምባቸው ይገባል፡፡ አባቴ ለኔ አገር አቆይቶልኛል፡፡ እኔም በተራዬ ለልጆቼ ቢያንስ ለኢትዮጵያዊነታቸው መገለጫ የምትሆን ቦታ ላቆያቸው በተገባኝ ነበር፤ግን አልሆነም፡፡ ይኸ መንግሥት ካፈርኩ አይመልሰኝ ካለ ችግሩ በምን መልኩ ሊፈታ እንደሚችል አላውቅም፡፡ በበኩሌም 300,000 ሺ ብር ከየት አግኝቼ ቦታዬን ማስቀረት እንደምችል ግራ ገብቶኛል፡፡ ለኔ ብዙም አልጨነቅም፤እድሜ ጠገብ አዛውንት ነኝ፡፡ የልጆቼ እጣ ፈንታ ግን ያሳስበኛል፡፡ አገር ቢቀር ትንሽ ቦታ የቤት መሥሪያ የማያቆይ አባት እንዴት አባት ሊባል ይችላል? የአገር አለኝ ትርጉሙስ ምን ሊባል ይችላል? የተፈጥሮ ሕጉም መሬት የሕዝብ እንጂ የመንግሥት ከቶ ሊሆን አይችልም፡፡ መንግሥትማ በሕዝብ የተመረጠ ወይንም የተወከለ መሪ ወይንም ሥርዓት አስከባሪ አስተዳዳሪ እንጂ ቋሚ ዘለዓለማዊ ባለመሆኑ ባለርስት ሊሆን አይችልም፡፡ የኛዎቹ ይህንን ነጠቃ ከየትኛው ዓለም እንዳመጡት አላውቅም፡፡ እግዚአብሔር ለገዥዎቻችን አስተዋይ ልብና አርቆ አሳቢ አእምሮ እንዲሰጣቸው ሁላችንም ትንሽ ትልቅ ሣንል እንፀልይ፡፡ ፈጣሪያችንን እንማፀን፤የሱ ዳኝነት ነውና የሚበልጠው ጧት ማታ እጆቻችንን ወደ ፈጣሪያችን ዘርግተን እንማፀን፡፡ በመጨረሻም እግዚአብሔር ኢትዮጵያን ይታደጋት፡፡

# ሀገር በፓርቲ መተዳደሪያ ደንብ አይመራም



አርምዴ ሽፈራው

ህገ-መንግሥቱን የማስጠበቅ አደራ ከሕዝብ ተሰጥቶኛል" የሚል መንግሥት ሽልማት በሰጠው ሕዝብና ከሕገ መንግሥቱ በላይ ሊሆን አይችልም፡፡

ኢትዮጵያውያንን እጅግ የከፋ የድህነት አረንቋ ውስጥ በከተተ አስተዳደር ላይ አየፈረጠመ የመጣው የመንግሥት ጡንቻ በአፈና ተግባር በሚያፈሰው መዋዕለ ንዋይ ላይ ያቆጠቆጡ የአፈና ሠራዊቶች ዘመናትን የተሻገረ የኢትዮጳያዊነትን መልካም ባህል አብሮ መኖር አንዱ የሌላውን ስሜት መጋራት መተማመን - - -ወዘተ እንደ ሰደድ እሳት በመብላት እርስ በርሱ በመጠራጠርና በመፈራራት እንዲኖር እያንዳንዱን ዜጋ በዚህ አፈና መዋቅር ውስጥ ለማስገባት ሲባል የሚደርሰው ወከባና እንግልት የሕገ መንግሥቱን መጣስ ያመለክታል፡፡

ሥልጣን በሕዝብ ተሰጥቶኛል የሚለው መንግሥት የመንግሥትን ሥልጣን አለአግባብ በፓርቲ ሥራ አገልግሎት ካላዋለው በስተቀር እያንዳንዱ ዜጋ በሀገሩ ላይ ያለ አድልዎ መሥራት በየትም ቦታ መንቀሳቀስ ማንኛውንም ማሕበራዊ አገልግሎት የማግኘትና የመስጠት የሕግ ጥበቃና ከለላ የማግኘት ሙሉ መብት ያለው ሲሆን ዛሬ ኢትዮጵያ በዘመንዋ ሁሉ አይታው በማታውቀው ሁኔታ ሕዝብ በፓርቲ ደንብና መተዳደሪያ እንዲገዛ የሕገ መንግሥት መብቱን በግልፅ እንዲገፈፍ ሆኗል:
:

ኢትዮጵያዊነት የማሕበረሰብ ኮራፕሽን በወለዳቸው ጥቂት ሞራል አልባ ዜጐች የሚለካ ሳይሆን በነፃነቱ ቀናኢ የሆነ ከራሱ አልፎ በፕላኔታችን ላይ ለሌሎች ነፃነትና ሠላም የሚቆም በመልካም ባህሉ የሚገለፅ ነፃ ሕዝብ ነው፡፡

"የአባይን ልጅ ውኃ ጠማው" እንደሚባለው አይነት ከ60 ዓመት በፊት የኰርያን ዕጣ ፈንታ የወሰነውን ወሳኝ ጦርነት ነፃዎቹ ኢትዮጳያውያን ነፃ ሀገርና ነፃ ሕዝብ ለማትረፍ ባደረጉት ተጋድሎ በድል ተወጥተዋል፡፡ ነገር ግን የሰሜኑ ክፍል ዕጣፈንታ አባቶች ከተዋጉበት በተቃራኒ በሀገራችንም ዛሬ ወያኔ ኢህአዴግ በፓርቲው የአፈናመዋቅር ያልታሰረን ሁሉ በጠላትነት ፈርጆ በገዛ ሀገሩ ላይ ሠላም ለማሳጣትና በሥሩ የገቡትን ለምቾቱ የመከራ ቀንበር ጭኖ ለመግዛት ሕገ መንግሥት አላገደውም፡፡ ለዚህም ብዙ እውነታዎችን በተነፃፃሪ ማንሳት ይቻላል፡፡

ከዓመታት በፊት የኢትዮ ኤርትራ ግጭት በፍርድ ውሳኔ ተሰጥቶት ጉዳዩን እንደ ባለመብት የሚከታተለው መንግሥትም ሕዝብም እኩል ተሳስተው ተፈረዱልን በሚል መንፈስ የአዲስ አበባ ከተማ በመኪና ጡሩምባ ድምፅ ስትናወጥ መዋሏና ማምሸቷ አይዘነጋም፤በሀገር ጉዳይ እኛም እንደ እናንተ ምንም አላወቅንም ቢሉን አስበው ከነበር በእያንዳንዱ ዜጋ ሕሊና ውስጥ እየመራን ያለው ማነው የሚል ጥያቄን አጭሮ አልፏል፡፡

ቢቢሲ ዎርልድ ኒውስ ወያኔ ኢህአዴግ ጫካ እያለ በይዞታው ሥር በነበረ በድርቅ በተጠቃ የሕብረተሰብ ክፍል የመጣውን የእርዳታ ገንዘብ ለመሣሪያ መግዣ አውሎታል የሚለውን የሚያመላክት ሲሆን በሌላ በኩል ወያኔ ኢህአደግ የተወነጀለበት 100 ሚሊዮን ዶላር መንግሥት ሆኖ ሀገር እየመራ ባለበት በዚህ ተከታታይ 20 ዓመታት ውስጥ ከዚህች ጉስቋላ ሀገር ሾልኮ የወጣውን የ11.7 ቢሊዮን ዶላር ዜና ቢያንስ ሁኔታውን መርጦኛል ለሚለው ሕዝብ ለመግለፅ ጆሮ ያለው አልመሰለውም፡፡ ማመን ወይንም ማስተባበል ግን ይጠበቅበት ነበር፡፡

ይህ ትልቅ አህዝ ያለው የገንዘብ መጠን የአፄው መንግሥት በዘመናቸው ሁሉ ዘረፉት ከተባለውና ከደርግ ጋር ሲካሰሱበት ከነበረው ጋር በንፅፅር በጊዜ ፈጥነት ሲለካ የአሁኑ በሃያ እጥፍ ፍጥነት በተቀላጠፈ ሙስና መብለጡን ያሳየናል፡፡ እናም ይህ እጅግ ታላቅ ጉዳይ እንዳይናገር ታፍኖ በድህነት አረንቋ ውስጥ ለሚማቅቅ ሕዝብ በቀላሉ የሚታለፍ አይደለም፡፡ ጠመንጃው በአጄ ነው ካልሆነ በስተቀር መንግሥት አስቾኳይ መልስ ሊሠጥበት ይገባል፡ ፡ መቸም ይሁን መች ተረስቶና ተዳፍኖ የሚቀር ጉዳይ አይደለም፡፡ ይህ የተዘረፈ የገንዘብ መጠን በተከሰሱበት ወንጀል ፍ/ቤት ጥፋተኛ መሆናቸውን ሳይወስን በአኬልዳማ ቅንብር ለሕብረተሰቡ ወንጀለኛ አድርጐ ለማቅረብ በመንግሥት ሚዲያ ላይ ከተሠራው የሕገ መንግሥት ጠሰት በላይ እጅግ በጣም የበለጠ አንገብጋቢ ነው፡፡ በሙስና በንቅዘት የተዘፈቁ አባላቱን አቅፎና ደግፎ የያዘ መንግሥት በማንኛውም መመዘኛ ቆይቶ ካድሬዎችን በፊልም ቀርጾ ከማቅረብ ከቶ ሊዘባበትብን አይችልም፡፡ የሞራል ብቃትም የለውም፡፡ በዚህ ትልቅ ገንዘብ በሙስና ከሀገር መውጣት ዛሬ ለመግለፅ እንደሚታየው የብዙ ኢትዮጵያውያን ድህነት አመላካች ነው፡፡ ብዙዎች በመልካም አስተዳደር እጦት ኑሮአቸው ተናግቷል፤ለውድቀት ተዳርገዋል፤በተጨማሪም ነፃ ዜጋን በአፈና ኔትዎርክ ውስጥ ለማስገባት የዚህን ድሃ ሕዝብ አቅም ከመጠቀም በላይ የዚህን ገንዘብ አወጣጥና መድርሻ ማወቅ አንገብጋቢ ነው፡፡

እንደ ነፃ ዜጋና እንደባለመብት ስናስብ ይህ ገንዘብ የ80 ሚሊዮን የኢትዮጵያ ሕዝብ ሀብት የሆነ ትልቅ ገንዘብ ነው፡፡ እያንዳንዱ በሙስና ከሀገር በሚወጣ ብር ሕዝብ በመከራው ይከፍለዋል፤እያንዳንዱ ኢትዮጳያዊ ለዚህ ሾልኮ ለወጣ ገንዘብ /አንድ ቢሊዮን ሰባ ሺ ዶላር/ በነፍስ ወከፍ በጉስቁለናችን እንከፍለዋልን፤ታዲያ ለዚህ ቢያንስ መልስ ሊሰጠን የሚችለው አካል ማነው? ወይስ ይህ ነፃ የነበረ ሕዝብ ለእንደዚህ አይነት አሳፋሪ ዘረፋ ስኬት ሲባል በመሸማቀቅና በመከራ ውስጥ እንዲያልፍ ስውር ፍርድ ተበይኖበታል?

ኢትዮጵያን በታሪኳ ገብታ ከማታውቅበት ከዚህ ክፉ አሠራር እግዚአብሔር ያውጣት

አሜን!!

# የኢትዮጵያ ሕዝብ ቆራጥ መሪ ካገኘ በቆራጥነት ይታገላል



ከስንታየሁ ቸኮል

ኢትዮጵያን በቅርበት የሚያውቋት ሰዎች ስለዚች ሀገር ብትጠይቋቸው የሚሰጧችሁ መልስ ኢትዮጵያውያን በቀኝ አንገዛም ብለው በዱር በገደሉ የወደቁ ጀግኖች ልጆች የፈለቁባት ሀገር መሆኗን ሊነግቹሁ ይችላሉ፡፡ እንዲሁም ኢትዮጵያ የ3 ሺህ ዘመን ታሪክ ባለቤት መሆኗ እና የሉሲ፣ የአክሱም፣ የጎንደር፣ ላሊበላ፣ ሶፍመር ወዘተ እየደረደሩ ሊጠቅሱ ይችላሉ፡፡ ግራ የተጋባ ውስጠ ወይራ የሆነ ፖለቲካ እንዳለንም ታሪክ እየቆጠሩ በደንብ ይነግሩናል፡፡ ከላይ ታዘልን ሳይሆን በእኛው ክፋት ያመጣነው የዜጎቻችን እራህብተኛን ቁልጭ አድርገው በእስታስቲክስ የተደገፈ ማስረጃ ይዘው የየአመቱን ዘርዝረው ይነግሩናል፡፡ ይሄ ልዩ ማፈሪያችን ቢሆንም የሚያፍር መሪ በሌለበት አገር የምንኖር ዜጋ መሆናችንን ስለሚገነዘቡ ብዙም ላይገርማቸው ይችላል፡፡ የሆነ ሆኖ በ97 ዓ.ም ላይ ግን አዲስ ነገር ሆነ፡፡ ዕርዳታ ጠያቂ ሳይሆን ያዩት የዴሞክራሲ ያለህ ብሎ ቁርጠኝነቱን ያሳየ ህዝብ እንዳላት ያወቁበት ሀገር መሆኗን ተገነዘቡ፡፡ ይህም ማጋነን አይደለም፡፡ ብቻ ምን ያደርጋል ጥርስን ነክሶ ልብን ከማቁሰል በቀር ማሰቡ ያሳምማል፡፡ መቼም በወቅቱ በሕዝባችን ዘንድ ያስከተለው ክፉም ይሁን ጥሩ ቀላል የማይባል ቢሆንም ጅማሬው ጥሩ መስሎ መደምደሚያው ግን የማይረሳ ጥቁር ጠባሳ ሆኖ ያለፈበት ጊዜ መሆኑ ማንም ሰው የሚያውቀው እውነታ ነው፡፡ ከዚያ ወዲህ ቢያንስ የተሻለ የፖለቲካ ምህዋር ተፈጥሮ ማየት የተራብንበት ጊዜ ላይ መድረሳችን እማኝ የሚያስፈልገው ጉዳይ አይደለም፡ ፡ በወቅቱ ለዴሞክራሲ ግንባታ እና ለለውጥ ቆርጦ የተነሳ ሕዝብ መኖሩ ምን ያህል የማይረሳ ትዝታ በሕዝብ ዘንድ እንደነበረ ለመገመት ነብይ መሆን አያስፈልግም፡፡

ቀደም ካለ ከምርጫ 97 በፊት ጀምሮ ገዢው ፓርቲ ስልጣን ከያዘበት ጊዜ ጀምሮ "ተቃዋሚዎች ግማሽ መንገድ ከመጡ ግማሽ መንገድ ሄደን እንቀበላቸዋለን" በሚል ፈሊጥ ዴሞክራሲ መኖሩን ለማስመሰል እና እኔን ካልሆነ ሕዝብ ሙብቱ የት ድረስ እንደሆነ አያወቀውም በሚል የተቃዋሚው ጎራ አሰላለፍ ለመፈተሽ የተደረገ የፖለቲካ ዲስኩር እንደነበር ብዙ ሰዎች ያምኑበት ነበር፡፡ በዚህ የተነሳ ገዢው ስርዓት አንቀላፍቶ ባለበት ጊዜ በዛች ክፍተት ውስጥ የተቃውሞ የፖለቲካ እንቅስቃሴዎች የተሻለ እንዲሆን እና ትልቅ የፖለቲካ ፓርቲ መመስረት ምክንያት ሆኗል፡፡

ለዚህም ዋነኛው ተጠቃሽ ምርጫ 97 ነው፡፡

ምርጫ 97 ከተፈጠረ ስድስት ወራት ባላስቆጠረ ጊዜ የተቃዋሚዎችን ጥምረት የሚያበረታታ የፖለቲካ እንቅስቃሴ ለማየት አስችሎናል፡፡ በወቅቱም እንዲህ አይነት ፖለቲካዊ መነቃቃት እንዲፈጠር ከጅማሮው አንስቶ ሕዝባቸውን ከተኛበት እንዲነሳ ያስቻሉት ሀይሎች ለፖለቲካዊ ባሕላችን የማይረሱ ባለውለታዎቻችን ናቸው ብንል ሁላችንም የምንስማማበት እውነታ ነው፡፡ ለዚህም ሕዝቡ በውስጥም ይሁን በውጭ የሚያሳየው ፖለቲካዊ ትንቅንቅ ብሎም ጅምሩ እንዲበረታታና ትውልድ እንዲነቃቃ ያስቻሉ ባለውለታዎች ናቸው፡፡

በወቅቱ "ሕዝብ ድምፄ ይከበር" በማለቱ መሪዎቹ ለእስር ሲዳረጉ በሕዝብ ላይም አሳዛኝ ቅጣት ተፈፅሟል፡፡ ይኸውም እጅግ አሳዛኝ ቢያደርገውም ለሕዝብ አልዋጥለት ያለውና እስካሁን ድረስ እምነት ያሳጣው በወቅቱ መሪዎቹ አይሆኑ መሆን እና መሰነጣጠቅ ነው፡፡ በፖለቲካ መሪዎች ላይ ሕዝቡ ተስፋ እንዲቆርጥ ዋነኛ ምክንያት የሆነው፣ ከዚህ በኋላ በገዢው ስርዓት በኩል የተደረገው የፖለቲካ ምህዳሩን እንዲጠብ ቀንና ማታ መባዘኑ በሕዝብ ላይ አስተዳደራዊ ግድፈት እና ኢኮኖሚያዊ ዝቅጠት ውስጥ እንዲገባ ግፍ ተፈፅሞበታል፡፡ አሁንም ለምናየው የፖለቲካችን ውድቀት ዋናው ምክንያት ነው፡፡ ከዚህ በኋላ በኢትዮጵያ ውስጥ በሕግ የምንዳኝ የሚመስል ሳይሆን በመንግስት ሰማያት ስንገናኝ የምንዳኝ እስከሚመስል የአንድ ሰው ትንተና ህግ ሆኖ የሚወጣበት አገር ሆኗል፡፡

ከዚህ የተነሳ ከምርጫ 97 በኋላ የሚደረጉ ምርጫዎች እና የፖለቲካ ጨዋታዎች ተከታታይ የቴሌቪዥን ድራማዎች እየሆኑ መምጣታቸው ብዙ ምስክርነት የማያስፈልገው እውነታ ነው፡፡ ገዢው ስርዓት ከዚያ በኋላ ለሀገራችን እና ለሕዝባችን የሚጠቅሙ እውነታዎችን እና የቃላት ሐረጎችን በዚች ሀገር እንዲደርቅ በስርዓቱ በኩል የተሰሩ የቤት ስራዎች እንደነበሩ ብዙ ሰዎች የተስማሙበት እውነታ ነው፡፡ ለዴሞክራሲ ግንባታችን ጠቀሜታ አላቸው የሚባሉትን ተቋማት ከሰባዊ መብት እስከ ቤተ ክህነት ሁሉ እምነት ያሉትን እንደ ሀገር ለሕዝባቸው አሳቢ ከመሆን ይልቅ ለስርዓቱ ጥፋትና ስህተት ደጋፊና ደባቂ እስከመሆን ደርሰዋል፡፡ ይህንንም ታዝበናል፡፡ ታዲያ ከዚህ በኋላ በኢትዮጵያ ውስጥ ስርዓቱን ለመቃወም አይደለም ለመኖር ሰው በሀገሩ እንዳይችል ሆን ተብሎ የተሠራ በዚህም የተለያየ ሕጎች መውጣት ጀመሩ፤ ለገዥው ስርዓት በረከት ለሕዝብ ሴራ የሆኑ ሕጎችን በማውጣት ወደር የለሽ ጥፋት እየጠፋ ነው፡፡ ለዚህ ሁሉ ችግሮች ሕዝቡ የሚያታግለውና የሚታገልለት የፖለቲካ ድርጅት እና ነፃ ፕሬስ እንዲሁም የተለያየ ተቋሚት እንዳይኖሩ ከኖሩም እንዲደርቁ ትልቅ ደባ ተሰራባቸው፡፡ በዚህ ምክንያት ለሕዝባቸው ነፃነት የሚንገጫገጩ ጥቂት የፖለቲካ ድርጅቶች እና በጣት የሚቆጠሩ አንድና ሁለት የሆኑ ነፃ ፕሬስን ጠልፎ ለመጣል በማሰብ የውስጡ ትንታኔ ለተከሳሹም ለዳኛውም በማይገባ ፈሊጥ የሽብርተኝነት ሕግ ተብሎ ታወጀ፡፡ ከነዚህ ውጣ ውረዶች በኋላ በገዥው ስርዓት በኩል የምንግዜም አሸናፊነቱን ለማስመስከር እራሱን በመቆለል አውራና አውሬ መሆኑን ከመደስኮሩም በላይ ሕዝቡ እንዲፈራና አንገቱን ደፍቶ ግርምት ውስጥ ያስገባው የፖለቲካ ጨዋታዎች ላይ መልካቸውን ለውጠው ስማቸው እና እውቅናቸው የተቃዋሚ ፓርቲዎች የውስጥ ገፅታቸው የስርዓቱ አጋር ፓርቲዎች መፈጠራቸው ነበር፡፡ በዚህ የተነሳ ገዢው ስርዓት የዴሞክራሲ እና የመድበለ ስረዓታችን ያልሞተ ለማስመሰል የተወሰዱ የሞኝ ፈሊጥ ነበሩ፡፡ ሕዝቡ ከማንም በላይ ጠንቅቆ አዋቂ መሆኑ ግን ተዋንያኖቹ እንዲያፍሩ ግድ ሆኖባቸዋል፡፡ ይህ መሆኑ ግን በሕዝብ ዘንድ ተአማኒነት ያለው ጠንካራና ሕዝባዊ መሠረት ያለው የፖለቲካ ፓርቲ በአንድ ላይ በመሆን እንዳይፈጠር ትልቅ እንቅፋት ፈጥሯል፡፡ የት እንዳሉ እንኳን የማይታወቁ ድርጅታቸውና የሚመሩት መሪዎቹ በቅጡ እንኳን የማይታወቁ እንደ አሸን መፍላታቸው ከማስገረሙም በላይ የምን ንቅናቄ የእንትን ንቅናቄ እየተባለ የንቅናቄ ዘማሪ ድርጅቶች እንደሞሉን አይተናቸዋል፡፡ አንዳንድ የሚታወቁም የፖለቲካ ፓርቲዎችም ቢሆኑ በሕዝባቸው ዘንድ ይህ ነው የሚባል እንቅስቃሴ ሲያረጉም አይታዩም፡ ፡ ከራሳቸው የግል ጥቅምና ከእኔ በላይ አዋቂ በሚል እራስን ከመቆለል ይልቅ በእውነተኛ መንፈስ ለሀገርና ሕዝብ የቆመ የፖለቲካ ድርጅት ካለና ከሕዝብ ፊት የሚቆም ከሆነ ከየትኛውም ጊዜ በላይ የሚቆምለት ሕዝብ መኖሩ በአሁኑ ጊዜ እየሰማችሁት ያለው የሕዝብ ብሶት ችጋርና እርሀብ በቂ ምልክት ነው፡፡ ለዚህም ሕዝቡ ሀገሬን ጥዬ ስደት ከምሄድ ጠንካራ ሕዝባዊ ድርጅት እስከሚመጣለት አንገቱን ደፍቶ እየጠበቀ መሆኑ እማኝ የማያስፈልገው ሀቅ ነው፡፡ ካለፈው ድራማ ከሆነ ምርጫ ላይ ሕዝቡ ያሳየው ትንቅንቅ ፈሪና ጥቅመኛ መሪ እና ድርጅት ካልሆነ ፈሪ ሕዝብ አለመኖሩ የታየ እውነታ ነው፡፡

በዚህ የተነሳም ትላንት በኢትዮጵያ ፖለቲካ የታየው የፖለቲካ ፓርቲዎች የመሰባሰብ እና አንድ ላይ በመሆንና ሐሳብና ፕሮግራምን ከሕዝብ ነባራዊ ሁኔታ ጋር በማቀናጀት የሚደረግ የፖለቲካ ስርዓት መሆን እንዳለበት ከተደረጉት ተከታታይ የምርጫ ጨዋታ ውጤት እንዳለው የሚታመንበት እንደሆነ ብዙ የፖለቲካ ተንታኞች የሚስማሙበት ነው፡፡ ለዚህም ለምርጫ 2002 ስድስት የፖለቲካ ፓርቲዎች ቅንጅት ፈጥረው ለምርጫ ቢቀርቡም በወቅቱ ካለው ተጨባጭ የምርጫ ጊዜ እና ቀደም ሲል በተፈጠረው የፖለቲካ ፓርቲዎች ሽምጥ ውጊያ አብሮ ለመስራት እውነተኛ ፓርቲዎችን ለመለየት ችግር ውስጥ ተገብቶ የነበረበት ጊዜ ነበር፡፡ ከሞላ ጎደል ሕዝብም ካለፈው የፖለቲካ ፓርቲዎች እርስ በርስ መነሻሸምና መከፋፈል የተነሳ ስነ ልቦናው በመነካቱ የተነሳ በመድረክ ላይ እብዛም ተስፋ አልተጣለበትም ነበር፡፡ ይህውም መድረክ ውስጥ ብሄር ተኮርና ሕብረብሄር መሆናቸው አንድ ቢመስልም በዋናነት ግን በውስጡ ያሉቱ የፖለቲካ ድርጅቶችና መሪዎች ለራሳቸው ጥቅምና ፍላጎት ሲሉ እንዳለፈው ጊዜ ኋላ ላይ ቢከፋፈሉ ይችላሉ የሚል ስሜት መኖሩ የአደባባይ ሚስጥር አይደለም፡፡ ከዚህ በኋላም መድረክ በወሰዳቸው የውስጥ የቤት ስራዎች እርስ በእርስ ከመተዋወቅም በላይ ድርጅታዊ አቅሙንም አጠንክሮ ከቅንጅት ወደ ግንባር ቢያድግም ከበታች ካለው 2007 ከምርጫ በፊት ያሉትን የቤት ስራ በመጠቅለል ወደ ውህደት መሻገር እንዳለበት ምንም ጥያቄ የሚሰጠው ጉዳይ አይደለም፡፡ ይሄም እውነተኛ ከራስ በላይ ለሕዝብ ብሎ የሚታገል

ወደ 15 ዞሯል

# "ኢህአዴግ በልማታዊ መንግሥት" ሽፋን ፖለቲካዊ ሕጋዊነት ለማግኘት የሚያደርገው ጥረት እየከሸፈ ነው



በበለጠ ጉሹ ወ/ሚካኤል

ለአለፉት ሰባትና ስመንት ዓመታት የኢህአዴግ መንግሥት በኢትዮጵያ እያካሄደ ያለው የመሠረተ ልማት ግንባታ ምሁራንን ጭምር የሚያታልል ሆኖ አግኝቼዋለሁ፡፡ ለምሳሌ፣ፕ/ር በፈቃዱ ደግፌ ኢህአዴግ ይፋ ያደረገውን የ11.4 በመቶ ወይም የሁለት አኀዝ ዓመታዊ የኢኮኖሚ ዕድገት የተቀበሉት መሆናቸውን ሕዳር 30፣2004 በወጣችው "ፍትሕ ጋዜጣ" ላይ በሰጡት ቃለመጠይቅ ገልፀዋል፡፡ እነ አቶ ዘመዴነህ ንጋቱ /ብዙ ብር ያካበቱ ደግሞ ከዚያም አልፈው ኢህአዴግ ያስመዘገበው የኢኮኖሚ ዕድገት "ተአምራዊ" ነው እስከ ማለት ደርሰዋል፡፡ ሰፊው ሕዝብም በቴሌቪዥን የሚያቸው የሚያማምሩ መንገዶችና ትላልቅ ሕንፃ ያስደመሙት ይመስላል፡፡ አሁን ቀደደም የኔው ጓደኛ የሆነ "የተማረ ሰው"፣ "እየተራመድክበት የኢአዴግን ተጨባጭ የልማት ሥራ እንዴት ትጠራጠራለህ?" ነው ያለኝ፡፡ በእርግጠም፣የዚህን ሽጋ መንገድ መገንባትና እኔና ጓደኛዬም በሚያምረው እግረኛ መንገድ ላይ እየተጓዝንበት መሆኑን ልክድ አልችልም ነበር፡፡

በሌላ በኩል፣እንደ እኔ፣የኢህአደግን የልማት ሥራ የሚጠራጠሩ ብዙ ሰዎች አሉ /የታወቁ ኢትዮጵያውያን ምሁራንን ጨምሮ/፡፡ ለምሳሌ፣ዶ/ር አክሎግ ቢራራ አሁን ያለውን የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ "የብልጭልጭ ኢኮኖሚ" ብለውታል፡፡ መስታውት የበዛባቸውን ሕንፃዎች ጭምር ለመግለፅ የተጠቀሙበት ሐረግ ይመስለኛል፡፡ አቶ አክሎግ ልመንህ /አሜሪካ፣ቦስተን የሚኖሩ ኢትዮጵያዊ/ በተመሳሳይ አገላለፅ ኢኮኖሚውን "ብርቅርቅ ኢኮኖሚ" ብለው ገልፀውታል፡፡ አንዳንድ ኢትዮጵያውያን ኢኮኖሚስቶች ደግሞ የኢህአዴግን የኢኮኖሚ ልማትና ዕድገት መግለጫዎች ጨርሶ አይቀበሉም፡፡ በእነሱ አመለካከት፣ኢኮኖሚው እንኳን በአሥራ አንድ በመቶ ይቅርና ሕዝብ በሚያድግበት መጠንም /3 በመቶ ገደማ/ ማደጉን ይጠራጠራሉ፡፡

ዝርዝር ትንተና ውስጥ ከመግባታችን በፊት አንድ አስቀድሞ መታወቅ ያለበት ሐቅ አለ፡፡ ይኸውም፣የኢህአዴግ መንግሥት ይፋ የሚያደርጋቸው የኢኮኖሚ አኀዞችና መግለጫዎች ግማሽ እውነት፣ግማሽ ውሸት ከመሆናቸውም በላይ ለፕሮፖጋንዳ ፍጆታ በስፋት የሚጠቀምባቸው መሆኑ ነው፡፡ የእውነትና የውሸት ይዘታቸው ስብጥር የሚለያይ ቢሆንም፣የሚባለውን ጊዜ ያለፈበት የፕሮፖጋንዳ ስልትም ኢህአዴግ እንደሚጠቀም በሚገባ የታወቀ ነው፡፡ ለምሳሌ የሁለት አኀዝ ወይም የአሥራ አንድ በመቶ ዓመታዊ የኢኮኖሚ እድገት የዚህ ስልት ውጤት ይመስለኛል፡፡ ይህ አኀዝ ሐሰት ለመሆኑ የተለያዩ ማስረጃዎችን ማቅረብ ይቻላል፡፡ ለምሳሌ፣አንደኛው ማስረጃ ከኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ ጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርትን በየዓመቱ በአንድ ብር ለማሳደግ አምስት ብር የካፒታል ኢንቨስትመንት ያስፈልጋል ተብሎ ይገመታል፡፡ በቀላል አገላለፅ፣በየዓመቱ አንድ ብር የሚያወጣ ምርት ለማግኘት ዛሬ የአምስት ብር ኢንቨስትመንት ማድረግ ያስፈልጋል እንደማለት ነው፡፡ በዚህ መሠረት ጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርትን (GDP) በየዓመቱ በአሥራ አንድ በመቶ ለማሳደግ፣በየዓመቱ ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ መርት ሃምሳ አምስት በመቶው /55 በመቶ/ ካፒታል ኢንቨስትመንት መሆን ይኖርበታል፡፡ የን በተጨባጭ አኀዞች እንደሚከተለው ማሳየት የቻላል፡፡ ለምሳሌ፣ጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት መቶ ብር ቢሆንና፣ይህን በሚቀጠለው ዓመት ወደ አንድ መቶ አሥራ አንድ ብር /111 ብር/ ለማሳደግ፣በመጀመሪያው ዓመት ከነበረው 100 ብር ጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት 55 ብር ኢንቨስትመንት /የኢንቨስትመንት ዕቃዎች/ መሆን አለበት፡፡ በሚቀጠለው ዓመት የተገኘውን 111 ብር ጠቅላላ የሀገር ውስጥ መርት እንደገና በአሥራ አንድ በመቶ በማሳደግ ወደ 122.1 ብር ለማድረስ ከተፈለገ ደግሞ ከ111 ብር ጠቅላላ የሀገር ውስጥ መርት 61 ብር ኢንቨስትመንት መሆን ይኖርበታል፡፡ ይሁንና የኢህአደግ መንግሥት ራሱ የሚያወጣቸው አኀዞች ዓመታዊ ካፒታል ኢንቨስትመንት ከ55 በመቶ እጅግ በጣም ያነሰ መሆኑን ያሳያሉ፡፡ /ከ25 በመቶ በታች/፡፡

የአሥራ አንድ በመቶ ዓመታዊ ዕድገት ሐሰት ለመሆኑ ሌላው ማስረጃ የዕድገት መንጮች ትንተና (growth accounting) የሚባለው ነው፡፡ ዕድገቱን ለማስገኘት አራት አበይት ምንጮች አሉ፡፡ እነሱም ተጨማሪ የሰው ኃይል ስምሪት፣የታረሰው ተጨማሪ መሬት፣ከላይ የተገለፀው ተጨማሪ ካፒታል ኢንቨስትመንትና ከተሻሻለ ቴክኖሎጂና የሰው ኃይል ሥልጠና የሚገኝ የሥራ ቅልጥፍና (efficiency or productivity) ናቸው፡፡ በኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ (በተለይም በከተሞች አካባቢ) ሥራ አጥነት ከፍተኛ ደረጃ ሰለደረሰ፣ከተጨማሪ የሰው ኃይል ስምሪት የሚገኘው የምርት ዕድገት አነስተኛ ነው፡፡ መሬትን በተመለከተ፣የሚታረሰው ተጨማሪ መሬት ከሕዝብ ዕድገት /ከ3 በመቶ በታች/ በላይ እንደማይሆን ይገመታል፡፡ ከላይ እንደተጠቀሰው አሥራ አንድ በመቶ ዓመታዊ ዕድገት የሚያስገኝ ተጨማሪ ካፒታል ኢንቨስትመንት አልተደረገም፡፡ የተሻሻለ ቴክኖሎጂም ስለሌለ፣የህም ዋና መክንያት ሊሆን አይችልም፡፡ ስለዚህ፣እነዚህ አራት የዕድገት መንጮች አሥራ አንድ በመቶ ዕድገት ለማስገኘት በሚያስችል መጠን እንዳላደጉ ከተጨባጩ ሁኔታ መረዳት ስለሚቻል፣የዕድገት አኀዙ /11በመቶ/ ሐሰት መሆኑን በሚገባ ይጠቁማሉ፡፡ አንድ አሜሪካዊ ኢካኖሚስት / ካሊፎርኒያ ዩኒቨርስቲ/ ባደረገው ጥናት በዚህ መንገድ የዕድገቱን ምንጮች ከተነተነ በኋላ፣የደረሰበት ድምዳሜ አስገራሚ ነው፡፡ የዕድገቱ መንጮች ተጨማሪ የሰው ኃይል ስመሪት፣ካፒታል ኢንቨስትመንት እና የመሬት ልማት አለመሆናቸውን ካረጋገጠ በኋላ የሥራ ቅልጥፍናን እንደ ቀሪ መንስዔ ሲወስደው፣ የኢትዮጲያ የሥራ ቅልጥፍና ዕድገት (Productivity or efficiency growth) ከሠለጠኑት ሀገሮች የሥራ ቅልጥፍና ዕድገት እስከ አራት እጥፍ ስለበለጠበት፣የደረሰበት የመጨረሻ ድምዳሜ የአሥራ አንድ በመቶ ዓመታዊ ዕድገት እውነት ሊሆን እንደማይችል ነው፡፡

ሌላው ማስረጃ የሕዝቡ የኑሮ ደረጃ በተጨባጭ አለመሻሻል ነው፡፡ ጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት በመጠን (GDP in real terms) በአሥራ አንድ በመቶ ካደገ፣የሕዘብ ዕድገት ከ3 በመቶ በታች ሰለሆነ /2.7 በመቶ/ ዓመታዊ የነፍስ ወከፍ ምርት ዕድገት ቢያንስ 8.4 በመቶ /11.4-3/ መሆን ይገባው ነበር፡፡ ይህ ማለት እያንዳግዳችን የሚደርሰን፣ እንጀራ፣ ዳቦ፣ በርበሬ፣ ውሃ፣ ወተት፣ የትራንስፖርት አገልግሎት፣ የጤና አገልግሎት፣የመኖሪያ ቤት፣ወዘተ. በዓመት ቢያንስ በመጠን በስምንት በመቶ ገደማ ማደግ ነበረበት፡፡ ተጨባጩ ሐቅ ግን ከዚህ በጣም የተለየ ነው፡፡ በአሁኑ ጊዜ የመኖሪያ ቤት ብቻ ሳይሆን የዳቦ እጥረትም ተከስቷል፡፡ ምን ዳቦ ብቻ ውሃ የለም፤ በአዲስ አበባ የኤልክትሪክ መብራት በሳምንት ሶስት ጊዜ የሚቋረጠባቸው አካባቢዎች አሉ፡፡ የመኖሪያ ቤት ነገርማ ጨርሶ ባይነሳ ነው የሚሻለው፡፡ በአጠቃላይ፣የኢኮኖሚው በአሥራ አንድ በመቶ እያደገ የሕዝቡ የኑሮ ደረጃ የሚያሽቆለቁልበት ሁኔታ መሠረታዊ የኢኮኖሚ ሕግጋትን ስለሚቃረን፣ትክክል ያልሆኑት ሕግጋቱ ሳይሆኑ፣ኢህአዴግ በየዓመቱ ራሱ በሚቆጣጠራቸው ሚዲያ የሚለቃቸው የኢኮኖሚ ዕድገት አኀዞች ናቸው፡፡

ታዲያ በሀገራችን በዘመኑ ኢህአዴግ የኢኮኖሚ ዕድገት የለም ለማለት እንችላለን? ይህን ጥያቄ ከመመለሳችን በፊት ጉልህ ዕድገት የታየባቸውን የኢኮኖሚ ዘረፎች ለመዳሰስ እንሞክር፡፡ ጠቅላላ ምርትን በሶስት የምርት መደቦች መክፈል እንችላለን፡፡ እነዚህም የፍጆታ ዕቃዎችና አገልግሎቶች፣ የኢንቨስትመንት ዕቃዎችና የምርት ግብአት ዕቃዎች ናቸው፡፡ የምርት ግባዕት ዕቃዎች ስማቸው እንደሚያመለክተው፣የፍጆታና የኢንቨስትመንት ዕቃዎችንና አገልግሎቶችን ለማምረት ግብዓት ስለሚሆኑ ዋጋቸው /እሴታቸው/ በእነዚህ ሁለት የምርት መደቦች ውስጥ ይጠቃለላል፡፡ ስለዚህ፣እንደ እውነቱ ከሆነ፣የመርት መደቦች ሁለት ብቻ ናቸው/ማለትም የፍጆታ እና የኢንቨስትመንት ዕቃዎችና አገለግሎቶች፡፡ በሀገር ውስጥ የሚመረቱት እነዚህ ሁለት የምርት ዓይነቶች ሁለት ገበያዎች ላይ ይቀርባሉ፡፡ እነዚህም የሀገር ውስጥ ገበያ እና የውጭ ገበያ ናቸው፡፡ የኢህአዴግ መንግሥት በሚከተለው ልቅ የገንዘብ ፖሊሲ (loose monetary policy) ይህ ገንዘብ ማተምን ይጨምራል፣የዶላር የብር ምንዛሪ ከፍተኛ በመሆኑ /17.50 ብር ለአንድ ዶላር/ ነጋዴዎች በተለይ በሀገር ውስጥ የሚመረቱ የግብርና ውጤቶችን ለሀገር ውስጥ ገበያ ከማቅረብ የልቅ ወደ ውጪ መላክን ይመርጣሉ፤ ምክንያቱም በዶላር ምንዛሪ ከፍተኛነት ዋጋው በጣም ጥሩ ስለሆነ፡፡ በዚህም ምክንያት የግብርና ውጤቶች ዋጋ ከፍተኛ ከመሆኑም በላይ፣የሀገር ውስጠ ገበያ ላይ እጥረት ይታይባቸዋል፡፡ በተጨማሪም፣በሀገር ውስጥ ገበያ ላይ የሚቀርቡት የግብርና ውጤቶች ምራጭ /ጥራታቸው ዝቅተኛ የሆነ/ ናቸው፡፡ በመሆኑም ለምሳሌ ብጣሪ ቡናና የበሰበሰ ሙዝ ለሀገር ውስጥ ገበያ ማቅረብ እየተለመደ መጥቷል፡፡

የውጭ ሀገርና የሀገር ውስጥ ገበያ ዋጋ በጣም ከፍተኛ ሆኖም እንኳን ለገበያ የሚቀርቡት የግብርና ውጤቶች መጠን ዝቅተኛ ነው፡፡ በመሆኑም፣የግብርና ምርት በከፍተኛ መጠን እንዳላደገ ተጨባጭ ሁኔታው ያመለክታል፡፡ ስለዚህ የግብርና ምርት ለዓመታዊ አሥራ አንድ በመቶ ዕድገት ያበረከተው አስተዋፅኦ ዝቅተኛ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡ ስንዴ ከውጭ እያስመጣን የግብርና ምርት አድጓል ማለት የሚያዋጣ ፕሮፖጋንዳ አይመስለኝም፡፡ በተመሳሳይ የኢንዱስትሪ ምርትም ለአሥራ አንድ በመቶው ዓመታዊ የኢኮኖሚ ዕድገት የሚያደርገው አስተዋፅኦ ከፍተኛ ሊሆን አይችልም፤ ምክንያቱም ገበሬው ጭምር የሚጠቀምባቸውን የኢንዱስትሪ ውጤቶች ከውጭ ሀገር እያስመጣን ነው፡፡ ለምሳሌ፣የምግብ ዘይት እንኳን የምናስመጣው ከውጭ ሀገር ነው፡፡ ሌላው የኢኮኖሚ ዘርፍ የአገልግሎት ዘርፍ ነው፡፡ የትምህርት አገለግሎት፣የጤና አገልግሎት /የጤና ኬላዎች/ የትራንስፓርት አገልግሎት፣ወዘተ በመጠኑም ቢሆን የተስፋፉ የመስላሉ፤ግን ዕድገታቸው ከሕዝብ ዕድገት ይበልጣል ተብሎ አይገመትም፤ምክንየቱም አሁንም ከፍተኛ እጥረት ከመኖሩ በተጨማሪ ዕድገታቸው የተሟላ አይደለም፡፡ ለምሳሌ፣የዩኒቨርሲቲ ሕንፃዎች ተሠርተው ቤተመጻሕፍት አይኖራቸውም፤ወይም ብቃት ያላቸው መምህራን አይሠማሩም፡፡

ታዲያ ዕድገቱ የት ነው ያለው? ለዓይናችን ጐልቶ የሚታየን የመሠረተ ልማት ግንባታ ነው፡፡ ኢህአዴግ በየቀኑ በቴሌቪዥን የሚያሳየን ከሆነ ለፕሮፖጋንዳ ፍጆታ ሲባል የተጋነኑ ናቸው፡፡ የኃይል ማመንጫዎች /ተከዜ፣ግልገል ጊቤ፣ጣና በለስ፣ፈንጫ፣ወዘተ/ ተገንብተዋል፡፡ ብዛት ያላቸው መንገዶች ተሠርተዋል፡፡ በየከተማው በርካታ ትላልቅ ሕንፃዎች፣ኮንዶሚኒየሞች፣ ቪላዎች፣ወዘተ ተገንብተዋል፡፡ ብዙ የዩኒቨርስቲ ሕንፃዎችና የአንደኛና የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች ተሠርተዋል፡፡ እንደሚታወቀው፣የኃይል ማመንጫዎቹና መንገዶቹ በአብዛኛው የተሠሩት በውጭ ዕርዳታና ብድር ነው /ከቻይና፣አውሮፓ፣ዓለም ባንክ፣የአፍሪካ ለማት ባንክ፣ወዘተ/ የኢህአዴግ አባላትና ደጋፊዎች የሠሯቸው ትላልቅ ሕንፃዎችና ቪላዎች ደግሞ የተገነቡት በአብዛኛው በሀገር ውስጥ የመንግሥት ባንኮች በሰጡት ብድር ነው፡፡ ኮንዶሚኒየሞቹን በተመለከተ በ1996 የተመዘገቡት የመኖሪያ ቤት ፈላጊዎች ቁጥር ወደ 500,000 /አምስት መቶ ሺ/ ነበር፤በስምንት ዓመታት የኢህአዴግ መንግሥት ሊሠራ የቻለው የኮንዶሚኒየም መኖሪያ ቤቶች ከ80,000 /ሰማንያ ሺ/ በታች ነው፡፡

በሌላ በኩል፣ የኮንስትራክሽን ዘርፍ ለጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት የሚያበረክተው አስተዋፅኦ አሁንም አነስተኛ ነው፡፡ ባህላዊና ዘመናዊ ኮንስትራክሽን ተደምረው አስተዋፅኦአቸው ከ10 በመቶ እንደማይበልጥ ይገመታል፡፡ ስለዚህ፣የኮንስትራክሽን ዘርፍ በዓመት በ50 በመቶ እንኳን ቢያድግ፣ለጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ዕድገት የሚያበረክተው ድርሻ ከ 5 በመቶ አይበልጥም፡፡ (10x50/100)፡፡ ስለአለው እጥረት አኳያ፣የግብርና፣የኢንዱስትሪ እና የአገለግሎት ዘርፎች ምርት ከሕዝብ ዕድገት በታች እንዳደገ ነው የሚገመተው፡፡ የኮንስትራክሽን ዘርፉም ቢሆን ያደገው የዘመናዊ ኮንስትራክሽን ዘርፍ በመሆኑና ይህም ከጠቅላላ ኮንስትራክሽን ያለው ድርሻ የተወሰነ እንደመሆኑ፣ከላይ እንደተጠቀሰው ዘመናዊ ኮንስትራክሽን በ50 በመቶ እንኳን ቢያድግ፣ለጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ዕድገት የሚያበረክተው ከ2-3 በመቶ አይበልጥም፡፡ በዚህ ስሌት መሠረት፣ጠቅላላ የሀግር ውስጥ ምርት ያደገው ኢህአደግ እንደሚለው በዓመት በአሥራ አንድ በመቶ ሳይሆን፣ምንአልባት ከ2-5 በመቶ ብቻ ነው፡፡ የዘመናዊ ኮንስትራክሽን ዘርፍ በከፍተኛ መጠን ሊያድግ የቻለው፣የኢህአደግ ሥልጣን ከያዘ ጀምሮ ከውጭ የሚገኘው ዕርዳታና ብድር እጅግ ከፍተኛ በመሆኑ ነው፡፡ የደርግ መንግሥት ለልማት ያገኝ የነበረው የውጭ ዕርዳታና ብድር /በአብዛኛው ከቀድሞ ሶሻሊስት ሀገሮች/ በዓመት ከ300-400 ሚሊዮን ዶላር፣በወቅቱ በነበረው የብር ምንዛሪ ደግሞ ከ600-800 ሚሊዮን ብር አይበልጥም ነበር፡፡ የኢህአዴግ መንግሥት የሚያገኘው የውጭ ዕርዳታና ብድር ግን በዓመት እስከ አራት ቢሊዮን ዶላር ወይም አሁን ባለው የብር ምንዛሪ በዓመት 70 ቢሊዮን ብር ገደማ ነው፡፡ ታዲያ ይህን ሁሉ የውጭ ዕርዳታ የሚያገኝ መንግሥት መሠረተ ልማቶች ቢገነባ ምን ያስደንቃል? ያውም፣ከፊሉን እየዘረፈና እያዘረፈ፡፡ ተደጋግሞ እንደተነገረው፣በአለፉት ዘጠኝ ዓመታት ብቻ ከኢትዮጵያ ሕዝብ 11.7 ቢሊዮን ዶላር /204 ቢሊዮን ብር/ ተዘርፎ ከሀገር መውጣቱን የታመኑ ዓለም አቀፍ ተቋማት (ለምሳሌ global financial Integrity) ዘግበዋል፡፡

# የሰመጉ ጥሪ

የሰብአዊ መብቶች ጉባኤ (ሰመጉ) በቀድሞው የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ጉበኤ /ኢሰመጉ/ የቀመው ለህግ ልዕልና፣ ለዲሞክራሲና ለሰብአዊ መብቶች መከበር ነው። የሰመጉ አባል ይሁኑ። ዓላማውን ለማስፈጸም ይችል ዘንድ በገንዘብ ይደግፉ።

ስልክ 011 551-44089/011 551-77-04

አድራሻ ሣህለ ሥላሴ ሕንፃ 8ኛ ፎቅ ከአዲስ አበባ ስታዲየም ፊት ለፊት

# ሀገርን መበደል፣ዜጎችን ማሰቃየትና የሀገርና የሕዝብ ሃብትን መዝረፍ ይቁም ! !

በኢትዮጵያ ባለው የመልካም አስተዳደር እጦትና ከመቼም ጊዜ በበለጠ እየከፋ በመጣው የሙስና መስፋፋት ምክንያት በአገሪቱ ከዳር እስከ ዳር ከፍተኛ የሆነ የሀብትና ንብረት ዝርፊያ እየተካሄደና በሕዝብ ላይ ከፍተኛ የሆነ የግፍና የበደል ተግባር እየተፈፀመ እንደሚገኝ ይታወቃል፡፡

ይህ የመልካም አስተዳደር እጦት፣የሙስና መስፋፋት፣የሀገርና የሕዝብ ሀብትና ንብረት ዘረፋ እና በሕዝብና በዜጎች ላይ የሚደርስ ግፍ፣በደልና መከራ በሁሉም የሀገሪቱ ክፍል ከከፋው በላይ እጅግ በጣም የከፋውና ሀይ ባይ የጠፋው በይበልጥ በደቡብ ኢትዮጵያ ክልላዊ መንግሥትና በሥሩ ባሉት ዞኖችና ወረዳዎች ውስጥ ነው፡፡ ለዚህም ትልቁ ማሳያና ምሳሌ የሚሆነው የጋሞ ጎፋ ዞንና በሥሩ ያሉት ወረዳዎች፣ቀበሌዋች እና የዞን፣የወረዳ፣የከተማና የቀበሌ መስተዳድር ባለሥልጣናት፣ ሹመኞችና ካድሬዎች ናቸው፡፡

በጋሞ ጎፋ ዞን መስተዳድር የሕዝብና የዜጎች በደልና ስቃይ የጀመረው ገና ዛሬ አይደለም፡፡ ዞኑ እንደተመሰረተ አብሮ የተፈጠረና ቀስ በቀስ እያደገና እየተስፋፋ መጥቶ ዛሬ ከቀበሌ ጀምሮ እስከ ዞን ድረስ ያሉት ሹሞችና ባለሥልጣናት መሾምና ኃላፊነትን መያዝ ማለት ሀገርና ሕዝብን መበደል፣ዜጎችን አንበርክኮ መግዛት፣በእያንዳንዱ ዜጋና በየአካባቢው ባለው ሕዝብ ልዩ የጭቆና ቀንበርን መጫን፣ግፍና በደል መፈፀም፣ዜጎችን ከመኖሪያቸውና ከይዞታቸው እያፈናቀሉ ማባረር፣የሀገርና የሕዝብ ሀብት የሆነውን መሬት እየተቀራመቱ መከፋፈል፣ይህንን ድርጊት የሚቃወሙ ዜጎችን የማሰር፣የመቅጣት፣የማሰቃየት፣አካባቢውንና ሀገር ለቀ እንደጠፉ የማድረግ ኃይልና መብት የማግኛ መንገድ ሆኖላቸዋል፡፡

በዞኑ ውስጥ በጨንቻ፣በአርባምንጭ፣በቁጫ፣በጌዜ ጎፋ፣በደንባ ጎፋ ወረዳና በሌሎቹም ወረዳዎች ያለው ሕዝብ በመልካም አስተዳደርና በፍትህ እጦት ተሰቃይቶ ወደ ዞን፣ወደ ክልልና ፌደራል መንግሥት መመላለስ እጣ ፈንታው ሆኗል፡፡

ለምሳሌ፡- በጨንቻ ወረዳ ውስጥ፡-

1. በቅርብ ጊዜ የጨንቻ ከተማን በማስፋፋት ሰበብ በከተማው ዙሪያ ባሉ ዘጠኝ ቀበሌዎች ላይ የተወሰደው መሬት የመንጠቅ፣አርሶ አደሮችን ከሀብት ንብረታቸው የማፈናቀል፣ የዘጠኙን ቀበሌ ሕዝብ ለሥቃይና ለመከራ የመዳረግ እርምጃ በወረዳው ውስጥ ሲፈፀም ከቆዩ ኢ-ፍትሃዊ ድርጊቶች ሁሉ የከፋውና በሕዝብ ላይ የተከፈተ የጅምላ ጥቃት ተግባር ነው፡፡ ይህን የጅምላ ጥቃት ተግባር በመቃወም ንብረታቸውን አናስነጥቀም ብለው ለአቤቱታ በወጡ የሻዬና የሎሻ ቀበሌ ነዋሪዎች ላይ የከተማው ጥበቃ ኃይልና ፖሊስ በፈፀመው ድብደባ 3 ወንዶችና 3 ሴቶች ላይ ከፍተኛ ጉዳት ደርሶባቸዋል፡፡ ሌሎችም ብዙ ሰዎች በደረሰባቸው ድብደባ ለጉዳት ተዳርገዋል፡፡

2. በዶኮ ሻሌ ቀበሌ ገበሬ ማሕበር ሕዝብ ላይ በደረሰውና እያደረሰ ባለው በደል ምክንያት ሕዝቡ አቤቱታ ይዞ ወደ ዞንና ክልል መንከራተት ከጀመረ አራት ዓመታት አልፏል፡፡ በዚህ መሀል የቀበሌው ነዋሪዎች ይታሰራሉ፣ይቀጣሉ፣ ይከሰሳሉ፣ከአካባቢያቸው እንዲሰደዱ ይደረጋሉ፡፡ ከ20 በላይ የቀበሌው ነዋሪዎች በእስራትና በገንዘብ ተቀጥተዋል፡፡ ከ10 በላይ እየተከሰሱ ያሉ ሲሆን በርካታዎች ከአካባቢው ተሰደዋል፡፡

3. የኤዞ አካባቢ ሕዝብ ለደረሰበትና ለሚደርስበት በደል መፍትሔ የሚሰጥ አካል አጥቶ አቤቱታ ይዞ ወደ ዞንና ክልል በመመላለስ ለበርካታ ዓመታት ተንከራትቷል፡፡ በአካባቢው ዜጎች በግፍ ይታሰራሉ፣ይቀጣሉ፣ይንገላታሉ፣ይሰቃያሉ፣

4. በጋሞ ጎፋ ዞን በአርባምንጭ ወረዳ የላንቴ ቀበሌ ሕዝብ በቀበሌና በወረዳ መስተዳድር ሹሞችና ካድሬዎች የደረሰበትን በደልና ጥቃት በተመለከተ ከዞን እስከ ክልል ድረስ ተንከራተው መፍትሔ የሚሰጥ አካል በመጥፋቱ እስከ ፌዴራል መንግሥት ድረስ አቤቱታ ለማቅረብ ተገደዋል፡፡ ለመብታቸው አቤቱታ በማቅረባቸውም ከ60 በላይ የላንቴ ነዋሪዎች ለእስራትና ለቅጣት ተዳርገዋል፡፡

5. በተመሳሳይ በቁጫ፣በጌዜ ጎፋ፣በደንባ ጎፋና በሌሎችም ወረዳዎች በተቃዋሚ ፓርቲ አባላት፣ደጋፊዎችና በሕዝብ ላይ እየደረሰ ያለው በደል፣ከቤት ንብረት ማፈናቀል፣መሬት መቀማት፣የዜጎችን ቤት ንብረት ማቃጠል፣ዜጎችን ማሰር፣ማሰቃየትና የመሳሰሉት የግፍ ተግባሮች ተባብሰው ቀጥለዋል፡፡ ስለዚህ፡-

ሀ/ በደቡብ ኢትዮጲያ ክልላዊ መንግሥት በጋሞ ጎፋ ዞን ውስጥ ባሉ ወረዳዎች በተለያየ አካባቢዎችና ቀበሌዎች በሕዝብ ላይ እየደረሰና እየተፈፀመ ያለው ግፍና በደል፣እስራት፣እንግልትና ወከባ፣

ለ/ በጨንቻ ወረዳ በዘጠኝ የከተማው አጎራባች ቀበሌዎች ላይ የተጀመረው የአርሶ አደሩን መሬት የመቀማትና ሕዝብን የማፈናቀል ተግባር፣እንደዚሁም በዶኮ ሻሌ ገበሬ ማሕበር የቀበሌውን ክልል በኃይልና በጉልበት ለማስወሰድ የሚደረገውን ህገ-ወጥ ተግባርና በዚህ ምክንያት በሕዝቡ ላይ እየተፈፀመ ያለው እስራት፣ቅጣት፣እንግልትና ወከባ በኤዞ አካባቢ ሕዝብ ላይ እየተፈፀመ ያለው በደል፣እስራት፣ቅጣት፣እንግልትና ወከባ፣

ሐ/ በአርባምንጭ ዙሪያ ወረዳ በላንቴ ቀበሌ ገበሬ ማሕበርና በሌሎች ቀበሌዎች ሕዝብ ላይ እያደረሰ ያለው ግፍና ወከባ፣እስራትና እንግልት፣

መ/ በቁጫ በጌዜ ጎፋ፣በዴንባ ጎፋና በሌሎችም ወረዳዎች በሕዝብና በተቃዋሚ ፓርቲ አባላት ላይ እየደረሰ ያለው ጥቃት፣እንግልትና ማዋከብ እንዲቆም፣በዞኑ ባሉ ወረዳዎች በሕዝብና በዜጎች ላይ እየደረሰ ያለው የሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶችን እየጣሱና እየረገጡ ያሉ ባለሥልጣናትና ካድሬዎች ላይ ሕጋዊ እርምጃ እንዲወሰድና ለፍርድ እንዲቀርቡ እንዲያደርግ

ሠ/ በጋሞ ጎፋ ዞን ከዞኑ ዋና ከተማ አርባ ምንጭ ጀምሮ በሌሎች የወረዳ ከተሞችና የገጠር መሬት ላይ በባለሥልጣናት፣በካድሬዎችና በዘመድ አዝማድ አማካይነት እየተካሄደ ያለው የሙስና ተግባር እንዲቆም፣በሙስናው ሂደት ውስጥ የገቡ ባለሥልጣናትና ካድሬዎች ጉዳይ ተጣርቶ ለሕግ እንዲቀርቡና የሀገርና የሕዝብ ሃብት በሆነው መሬት ላይ እየተፈፀመ ያለው በዘመቻ ተከፋፍሎ የመያዝ ተግባር እንዲቆም እንጠይቃለን፡፡

የጋሞ ዴሞክራሲያዊ ሕብረት ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ
ታህሣስ 30 ቀን 2004 ዓ.ም

## የኢትዮጵያ ሕዝብ ቆራጥ . . .

ከገፅ 13 የዞረ

የፖለቲካ ድርጅትና መሪ መኖሩ ማረጋገጫ ነው፡፡

ከነዚህም በላይ የግለሰቦችን መፈተኛ ነው፡፡ በመሆኑም መድረክ ቀደም ብሎ ምርጫ ከመድረሱ በፊት ውህደቱ አድርጎ በሕዝብ ዘንድ ያለው ጥርጣሬ እና መንፈስ ሰብሮ እውነተኛ የሕዝብ ድርጅት መሆኑ ማስመስከር አለበት፡፡ ለዚሁም ሕዝብንና ድርጅት አታጋይ መሪውን ማሳወቅ አሁን የምናየው የሕዝቡን ችግር መስማት ብቻ ሳይሆን በተጨባጭ አሁን ትግሉ የሚጠይቀው የውሳኔ አሳብ ጭምር ነው፡፡

አንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትሕ እና ከብርሃን ለአንድነትና ለዴሞክራሲና ለፍትሕ ያደረጉት ውህደት ለመድረክ ትልቅ ትምህርት የሰጠው ቢሆንም በሀገራችን ያሉት የፖለቲካ ፓርቲዎች ግን ፍቃድ አውጥቶ ቢሮ መከራየት የሕዝብ ትግል መስሎአቸው በራሳቸው ላይ እንዳያፌዙ ለመጀመሪያ ጊዜ እንዲማሩ ማድረጋቸው ወቅታዊ የሕዝብን ጥያቄዎች ፈተዋል፡፡ ይሄም ይበል የሚያሰኝ መሆኑ ሕዝቡ እየተነጋገረ ነው፡፡ በአንድነት የአምስት አመት እስትራቴጂ ላይ በግልፅ እንደተቀመጠው ከመድረክ ጋር ያለውን ውህደት በቁርጠኝነት እየተንቀሳቀሰ መሆኑ በዋናነት ሕዝባዊ መሠረቱን እያስመሰከረ ነው፡፡ ይህ ካልተሳካ ግን ከወዲሁ ከሚቀሩት ፓርቲዎች ጋር በመዋሀድ ታሪካዊ ድርሻውን መወጣት አለበት፡፡ ይህን ማድረግ ደግሞ ሕዝብን ብቻ የሚያኮራ ሳይሆን በፓርቲው ውስጥ የተከፈለው መስዋህትነት ማንጸባረቂያ ድል ነው፡፡ የዚህን ፅሑፍ ከመደምደሜ በፊት የአንድነት ለዴሞክራሲ ለፍትህ የብሔራዊ ምክር ቤት አባልና ሥራ አስፈፃሚ የሆኑት ዶ/ር ንጋት አስፋው ከፍኖተ ነፃነት ጋር ቁ. 21 ጋር ካደረጉት ቃለ መጠይቅ ላይ የተናገሩትን በመጥቀስ ፅሁፌን እደመድማለሁ፡፡

ጋዜጠኛው "የኢትዮጵያ ህዝብ ደፋር ነው፤ አይበገሬ ነው ይባላል፡፡ ዛሬ ደግሞ በፍርሃት ቆፈን ውስጥ ተጨብጦ ይገኛል፤ ድሮ ጀግና ነው የሚባለው ውሸት ነው ወይስ የዛሬ ፍራቱ ከምን የመጣ ነው?" ተብለው ለተጠየቁት ጥያቄ የሰጡት መልስ እንዲህ ነበር ያሉት፡፡ "የኢትዮጵያ ሕዝብ ጀግና እንደነበር በርካታ የታሪክ ምስክሮች አሉ፡፡ ዛሬ ፈሪ ለመሆኑ ተጨባጭ ማስረጃ አለ ወይ? በእኔ እምነት ዛሬም ደፋር ነው ብዬ አምናለሁኝ፡፡ በድፍረት ለመጓዝ ጥሩ መሪ ያስፈልገዋል፡፡ ነጥሮ የወጣ ማን መሪ አለና ነው? ፈርተህ አልተከተልከኝም ብለን የምንወቅሰው፤ የተፈተነ የሚታመንበት መሪ ካገኘ ዛሬም ወደ ኋላ የሚመለስ ህዝብ አይደለም፡፡ ጀግንነቱ ከጦርነት ጋር ብቻ የሚያያዝ አይደለም፡፡ የዛሬው የሚጠብቀው ጀግንነት ረሃብን ለማጥፋት ከአብራክ የወጡ ጨቋኝና አንባገነን ገዢዎችን አሽቀንጥሮ ለመጣል መታገል ይፈልጋል፡፡ ይህን ለማድረግ ቆራጥ መሪ ያሻል፡፡ ቆራጥ መሪ ካለ ዛሬም የኢትዮጵያ ህዝብ ደፋር ነው፡፡" ነበር ያሉት እናም አሳባቸውን እየተጋራው ቆራጥ መሪና መድረክን በዝች አጭር መልዕክት ፅሑፌን አጠቃልያለሁኝ፡፡

የእናት አገር እንባ መልቶ እስኪፈስ፣
እያየን ዝም ነውተርቦ ሲያለቅስ?
ወይስ እየሰሩ እንባውን ማበስ!

## ተቋሙ የሚተዳደረው ...

ከገፅ 4 የዞረ

ሁሉ ይቅርታ ጠይቀው የተበላሸውን ለማስተካከል ደፋ ቀና ይላሉ፡፡ የ68 ዓመት አዛውንትና የተማሩ ዶክተር ናቸው፡፡ የቀማኛና የበዳይ ሳይሆን የጨዋና ድሃ ኢትዮጵያዊ ቤተሰብ ውጤት ናቸው፡፡ ኧረ -ስንቱ! ታድያ ምን ቢበድሉ ነው ስሜታቸው እንዲጎዳ የተፈለገው? አስተምህሮቱስ ታስቦበታልን? አንድነታውያን ሁሉ ግን አሁን ያሉት የሀገር መሪዎች፤ ነገ ተራ ሰዎች ሲሆኑ ክብራቸውን ማስጠበቅ ግዴታችን መሆኑን እናውቃለን፡፡ መንግሥት ስንሆን! በሌላም በኩል ሁላችንም የተቃዋሚ አባላት ውክልና አለን፡፡

አንድነት ባካሄደው ሁለተኛ መደበኛ ጉባኤ በርካታ ተሳታፊዎች ከአራቱም አቅጣጫ ተገኝተዋል፡፡ የማንም ፓርቲ አባላት አያድርጉትም፡፡ ተጠቃሚዎቹ የኢህአዴግም ቢሆን፡፡ አሁን የሚነገድባቸው ጀግኖቹ የህወሓት የትጥቅ ትግል ወቅት ታጋዮች ገንዘባቸውን ሳይሆን ህይወታቸውን ለተሰረቀው ትግል ሰጥተዋል፡፡ አሁን ግን ማንም፤ የማንም ድርጅት አያደረገውም፡፡ የአንድነቶች ግን አድረገውታል፡፡ ዳቦ በሻይ እየበሉ፤ ተንጠላጥለው ተጓጉዘው በራሳቸው ወጪ 4-5 ቀን በአዲስ አበባ አሳልፈዋል፡፡ ስለአገራቸው፣ ስለህዝባቸውና ስለ ድርጅታቸው መክረዋል፡፡ እነዚህ የድርጅቱ የቁርጥ ቀን ልጆች በቀጥታ በምስጢር ድምጽ መሪያቸውን መርጠዋል - ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳን፡፡ የተከበሩ አቶ ግርማ ሰይፉም የብሔራዊ ምክር ቤት አባል በመሆን በነዚህ አባላት ዘንድ በከፍተኛ ድምጽ ተመርጠዋል፡፡ የጉባኤውን ውበት፣ ብስለትና ጥልቀት በርካታ እንግዶችና የተከበሩ የብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ተወካዮችም ተገንዘበውታል፡፡ ለዚህ ድርጅት አባላት ክብር ሲባልም መሪዎቹ ይከበሩ ዘንድ ይገባ ነበር፡፡

ተቃዋሚን በጠላትነት መፈረጅ የህወሓት/ኢህአዴግ ተፈጥሮአዊ ባህሪ መሆኑን ብዙዎች ይመስክራሉ፡፡ የመንግሥትነት ሥልጣን ጨብጦም አመራሩ ባህሪውን እንዳልቀየረ በተለያዩ መድረኮች እያንፀባረቀው ይገኛል፡፡ ህገ-መንግሥታችንና ሌሎች የአገሪቱ ህጎች ፖሊስና የፍትህ አካሉ ከፓርቲዎች ቁጥጥርና ተጽእኖ ነፃ መሆናቸውን ይጠቁማሉ፡፡ በህጎቹ መሠረት ፖሊስቹ ነፃ ናቸው ብዬ አምናለሁ፡፡ ይህ ባለማእረግ ተረኛ የማረሚያ ቤቱ መኮንን የቀድሞውን የሀገሪቱን ፕሬዚደንትና የተቃዋሚ መሪ፤ እንዲሁም ከፍተኛ የመራጮች ድምጽ አግኝተው ፓርላማ የገቡትን የህዝብ ተወካዮች ማንጓጠጥ ከየት የመነጨ ጥላቻ ነው?

አንድነት የጥላቻና የበቀል ፓርቲ አለመሆኑን በተደጋጋሚ ገልጿል፡፡ ችግሮችን በውይይትና በድርድር የመፍታት ዘይቤን አጥብቆ ይከተላል፡፡ የኢህአዴግ መሪዎች ግን በብቸኝነት በሚቆጣጠሯቸውና በህዝብ ገንዘብ በሚተዳደሩ ሚዲያዎች የአንድነትን ጥላቻ ለአባሎቻቸው ይሰብካሉ፡፡ ከሚሊዮኖች አባሎቻቸው ጥቂቶቹ የጥቅም ተጋሪዎችና ቤተሰቦች እንዳሉ እናውቃለን፡፡ ህዝቡም በደንብ ለይቶ ያውቃቸዋል፡፡ እነዚህ ግለሰቦች የተቃዋሚዎችን መሪዎች በጥላቻና በጥርጣሬ እንዲመለከቱ የሥነ- ልቦና ዘመቻ ይደረግባቸዋል- በኢህአዴግ ቁንጮ መሪዎች፡፡ የማረሚያ ቤቱ ፖሊሶች ሁሉ ከፖለቲካ ነፃ ናቸው፡፡ ይህ ተረኛ ባለማእረግ የፖሊስ ባልደረባ ግን ያየሁበት ጥላቻ ከነዚህ የሥነ-ልቦና ቀውስ ውስጥ ካሉት ጥቅመኞች አባሎች የበለጠ ነበር፡፡ ፈውሱን ይሰጠው ዘንድ እፀልያለሁ፡፡ የሚመለከተው አካል ለዚህ ጉዳይ አጽንኦት ሰጥቶ መፍትሔ ያበጅለት ዘንድም እምነቴ ነው፡፡ ተሰድበውና ተመናጭቀን ስንወጣ ተሰልፈው የሚገቡ በርካታ ዜጎች ነበሩ፡፡ አንድ ሴት ግን ቀልቤን ሳበችው፡፡ ጀግና የሴት ኮለኔል አየሁ፡፡ አሁን በጡረታ ላይ ትመስለኛለች፡፡ አላዘንኩባትም፡፡ ለኔና ለህዝቧ ነፃነት የታገለች፤ ከቀውጢ ጦርነቶች ሁሉ ያመለጠች ነች፡፡ ወሬ የማታውቅ የተግባር ሰው እንደነበረች እሰማለሁ፡፡ የቤት መኪና ታርጋና ሾፌርዋን ይዛ ወረደች፡፡ ባለቤቷ «የአኬልዳማ ድራማ» አዘጋጅ የኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ሥራ አስኪያጅ ነው፡፡ ስለዚህ ጉዳይ ምንም ማለት አያስፈልገኝም፣ ህዝቡ ያውቀዋልና፡፡ የምትጠይቀውን ልትጠይቅ በእለቱ በቃሊቲ ታሳሪው ብዙ፣ ጠያቂውም መአት ነውና አላየችንም ብዬ አገምታለሁ፡፡ አላስተዋለችም፡፡ እኔ በደንብ ባውቃምትም እሷግን ጭራሹን አታውቀኝም፡፡ በርግጠኝነት የቀድሞ ፕሬዚደንቷን ግን ታውቃለች፡፡ ህዝብ የመረጣቸውና ህጉ የሚፈቅድላቸው የፓርላማው ተወካይ ተሰድበው ሁላችንም ተመናጭቀን ተመልሰናል፡፡ ብንነግራት ምን ይሰማት ይሆን? ሌሎችን ጓዶችዋን ለፍትሕ ፣ ለዴሞክራሲ፣ ለነፃነትና ለእድገት ገብራ አልፋለችና የምታደርገው ነገር ባይኖርም እንደሚሰማት ግን እገምታለሁ፡፡ እኔ ግን አዘንኩላት- ነፃ አልወጣሁምና!

እርምት ፡- ባለፈው ሳምንት ባወጣነው እትም የአቶ ደምሴ መንግስቱ እድሜ 48 ተብሎ የተገለፀው 42 ተብሎ ይነበብ።

# ለመላው የክርስትና እምነት ተከታዮች በሙሉ እንኳን ለብርሃነ ጥምቀቱ አደረሳችሁ።
# በዓሉ የሠላም የጤና የፍቅር እንዲንሆንላችሁ እንመኛለን

## አንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ /አንድነት/
## 2004 ዓ.ም

የኢትዮጵያ ሕዝብን የሥልጣን ባለቤት ለማድረግ በሚደረገው ትግል የግልዎን ድርሻ መወጣት ይፈልጋሉ?
እንግዲያውስ ለዚህ አላማ በፅናት ለሚታገለው አንድነት ፓርቲን በሞራል፣ በሀሳብና በገንዘብ ይርዱ።

አንድነትን በገንዘብ መርዳት ለምትፈልጉ፤
አንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትሕ ፓርቲ
የሂሳብ ቁጥር፡- 510
ንብ ባንክ፣ ዑራኤል ቅርንጫፍ ገቢ ያድርጉ።

ድረ-ገፅ: www.andinet.org
E-mail: andinet@andinet.org
or udjparty@gmail.com
Tel. 0111226288